
# የጠብታ ፍንጣቂ!*

(ገ.ኀ.ብልጣሶር)



ከመከራ ለብራክና ከሥቃያት ማህፀን ተፈልቅቀው የወጡ ፤ የአሥራ አምስት ጥቁር
አመታትን ያሳዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ታሪካዊ ውልዶች።

## የጠፍ.ቁ.2—12

* በተከታታይ የሚወጡ ያጫጭር ልበ-ወለድ ታሪኮች

ማኅደር ገጽታ ይህ ነው።

Oct.20/2

STOCKHO

Yeshigigir Deba
(G.N. Biltasor)
Författares Bokmaskin, Stockholm 1990
ISBN 91 7328 675 3
July 1989
STOCKHOLM — SWEDEN

# የምንገኝበት መጠቆምያ

**ሥያሜያችን** **አድራሻችን**

1. የአርእስትገጽ ........ 1
2. የምንገኝበት መጠቆሚያ ........ 3
3. የእርስዎ እስካልሆን ድረስ ........ 5
4. መዘክሩ ትሁንልኝ ........ 7
5. እንተዋወቅ ........ 9
6. የሽግግር ደባ ........ 65
7. አዋልደ-ወንዴ ........ 79
8. የተጣሰ አጥር ........ 103
9. ሞኝ ባገኝ ........ 137
10. ሩብያ ........ 169
11 ዘሊባኖስ ........ 203
12. እየመረረ የሚጣፍጥ ........ 239
13. ሠመኑ ........ 269
14. እናቴን ለመቅበር ........ 303
15. ብድር በምድር ........ 327

# የርስዎ እስካልሆነ ድረስ

" ኀሊና ያለው ሰው " ማለት የሞራል ሕግ የሚገዛው ነው። እንደዚያ ዓይነቱን ሰው ደግሞ የገዛ ራሱ ያልሆነ ነገር ሁሉ አይማርከውም። በመሆኑም የሌሎችን " አትመኝ፣ አትንካ፣ አትስረቅ....." ብለው አይነግሩትም። የዚህች ቍንጽል መጣፍ ባለቤትነት የርስዎ እስካልሆነ ድረስ፣ ያለደራሲው ፈቃድ በፈለ ጉት ሁኔታ ለመጠቀም እንደማያስቡ በባለኀሊና ሰውነ ትዎ ደራሲው ተስፋ ያደርጋል።

# የጠለቀ ምሥጋና

ይህ መጽሐፍ፣በዚህ መልኩ ታትሞ እንዲወጣ ግማሹን ያህል ርዳታ ለሰጠኝ፣እንድ መንግሥታዊ ድርጅት፣ስሙ ተጠቅሶ መመሥገን ባለመፈለጉ ተውኩት እንጅ፣መጽሐፋን አግኝተው የማንበብ ዕድል በሚያጋጥማቸው ወገኖች ስም፣ የጠለቀ ምሥጋና (djupa tacksamhet) ለማቅረብ ወስኜ ነበር።

ሌላው እንኳ ቢቀር፣ "ሞያ በልብ ነው" እንደሚባለው፣ ድርጅቱ "አታመሥግኑኝ" ማለቱ ብቻ፣ሊያስመሠግነው ይገባም ነበር። በዚህ አጋጣሚ፣ ይህ ድርጅት የሚመራበት ታላቅና ክቡር ዓላማ፣ገና በማደግ ላይ ለሚገኙ ለየብሔረ-ሰቡ ሥነ-ጽሑፍ አምራች ደራስያን ሁሉ፣ ርዳታዊ ተልእኮው፣"በርቱ!" የሚል ማነቃቂያ በመሆኑ፣በይፋና ባደባባይ ሊያደንቁት የሚገባ ነው።

ይህን እትም ከሌሎቹ እትሞች ሁሉ ልዩ የሚያደርገው፣ የማሳተሚያውን ግማሽ ወጭ የሸፈነው፣በ" ጠረጋ ሥራ"(ተግባረ-ጽዳት) የተገኘ አበል መሆኑ ነው። ምናልባትም ጉድፋ መካን ባለመሆኑ፣ገና ብዙ አስደርሶ ያሳትምልኝ ይሆናል።



# መዘክሩ ትሁንልኝ



መምህር ጣሰው ቸርነት
( 19?? - 19?? )

(ያልኖረበትን ሕይወት መመዝገቤ ምን ይጠቅመዋል?)

ይህ ዓለም ለሰው ልጅ ሲባል እንጅ፣ በተቃራኒው የሰው ልጅ ለዓለም ሲባል አልተፈጠረም። በመሆኑም፣ የዓለማችን ዓቢይ ቁም ነገር፣ የሰው ልጅ ነው። ይህ እስከሆነም ድረስ፣ ጠቅላላው ዓለም ለሰው ልጆች ፍስሐና ተድላ ሊያረግድለት ይገባል እንጅ በግልብጡ፣ የሰው ልጆች ለዓለም ምርቅና ሊያደገድጉለት አይገባም። ዓለም በባሕርዩም ሆነ በተፈጥሮአዊ መዋቅሩ፣ ለሰው ልጆች ርካታ ተስማሚና አመች ሆኖ መዘጋጀቱን እናውቃለን። የሰው ልጅ ኅሊናዊ ጡንቻው በጐለበተ መጠን፣ ዓለምን እንደ ወላድ ጥገት የፍላጎቱን ያህል፣

ሲሳያዊ ወተቱን ሊያልብ ይችላል። በሕዋና በየብስ፣ በባሕርና በውቅያኖስ፣ ዓለም አርግዞት ያለው የሚሳይ ድልብ፣ ይህን ያህላል ብሎ ለመናገር ያስቸግራል። ገና ያልተነካው የሕዋ ውስጥ ጠቋር መካናት ( Black Spots) ብቻ፣ አርግዞት ያለው ኃይለ-ጉልበት፣ ፍፁም ድንግል ነው። በየብስ ውስጥም ተሠውረው ያሉ ልዩ ልዩ ማዕድናትም፣ ለዘመናት የሚዛቁ የጠቅላላው የሰው ልጅ ድልባዊ ቅርሶች ናቸው። የታላላቆቹ ውቅያኖሶች ወለሎች ብቻ፣ አፍነው በያዙት ሀብት አንፃር፣ የሰውን ልጅ ከህላዌ ቀቢፀ ተስፋ፣ ነፃ የሚያወጡ ጽንፍ የሌላቸው የሕይወት ኣለኝታዎች ናቸው።

ይሁን እንጅ፣ እንደ ኣጋጣሚ ሆኖ፣ እፍኝ በማይሞሉ የስግብግቦች ዕቡይ አርአያነት ተፅዕኖ የተነሣ፣ የሰው ልጆች ያለ ተፈጥሮአዊ ተልእኮአቸውና ያለ ዓለማችንም ነባር ባሕርይ፣ ለዓለሙ ሲያረግዱለትና ሲያብዱለት እናያለን። በአንፃሩም፣ ይህ ዐይነቱ ኢሰብኣዊ ዝንባሌ የማይሰማቸው፣ ብዙ ግሑሳን ሰዎች በየሀገሩ ማኅበረ-ሰብ ውስጥ ይገኛሉ። የነዚህ ሰዎች ምድራዊ ሕላዌ ግብ የተነደፈው፣ ለዓለሙ መብለጭለጭ ሳይሆን፣ ለሰው ልጆች ጤናማ ሕይወት ዋስትና ላይ ነው። የነዚህ ሰዎች አጠቃላይ ተጋድሎና መሥዋዕትነት፣ ለሰው ልጅ መሠረታዊ ሕይወት የጋርዮሽ ሕጋዊ ርካታ ማግኘት ነው። ስለዚህም፣ የራሳቸው ግለኛ ኑሮና ሕይወት፣ ዶጋመድ ቢሆንና አፈር ድሜ ቢግጥ፣ ጨርሶ ደንታቸው አይደለም። ዠምበር ሠርቃ እስክታርብ ድረስ፣ የየቀኑ ተግባራቸው፣ የሰውን ልጅ በሚችሉት ሁሉ ማገልገል ነው። ለግላቸው ጥቅምም ሆነ ዝና፣ ለራሳቸው ምቾትም ሆነ ብልፅግና በፍፁም አያልሙም። ለታመመው መድኃኒት፣ ለመሐይምኑ እውቀት፣ ለተራበው ምግብ፣ ለታረዘው ልብስ፣ ለሚበሳጨው መጽናናት፣..... ሆነው





በማገልገላቸው ብቻ ራሳቸውን እንዳገለገሉ ያህል ይሰማቸዋል። ሞራላቸውና ሥነ-ምግባራቸው፣ ሰውን ባለ አቅማቸው በማገልገል ላይ የተመሠረተ ነው። ከዚህ ሰብዓዊ ልግሥናና በጎምግባር ውጭ፣ እነዚህን ሰዎች ሌላ ነገር አይታያቸውም። ባስተሳሰባቸው ክልል ውስጥ “ ለኔ- ለግሌ ” የሚል ስሜትና ዝንባሌ አልሠረፀባቸውም። እነዚህን የመሰሉ ሰዎች፣ ቁጥራቸው ኣይብዛ እንጅ፣ በየዘመኑ ጣቢያዎች ላይ ብቅ ብቅ እያሉ አልፈዋል። እጅግ በጣም የሚደንቀኝ ግን፣ እነዚህን መሳይ ሰዎች ዓለምም ሆነ ሕዝብ በሥርዓት ሳያውቃቸው ማለፋቸው ነው። ተደብቀው ተወልደው፣ ተደብቀው ኖረው፣ ተደብቀው ያልፋሉ።

ከነዚህ መሰል ሰዎች አንዱ መምህር ጣሰው ነበር። የዚህን ወንድም፣ ክቡር ሰብዕናና ግሑስ ባሕርይ፣ ኣሟልቶ ለመግለፅ እጅግ በጣም ያስቸግራል። ምንም ዓይነት የብዕር ኃይል ሊገልጸው የማችልም ሆኖ ይሰማኛል። እንደ ማንኛውም ሰው ሁሉ ከሰው የተገኘ በመሆኑ፣ የደረጁ ወላጆች እሉት። ይሁን እንጅ፣ መምህር ጣሰው ኣዘውትሮ አያገኛቸውም ነበር። ለተሰለፈበት ማኅበራዊ ተግባር፣ አብዛኛው ጊዜውን የሠዋ በመሆኑ፣ የቅርብ ወላጆቹን እንኳ ለመጎብኘት በቂ ጊዜ አልነበረውም።ልጅነቱ፣ የማኅበረ-ሰቡ ነበር።

መምህር ጣሰው፣ እንደኛ ላለው ሕዝብ፣ መዳኛ መድኃኒቱ ትምህርት ብቻ መሆኑን ቀደም ብለው ከተረዱት ጥቂት ወገኖች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ብዙ ሲሳይ ሊያስገኝለት ከሚችለው የሠዓሊነት ሙያው ኣፈንግጦ በመውጣት፣ መምህራን ለመሆን ከሚዘጋጁ ወጣቶች ኢንስቲትዩት ተሠማርቶ በፍፁም ቅንነት ያስተምር ነበር። ከምድብ የመምህርነት ሥራው ውጭ ትምህርት ቤቱን እንደ ግል ቤተ-ሰቡ በመቍጠር፣ ሌላው

ቀርቶ እዚያው ትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚያድርበት ቀናት ጥቂት አልነበረም። ከሥራው መመሠጥ የተነሳ፤ የምግብ ሰዓቶችን ሳይቀር ይዘነጋቸው ነበር። ተማሪዎቹን እንደግል ልጆቹ ስለሚቆጥራቸው፤ እጅግ ይሳሳላቸው ነበር። ታዲያ ያን ሁሉ የሚያደርገው፤ የራሱ ሕፃናትና የግሉ ቤተሰብ ሳይኖረው ቀርቶ አይደለም። እነሱንም ቢሆን አንዳንድ ጊዜ ለማምንት ያህል፤ እስከ መኖራቸው ድረስ ይረሳቸው ነበር። በመምህር ጣሰው ኅሊና ውስጥ ምንጊዜም የሰፈነው፤ እንደ ዐይኑ ብሌን የሚሳሳለት ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ እድገትና መሻሻል ነበር። የሚያስበውን ያህል፤ የወገኑ እድገት እጅግ ባለመራመዱ፤ የመንፈስ ብስጭት እያደረበት፤ ጤናው ይረበሽ ነበር።

ምድብ የስነ-ጥበብ ትምህርቱን በሚያስተምርበት ወቅት፤ በተማሪዎቹ ዘንድ ብቻ ሳይሆን፤ በሌሎች መምህራንም ጭምር ከፍተኛ አድናቆትን አትርፎለታል። በመረጃነት የሚያቀርባቸው የተለያዩ ናሙናዎች ሳይቀሩ፤ እጅግ የሚያስደንቁና ከዚያው ካካባቢው የሚሰበስባቸው ነበሩ። ከሌሎች መምህራን ጋርም የነበረው መግባባትና የሚያደርጋቸውም ውይይቶች፤ ኅሊናን ሠንጥቀው የሚገቡ ቁም ነገሮች ነበሩ። ከሁሉም ደግሞ፤ ከዚያ ሁሉ ችሎታውና ተሰጥዎው ውጭ የሚታይበት ትህትና የፍፁምነት ሰብዕናውን የሚያንፀባርቅ ልዩ ምልክት ነው። በዚያ የእጩ መምህራን፡ መሠልጠኛ መናኸርያ ውስጥ፤ የእንደ መምህር ጣሰው ዓይነት ሰው መኖር ከሚሰጠው ምድብ ትምህርት ይልቅ፤ አርአያነቱ ከፍተኛ ዕሴት አለው። አንዳንድ ተማሪዎችን ለመጎብኘት የሚመጡ እንግዶች፤ መምህር ጣሰውን ቅዳሜና እሁድ ጭምር ዶማና አካፋውን ይዞ ሲያዩ፤ የትምህርት ቤቱ አትክልተኛ እንጅ የቀለም መምህር አይመስላቸውም ነበር። ጊቢውን በጽጌያትና በተክሎች አሸብ





ርቆት፤ ገነተ-ጽጌ ምሥጋን ይገሚው። እንዲውም ካለበት ትውልድ አልፎ ለመጭው ትውልድ ጭምር የሚያስብ ሰው መሆኑን የተከላቸው ዕፀዋት ጭምር ሳይቀሩ ይመሰክሩለታል። ዘመናት ቆጥረው የሚያፈሩ ተክሎች ሳይቀሩ በጊቢው ውስጥ ነበሩት። " ጅል ሰው የመጨረሻዪቱን ድንች ሲበላት፤ ጠቢብ ሰው ግን ይተክላታል " እንዲሉ፤ መምህር ጣሰውም፤ የባለ ዘጠና ዓመቱ አረጋዊ፤ የብርቱካን ችግኝ ተክሎ ውሃ ሲያጠጣ ያየው አንድ ሞኝ " ምን ትፋሽካለህ መቶ ደርሶልህ ለመብላት ነው? " ሲል በማፌዝ ቢጠይቀው " መጪው ትውልዴ ይመገብልኛል " እንዳለው ሰው ዓይነት ነበር፤ አትክልታዊ ተግባሩ። እንዲህ ዓይነቱ የመምህር ጣሰው የየቀኑ ተግባር፤ ጥቂቱ ክፍል ብቻ ሲጠቀስ ነው። ይህ ተግባሩም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ብቻ የሚታየው ሲሆን፤ ከትምህርት ቤቱ ውጭ የሚያከናውናቸው ልዩ ልዩ ሥነ ምግባሮቹን መዘርዘር ያስቸግራል።

እንደ እድር ባሉት የማኅበረ-ሰቡ ባሕላዊ ማኅበራት ውስጥ፤ መምህር ጣሰው ዓይነተኛው ቁልፍ ነበር። በእጁ እየሣለ የሚያዘጋጃቸው የኪነት ውጤት ሽያጭ ገንዘብ ውስጥ፤ አቅሙቹውን የሚያውሰው፤ ባካባቢው የሚገኙትን ችግረኞች፤ ሕሙማቶችን፤ ሽማግሌዎችንና ባልቴቶች፤ እጓለ-ማውታንና የመሰሉትን በመርዳት ነበር። የዘመኑ ወጣት እንደመሆኑ ሁሉ፤ በመልበስ በሌላም መሽቀርቀር ሲችል፤ መምህር ጣሰው ግን ለአንዱ እንኳ ያሰው ርካሽና ግብዝ ባሕሪ ተገዥ ባለመሆኑ፤ መቼም የተበ ልብሱን እንኳ ሳይለውጥ፤ ደሞዙንም ሆነ የኪነት ቀማሙቱ ገቢውን፤ ለተቸገሩ ወገኖቹ መድቦ በመቸሩ፤ እጅግ ቀልላቹ አርነት ኖሯል። እስከ አውሮፓ ድረስ ሔዶ ከተማረው የኪነት ትምህርት ይልቅ፤ ከዚያው ከሀገሩ ሕዝብ የተሰማው ትምህርት ይበልጥ እንደሚጥመው አዘውትሮ ይናገር ነበር። ከአንደበቱ የሚወጡት ቃላት ሁሉ፤ የወሰላ ማር ያህል ማልም ከበሩቸው። የቁም ነገር ባለአንደበት የሆነውንም ያህል ጨዋታ አዋቂም ነበር።

መምህር ጣሰው የሕፃንነቱን ዓመታት በትምህርት ያሳለፈው፤ በቤተ-ክህነት አካባቢ በመሆኑም፤ ትምህርተ-ሃይማኖቱን በሚገባ ጠንቅቆ ያውቃል። ማወቅም ብቻ ሳይሆን ሠርቶ ለማሳየት። ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው በየቤተ-ክርስቲያናቱ የትምህርቱ መድረክ ላይ ሳይቀር በመገኘት፤ በዚያ ነደ እሳት አንደበቱ፤ ለምዕመናን ሲኤቲክስ፤ ባጠቃላይም ስለሥነ-ምግባራት መሠረተ ትምህርት ሲሰብከው፤ የወንጌሉን " በእንተ ብፁአን " ለንፅፅር ከዘመኑ የሶሻል ተጨባጭ እውነታ ጋር እያዛመደ በሚያስደምም ሲተረትረው ለሰማው ሰው፤ አዳማጩ ሳይቀር የራሱን ጆሮ አያምነውም ነበር። የበሰለች መንጦላዕቱን አጣፍቶ፤ በዚያ አደባባይ ላይ እየተንጠራራ፤ ሥነ ምግባርን በነቢብ ሲያወርደው፤ ለተመልካቹ ምድራዊ መሆኑን ያዘነጋ ነበር። የሰው ልጅ ለመሰሉ ፍጡር በርኅራኄ ስሜት መተሳሰቡና መራራቱ ሊጠቅመው እንጅ ሊጎዳው እንደማይችል በሎጂክ ጭምር ሲያረዳ ሳዳመጠው፤ እንደ ሶቅራጥስና ፕላቶ ያስተካክለው ነበር።

ልማዱ ሆኖበት፤ ዓለማችን ብዙ ብሩሃንና በጎ የሥነ-ምግባር ሰዎችን፤ ከነመፈጠራቸው ለሕዝብ ሳያሳውቅ፤ እንዳልነበሩ አድርጎ፤ ጓጭር እየቀጨ፤ በሞት-ሠረገላ ይሸኛቸዋል። ተደብቀው ተወልደው፤ ተደብቀው ኖረው፤ ተደብቀው የሚያልፉ ገርና ቅን ወገኖች ቁጥር ጥቂት አይደለም። በተለይም የሥነ-ምግባር ሰዎች ሁሉ፤ በተፈጥሮ ባሕርያቸውና ዝንባሌአቸው፤ ትሁትና ግሑስ በመሆናቸው፤ አብዛኛውን ጊዜ ባደባይ ጉልተው አይታወቁም። ራሳቸውን በራሳቸው ሲያስተዋውቁ ቀርቶ፤ ሌሎችም ሲያስተዋውቋቸው ደስ አይላቸውም። በእንፃሩ፤ ለስሙና ለዝናው የሚንሰፈሰፈው የማኅበረ-ሰቡ ክፍል፤ በሚፈጥረው ግርግር ውስጥ ስለሚዋጡ፤ እነዚህ የዋህን ሰዎችም ሆኑ፤ በጎ ምግባራቸው፤ በሰፊው ሕብረተ ዘንድ በሥርዓት ሳይታወቅ ይቀራል። በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎችም ቢሆኑ፤ የእንደዚህ ያሉ ሰዎች መታወቅ፤ የራሳቸውን የክብር ደረጃ የሚፃረሩባቸው እየመሰላቸው፤ እያስቀሩባቸውም፤ ከሕዝብም ጋር እንዲተዋወቁ አያደርጉም። የሞራል ሰዎች፤ በመሠረተ-ባሕርያቸው ፀረ-ሥልጣን በመሆናቸው፤ ይህ ዐይነቱ የመንግሥት ባለሥልጣናት ማስተዋወቅ፤ የሚጠበቅ አይደለም። ተራማጁና ንቁው የማኅበረ-ሰቡ ክፍል ግን፤ ሥነ ምግባራቸውን ብቻ አንሸቶ ይደርስና፤ ባሰው

እትሙ ሁሉ ያከብራቸዋል። ራሱ ንቁው ክፍል ግን ቁጥሩ ውሱን በመሆኑ፣ የሥነ ምግባር ሰዎችም መታወቅ መጠን፣ ያንኑ ያህል ውሱን ነው።

የእበላ ባይናና ያድር ባይ ቡድን በሚያወናብደው ዓለም ውስጥ፣ የግሑሳን ሐዋርያት፣ በሠፈውና በይፋ በሕዝብ ዘንድ አለመታወቅ፣ ብዙ አያስደንቅም። ዝናና መታወቅ በዓለማችን አንፃራዊ ይዘት ሲመዘን፣ ያወናባጆችና ያጭበርባሪዎች ንዋያዊ ውጤት ነውና።

" የዚህ ዓለም ክብር ከዚህ ዓለም እትም አይበልጥም " እንደሚባለው፣ ዓለማዊውን ክብር የሚያተርፉ ሁሉ፣ እትማቸውን ከዓለሙ እትም ጋር የሚያስተካክሉ ብቻ ናቸው። የግብሩ ዓለም ክብርና ዝና ደግሞ ንዋይና እፍትሮ ርዕስ ነው። ፍፁም ግብዝነት!!

የሁሉ ወንድም 'የነበረው፣ ወንድሜ ጣሰው በመምህርነት ጉራ አንድነት ተሰልፈን በቆየንበት ዓመታት ሁሉ፣ እጅግ ይጠላቸው የነበሩት እፍትሮ-ንዋይና እፍትሮ-ርእሰ እንደነበሩ፣ በሚገባ አውቅለታለሁ። ያንድን ሰው ባሕርይና ዝንባሌ በሥርዓት ሠትስቶ ለማወቅ የሚቻለው በየዕለቱ ከሚፈጽማቸው ድርጊቶችና ከሚያሳያቸው ግብሮቹ ስለሆነ፣ በዚህ ላይን ላይ ጣሰውን አሰቀምጦ መመዘን አስቸጋሪ አይደለም። በቤቱ ፣ በጐረቤቱ፣በቀበሌው፣ በማኅበረ-ሰቡና በትምህርት ቤቱ ውስጥ ይሠራቸው የነበሩትን ቁምነገሮች ሁሉ፣ በቅርቡ ሆኜ የተመለከትሁ ስለሆነ፣ ስለማንነቱ ለመመሥከር እትም የሚያንሰኝ አይደለሁም። የነጠረ የሞራል አቢጋዝ ነበረ። ሌላው ቀርቶ፣ መምህር ጣሰው፣ በማኅበረ-ሰቡ ተግባራዊ ባሕርች ውስጥ የተዋጠ ሰው ስለነበረ፣ ለግላዊ ቤቱና ትዳሩ የሚያስብና የሚጨነቅ አልነበረም። በቤቱ ውስጥ የሚገኙ ንብረታዊ ቁሳቁሶች እንኳ፣ የዓይነታቸው ሁኔታ የጣሰውን ሰብአዊ ባሕሪ ያሳያሉ። ከተራ ከርካሳ የእንጨት ወንበሮች በስተቀር የተሰየ ምቾታም መቀመጫና መቶኛ አልነበረውም። የሚያገኘው ደሞዝ መጠን እንኳ፣ ሌላው ቢቀር መናኛ ቢጤ ዳገመኛ እጅ ሰፋ ሲገዛለት የማይችል ሆኖ አይደለም። ወይም በዚያች ኩንትሽ የትኩል ቤት በኪራይ መኖሩ፣ ደሞዙና አየገለ በሚሸጣቸው ሥዕሎች አንጡራ ገንዘቡ መሰሰተኛ የራሱ ህኒጋባ መቀሰስ አቅቶት አይደለም። ጣሰው በተፈጥሮው እንደዚያ ያለ፣ ግለ-እሱነቱን ብቻ የሚያዝናና ነገር የሚዋጥለት ሰው አልነበረም። የግል ዓለንብ ረትነት ስሜት ደንታ የሚሰጠው ምሁር አልነበረም። የደስታ ምንጩ የነበረው፣ ዓለው ነገር ሁሉ የማኅበረ-ሰቡን ችግሮች መቋቋሙ ብቻ ነው። ጣሰው በርግጥ በቸርነት ረገድ ውሱን አልነበረም። አልባሌ ለብሶ፣ አልባሌ ተጫምቶ፣ አልባሌ በልቶ... ለሰው ሲል ተቸግሮ የኖረ ሰው ነበረ። በቅርብ የሚያውቁት ሁሉ፣ በሚታዩበት ሞራሉና ሥነ-ምግባሩ፣ በከፍተኛ ሰብዕናው በመንፈስ ሲኮሩበትና እጅግም ሲመኩበት፣ በትርጉው ጉሰቍልናና ገቅተኛነት ግን እጅግ ያዝኑለት ነበር። ያም ሆኖ ግን፣ ጣሰውም ከዚያ ጠንቀኛ ሞት አላመለጠም። እንደማንኛውም ተራ ሰው፣ ተራውን አልፏል። እጅግ የሚያስተቀው ግን ከነዚያ ሁሉ ምግባሮቹ ጋር፣ በወጣትነት እድሜው መቀጨቱ ነው። <u>የዘመናችን ጀርጃራ የፖለቲካ ሁኔታ ሰጣሰው፣ ያለዕድሜው መቀጨት፣ በርቱዕም ሆነ በኢርቱዕ ተጠያቂ ነው።</u>

እንደሩቅ ምሥራቅ ነባር ባሕል ቢታሰብ ኖሮ፣ የሞራል መምህሩ ጣሰው፣ የሞራል አርአያዊ ናሙና (ሞዴል) ተደርጎ በመጭው ትውልድ ሁሉ "ከጣሰው ተማር! እንደ ጣሰው ሁን" እየተባለ ይኖር ነበር። ጣሰው ግን ኢትዮጵያዊ ሆነና፣ እንደ ዘመኑ ብሔራዊ ሰብዕና ከነሞራሉ ተቀብሮ ቀረ።

ግን ምን ይሆናል፣ እንደ መምህር ጣሰው ያሉትን ሰዎች፣ ዓለምም ሆነ ሕዝቦቿ፣ እስከ መፈጠራቸው ሳያውቋቸው በድብቅ ተወልደው፣ በድብቅ ኖረው፣ በድብቅ ያልፋሉ። እንደዚያ ያሉትን ግሩማን ሰዎች፣ ዓለምም ሆነች ሕዝቦቿ በሚገባ ለማወቅና ለማስተዋወቅ ባሕሉም ሆነ ልማዱ የላቸውም። ስለ ሆነም ጣሰው፣ ከዚያ ችሎታውና ከዚያ ትሁት ሰብዕናው ጋር እንደተደበቀ ኖሮ እንደተደበቀ አልፏል። እንደሱ ያሉ ሰዎች ሁሉ፣ ለከሠረ እታው ማጣሪያ እንዲሆንለት ለሸቀጣ ሸቀጡ ማስታወቂያ እንደሚያሰራጨው የዲታ ሪከሰም የማይፈልጉና የማይመኙ በመሆናቸው፣ ራሳቸውን ሳያስተዋውቁ፣ የልብ ሙያቸውን በሥውርና በሰሆሳስ አከናውነው ይሞታሉ። መምህር ጣሰውን ከዚህ ለየት የሚያደርገው ቢኖር ምን ጊዜም ማንነቱን የማይረሱለት እጩ መምህራንን፣ የእርእያነቱ ቅርስ አርጎ ማለፉ ነው። በበኩሌም እንደ መምህር ጣሰው ቸርነት ያሉ ትንና የሥነ ምግባር ሐዋርያት፣ እፈር ሰለተጫኑባቸው ብቻ ተረስተው መቅረት እንደሌለባቸው ለማስገንዘብ፣ ይቺን መጣሐፍ መዘክሩ እንድትሆንለት አበረክቻለሁ።

( ጊኒ ብልጣሶር )





# እንተዋወቅ

ስሜ " የጠብታ ፍንጣቂ" * ይባላል። ያወጣልኝ የግል " አስገኘዬ " ነው። በይዘት ባህርዬ " ፈጠራ " መሆኔን ባውቅም፣ አስገኘዬን " ፈጣሪዬ " ልለው አልፈልግም። ስያሜዬ በይዘቴ አንጻር ሲታይ የ "ጥቅል " እንጅ የ " ተፀውኦ ስም " አይደለም። በዚህኛው ቀዳማይ እትሜ ብቻ፣ ከአስር በላይ የየራሳቸው የተፀውኦ ስም ያላቸው አጫጭር ታሪኮችን አቅፌ መያዜ፣ ለጥቅል ስምነቴ፣ ብቁ ማስረጃዬ ነው። አስገኘዬ በራሱ ልዩ ግላዊ አጠራረሩ፣ በእኔ ታቅፈው ያሉትን አጫጭር ታሪኮች ሁሉ፣ " ቆናፅል ድርሣናት " ይላቸዋል። " ቁራጭ ታሪኮች " ለማለት ነው። ይሁን እንጅ፣ "ቁራጭነታቸው " የመጠን እንጅ የሐሳብ እንዳይደለ አውቃለሁ። እንደ ሐሳብ ረዥምነታቸው የማይዳሰሱት ጉዳይ የለምና!!

ከሠፈው ባሕረ-ሥነ ጽሑፍ ውስጥ፣ በመጠነ-ሕሊና ተጨልፋ ከወጣችው ማየ-ድርሰት፣ አንዲቷ ጠብታ ተድበልብላ ስትወድቅ፣ የተፈጥትን ብዙኃን ፍንጣቂዎች አስመልክቶ፣ ይህን ስያሜ እንደሰጠኝ አስገኘዬ ይናገራል። " ፈጠራ " ብርቅ ላልሆነበት ጣሪ፣ እንዲህ መሰሉን ስያሜ ማውጣቱ፣ ውቅያኖሳዊው ሥነ-ጽሑፍ፣ ምን ያህል ዕመቅና ስፋት እንዳለው አገናዝቦ ይዘቱ ገና ያልተቆነጠረ ድልብ መሆኑን በትህትና ቃና

* ይህ እትም " የጠብታ ፍንጣቂ " ግግደ-እካል ቢሆንም፣ በተሰደ . " የዘንግር ደባ " የሚለውን ሥያሜ ይዞ እንዲወጣ የተደረገው፣ የሠፈሩት ያጫጭር ታሪኮች ይዘቶች፣ የወርሀ-ግእዶት ነፀብራቆች በመሆናቸው ነው።

ለመጠቆም በማሰብና፣ እግረ መንገዱንም ለአንባብያን ጉዳዩን ለማስረዳት ሲል፣ የዘየደው መላ ጭምር እንደሆነ እገም ታለሁ።

በዚህ ቀዳማይ እትሜ ውስጥ ታቅፈው የሚገኙትን አጫጭር ታሪኮች፣ አስገኛዬ ካዘጋጃቸው ዓመታት አልፈዋል። በየምክንያቱ በየማንዱታቸው ውስጥ ተዘርረው ከርመዋል። አብዛኛዎቹ ታሪኮች " ፈጠራዎች " ናቸው። ይሁን እንጅ፣ ሥርወ-ምንጫቸው ግን፣ ግዙፋዊው ጭብጥ ዓለም ነው። በተአምር ከሰማያት በርቀው የወረዱ አይደሉም። የማኅበረ ሰብ ፍጭት የወለዳቸው ግኝቶች ናቸው። እንዴውም የልደ ታቸው ወቅት፣ ከድኅረ የካቲት ኢትዮጵያ በነበሩት ዓመታት ውስጥ መሆኑን አስገኛዬ ገልጾ፣ በዚያው ዘመን አርጋጅ አንጋ ጅነት፣ ተጥደውና ፈልተው፣ ነፍረውና ተንተክትከው፣ በዚ ያው ዘመን ውስጥ በቅቷቸው የሠከኑ ጥዶሾች ሳይሆኑ፣ እስከ ዚህኛው ወቅት ድረስ ንፍረታቸው በመንተክተክ የቀጠለና፣ በስሎም ያልለየለት ሥሪታዊ ትንግርት እንደሆኑ ይጠቁማል። በርግጥም፣ የታሪኮቹ ባሕርያት የሚያተኑት ጠረን፣ ድኅረ የካቲት ድኅረ የካቲት ይሸታል። መዓዛቸውም የተጨነቁ ሰዎ ችን ዐይነት ያውዳል። እኔ ራሴ በግላዊ አባባሌ፣ እንድገል ፃቸው ቢፈቀድልኝና፣ ግራና ቀኝ ወይም ላይና ታች ሳልል፣ ፊት ለፊት በቀጥታ ስለአጠቃላይ ይዘቱ ብናገር፣ " ያለፉት አሥራ አራት ጥቁር ዓመታት፣ ኢትዮጵያዊው ማኅበረ-ሰብ የደረሰበት አሣርና መከራ፣ በደልና ፍዳ፣ ደባና ቍስቍልና፣ በመለስተኛ የጨረፍታ ጭላንጭል የሚንፀባረቅብኝ መስተዋ ትና፣ ይህም ጭንቀት የፈጠረው ብሶትና ስቆቃው፣ እሪታና





ዋይታ የሚያስተጋባው የሥቃያት ገደል ማሚቶ ነኝ " እላለሁ።

ማንኔቴን አካቴቼ ለመግለጽ፣ ከላይ የሠፈረውን አጭር መግለጫ ካቀረብኩ፣ በበኩሌ ይበቃኛል። ዝርዝሩን ሐተታ ግን፣ አዘጋጅዬ ራሱ፣ በሚከተለው ሁኔታ አቅርቦታልና፣ የእት ማዊ ይዘቴን ምንነት ማወቅ ለሚፈልጉ አንባቢዎች ሁሉ ሊረኩበት እንደሚችሉ ስለማምን፣ ልብ ብላችሁ እንድታነቡለት እያስታወስኩ፣ እኔ ከዚህ ምክሬ ጋር እሰናበታለሁ። ቺስስ!!

የጠብታ ፍንጣቂ ነኝ!

መልካም ንባብ እመኝላችኋለሁ።

ጥቅል አባባል ቢሆንም፣ የማንኛውም ሀገር ሕዝብ፣ ሥነ ጽሑፍ አለው። የኔ፣ የግሌ የሚለው ሥነ-ጽሑፍ። ይህም ሥነ-ጽሑፍ፣ የየሀገሩ ሕዝባዊ አስተሳሰብ ነፀብራቅ ነው። ብሶቱን፣ ተድላውን፣ ሐዘኑን፣ ዕሴቱን፣ ፍቅሩን፣ ጥላቻውን፣ መከራውን፣ ምኞቱን፣ ተስፋውን፣ ሥቃዩን.......... የሚገልጽበትና የሚያሳይበት ሕዝባዊ ሠነዱ ነው። ሲለው አክርሮ፣ ሲያሻውም አርግቦ ያቀርበዋል።

ሥነ- ጽሑፍ፣ የየኅብረተሰቡ አስተሳሰብ ኑሮና ሕይ ወት ነፀብራቅ ነው ሲባል የዘመን ክልል የለውም። ነበረ፣ አለ፣ ይኖራልም። ቅርፁና ዐይነቱ ቢለያይ የየዘመኑ ሕዝብ፣ የኢኮ ኖሚና ያስተሳሰብ እርከኖች የሚፈጥሩበት፣ የእድገት ትዕምርት ሆኖ ነው። ማኅበረ-ሰባዊ ነፀብራቅነቱ ግን፣ ሁለንተና ነው። በባሕርዩ ጠብ ስለሌለው፣ ሁሉንም፣ የትም፣ ምንጊዜም ሕይ ወትን በየመልኳ ቀርፆ ያቀርባል። ያቀራረብ ስልቶቹም የተለያዩ ሲሆኑ፣ በተለይም፣ ዐቢይ ልቦለድና ንዑስ ልቦለድ፣ ቅኔና

ግጥም፣ ቲአትርና ድራማ፣ ሒቲትና መጣጥፍ.... የተባሉ ልዩ ልዩ ዘርፋዊ ዐይነቶች አሉት ። እነዚህ ሁሉ የሥነ-ጽሑፍ ዐይነቶች፣ የየራሳቸው የሆነ ያቀራረብ ስልትና ቅርፅ አላቸው ። የየሥነ-ጽሑፉን ዓይነታዊ ቅርፅ የሚወልደው፣ እንደእናቱ የሆነው የየሥነ-ጽሑፉ ዐይነታዊ ይዘት ነው ። ቅርፅ በባሕርዩ፣ ከይዘት ይሠርፃልና ።

በተለይም ቅኔና ግጥም የተባሉት የሥነ-ጽሑፍ ዐይነቶች፣ ልዩ ጣዕምና ውበት፣ ጥልቀትና ምጥቀት፣ ስልታዊ ባሕርያትም ስላሏቸው፣ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትና ተቀባይነት አግኝተዋል ። አብዛኛውንም ጊዜ አቀራረባቸው በንፃሬ የተምሣሌት፣ በርቅቀት፣ በስልትና በሕገ-ቋንቋ የበለፀጉ በመሆናቸው፣ ሁኔታውያንን ሁሉ፣ እንደ ደራሲው ፍላጐትና እንደ አንባብያንም ዝንባሌ የመታዘዝና የመግለጽ ችሎታና ተሰጥዎ ይታይባቸዋል ። ሙሴ ደራስያንም፣ ተልእኮአዊ ሐሳባቸውን ለመግለጽ እነዚህን መንታ የሥነ-ጽሑፍ ዘርፎች አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው፣ በነዚህ ባሕርያቸው መንሥኤነት ነው ። በተለይም፣ ምዝብሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በመከራ አጣብቂኝ ውስጥ የኖረ፣ ነፃና ልቅ ኅብረተሰብ ባለመሆኑ፣ ቅኔና ግጥምን እንደጥልቅ ሐሳብ መግለጫና የልቡን ተናግሮ ሳይወነጀል ማምለጫ አድርጎ ሲጠቀምባቸው በመኖሩ፣ ስልታቸው ደርዝ ይዞ የጭንጫ ድንጋይ ያህል ጠንክረውና ደርጅተው ይገኛሉ ። ከዚህም የተነሳ፣ የሕዝባችን ግጥማዊና ቅኔያዊ ቅርስ፣ ከየትኛውም ሕዝብ ይልቅ የበለጸገና የዳበረ ይዘትና ቅርፅ አለው ማለት ይቻላል ።

ሕዝባዊ የመንፈስ ቅርስ የሆነው ኢትዮጵያዊ ቅኔ





ወይም ግጥም፣ ባብሕርዩ፣ ያሚያዝናና፣ የሚያስተምር፣ የሚያስጠነቅቅ፣ የሚተርክ፣ የሚያጋልጥ፣ የሚያፈላስፍ፣ የሚያስመጥቅ፣ የሚያሸብር፣ የሚያስቀልድ፣ የሚያፖላትክ ወዘተ.. ኃይል ስላለው፣ በብዙዎች ዘንደ መፈቀሩና መወደዱ የሚበዛበት አይሆንም ። ስለቅኔና ግጥም መዝግቤ ያሰፈርኩት ዝርዝር ሐሳብ በሚቀጥለው ባለ አሥር ግጥሞች እትሜ ላይ ( ዛር ነው በሽታዋ) እንዲያነቡልኝ እያስታወስኩ፣ በቅድሚያ ግብዣዬን አቀርባለሁ ።

ከቅኔና ከግጥም በስተጐን ደግሞ፣ ባጠቃላይ ይዘታቸውና ቅርፃቸው የተለዩ ዝርው ( ብትን) የሆኑ የድርሰት ዐይነቶች አሉ ። እነዚህ የሥነ-ጽሑፍ ዘርፎች የበኩላቸው ቅርጽና መዋቅር አላቸው ። በስልታቸው አንፃርም፣ ራሱን የቻለ መዋቅራዊ ይዘት አላቸው ። ከዝርው ድርሰቶች ውስጥ ዋናዎቹ " ዐቢይ ልቦለድ " (ረዥም ልቦለድ) እና " ንዑስ ልቦለድ " ( አጭር ልቦለድ ) የሚባሉት ናቸው ። ሁለቱም በይዞታቸው ብዛትና ስፋት መጠን ይለያዩ እንጅ፣ አጠቃላይ ውቅረታቸው፣ ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ ነው ። ሁለቱም የሚነድፏቸው የባለ ታሪክ ባሕርያት አሏቸው ። የባሕርያት ወኪሎች የሚሆኑቱ ተዋንያን ግን፣ በቍጥራቸው አይመሳሰሉም ። የዐቢይ ልቦለድ ተዋንያን ሲበዙ፣ የንዑስ ልቦለድ ግን አንድ ወይም የጥላ ያህል ውል ውል የሚሉ አጫፋሪ ይኖሩታል ። ሁለቱም፣ በማኅበረ-ሰብ የሚከናወኑትን የየዘመን እውነተኛ ድርጊቶች በፈጠራ መልክ ያቀርባሉ ። . . . በየወቅቱ የሚከናወኑትን የማኅበረ-ሰብ ድርጊቶች፣ በግለ-ሰብ ባሕርይ ላይ አስታከው ይተርካሉ ። ገጠመኝ፣ ችግር፣ መከራ፣ ግፍ፣

ድክመት፣ ድቀት......... ከሆነ፣ አሳዛኝ ገፁን አጕልተው ሲያቀርቡ በአንፃሩም፣ ገጠመኙ፣ ፍስሐ፣ ዕሴት፣ ፍቅር፣ ብሩህ ምኞት፣ ብሩህ ተስፋ፣ ብልፅግና... ከሆነ፣ አስደሳች ገፁን አብራርተው ይጽፋሉ። "ትራዠዲና ኰመዲ" የሚሏቸውም ከዚህ በመነሳት ነው። አብዛኞዎቹም መጻሕፍት እንደ አጠቃላይ መምሪያና ግብ አርገው የሚጠቀሙበት፣ አጓዳኝና ማዕከላዊ መርሖአቸው፣ የትሑት ሰብዕናን ምንነት ቀርፆ ለማሳየት ነው። ስለዚህም እንደትህትና፣ ቅንነት፣ ገርነት፣ ጨዋነት ያሉትን በጎ ባሕርያት፣ እንደባሕርይ መግለጫ ለፈጠሩት አቀንቃኝ ፈትለውና ሸምነው ያለብሱታል። እንደነሞራል፣ ኤቲክስ፣ በጎ ሥርዓት፣ ሉዓላዊ ልቦና፣ ራማዊ መንፈስ ያሉትን መድኃኒተ-መንፈስ ባቀንቃኙ ተዋናይ ላይ ይሥሉበታል፣ ይኩሉበታል። በዚህም ድርጊታቸው በማኅበረ-ሰብ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ግለ-ሰብ የነጠረ ሥነ-ምግባር ሊኖረው እንደሚገባ ያስተምራሉ። ወይም ደግሞ፣ የበደልንና የግፍን አፀያፊነት ለማጋለጥ፣ የአንቃኞቻቸውን ባሕርይ እንደጭራቅ አርገው ያቀርቡና፣ ኢሰብአዊ ግብሩን ያጋልጣሉ፣ ይኰንናሉ። በተመክሮ ደረጃም ትምህርት እንዲሆን፣ ባለዕኩይ ምግባርን ግለ-ሰባዊ ባሕርይ፣ እርቃነ-መንፈሱን ቅልጥጥ አርገው ያሳያሉ። ግለ-ሰቦችን እንደባሕርያቸው አቅርበው፣ በጐም ሆነ እኩይ ምግባራቸውን በማንፀባረቅ፣ የማኅበረ-ሰቡን የጐበጠ አስተሳሰብ ያርቃሉ። የሰውን ልጅ መማረክ የሚቻለው፣ በስሜቱ በኩል መሆኑ ቢታወቅም፣ ከስሜቱ ይልቅ ኅሊናውን ለማሸብረክ፣ የብዙዎች ልቦለድ መጻሕፍት ጥረት ነው።

ያቀራረብ ስልቱ፣ መተረክና ማተት የሆነውን፣ የዐቢይ ልቦለድ መጣፍ ጉዳይ ከዚሁ ላይ ልተውና፣ የዚህ እትም ወደ አቀፋቸው " አጫጭር ታሪኮች " ሐተታ ላቅና።

" ያጫጭር ታሪኮች " መሠረት፣ በአፍ የሚነገሩ ተረቶችና ታሪኮች ናቸው። አቀራረባቸው፣ አብዛኞዎቹ ግልጽና ፊት ለፊት ይሁን እንጅ፣ ምፀትና አሽሙር፣ ስቅሎሽና ምስሎሽ አለባቸው። አብዛኛውን ጊዜ በግለሰቦች ባሕርያት ተዋቅረውና ተነድፈው፣ ነጠላ ገጠመኝ ይተረክባቸዋል፣ ይንፀባረቅባቸዋል። አጭር ታሪክ በመሠረታዊ ይዘቱ፣ የገጠመኝ ሁኔታዎች መስተዋት ነው። በጽሑፋዊ አቀራረቡም ገላጭ ዘዬ ይበዛበታል። ስለዚህም ነው፣ መስተዋታዊ መሰኘቱ።

የገጠመኙ ሐሳባዊ እንብርት፣ መገለፅ ያለበት ቢሆንም ገላጭነቱ አይንዛዛም። እጥር ምጥን፣ ቁልጭ ቅልብጭ ብሎ የተከሸነ ነው። ምንም ጊዜም ቢሆን፣ የወጠነውን አቀንቃኝ ሐሳብ፣ በታሪኩ መጨረሻ ላይ፣ አሟልቶ ማካተት ይኖርበታል። መነሻ ውን በማሳመር የወጠነውን ያህል መድረሻውንም በመቅድመ ሐሳቡ መሠረት፣ መደምደም ግዴታው ነው።

አብዛኛውን ጊዜ፣ ያጭር ታሪክ ንድፋዊ ውቅረት፣ የነባር እውነታን ሐቃዊ ሁኔታ፣ የሚያስተርክ ነው። የሐሳብም ሆነ የቋንቋ ድግግሞሽን፣ ይህ ባሕርዩ ይከላከልለታል። ሐቃዊ እውነታውን ለመግለጽ፣ የቃላትና የሐሳብ ድግግሞሽ ሳይሆን፣ የተለያዩ አገላለጾች ይበልጥ ያገለግሉታል። ነባር ሁኔታን በመግለጽ ረገድም፣ ከድርቀት ይልቅ ልስላሴ ይስማማዋል። ማለትም፣ ነባሩን ሁኔታ እንዳለ ድርቅ አድርጐ ከማቅረብ ይልቅ " ይሆነኝ " ብሎ እንደሚስማማ ማቅረቡ ይመረጣል።

እንዲህም አቀናብሮ ለማቅረብ፣ የደራሲውን ልዩ ጥበብ ይጠይቃል። ስለዚህም ነው፣ ከደራሲ መምሪያዎች አንዱ መርሐ-ሙያ፣ " ደራሲ እንደ ካሜራኛ ፎቶ አንሺ ሳይሆን፣ እንደ እውቅ ሠዓሊ መሆን አለበት" በማለት ያቀረበው። በተለይም፣ ስለ አጭር ታሪክ አፃፃፍ ዘዴ የሚተርክ አንድ ጎድፌ ሐሳብ፣ " The importance of realism lies not in subject matter, but in the writer's attitude toward his material ………" ስለሚል፣ የሚጠቀስና እጅግ የሚተኰርበት ሐሳብ ነው። በዚህ እትም ውስጥ ሠፍረው የሚገኙት አሥር ድሁር ታሪኮች፣ ይህን መመሪያ ተከትለው የተነደፉ፣ የተዋቀሩና የተፃፉ በመሆናቸው፣ " ካሜራኛንና ብሩሽኛን " በመጠኑም ቢሆን፣ ሰፋ አድርጎ ማብራራት ጠቃሚ ይመስለኛል።

" ደራሲ ነው በርግጥ፣ ግብሩ እንደሰዓሊ፣
እንዳሻው የሚሥል፣ ጭብጥ ይዞ ደባሊ፣
ያ ጋዚጠኛ ግን፣ እንደ ፎቶ አንሺ ነው፣
የሚያየውን ብቻ እንዳለ ገልባጭ ሰው። "

በዚህ አንድ ሥነ-ጽሑፍ ጠቀስ የግጥሜ አርኬ ላይ፣ ሁለት ነገሮች ይታወሳሉ። የካሜራኛ ፎቶና፣ የሰዓሊ ሥዕል ናቸው። አንዱ ግዑዝ ወጥ ሲሆን ሌላው ደግሞ፣ ባለ ሕይወት የወለደው ነው። ፎቶግራፍ፣ ያንዳንድ ሰው ዐካላዊ ገጽታ ሲያነሳ፣ የፊት ላይ ጭረትን ሳይቀር እንዳለ ገልብጦ አንስቶ የሚመዘግብ ሲሆን፣ የእጅ ሥዕል ግን፣ ሠዓሊው እንደሚታየውና ኅሊናውም እንዳሰኘው፣ ወይም ምናቡም ሆነ ቀልቡ እንደመራው ወይም ደግሞ ሊሆን ይገባዋል ብሎ እንዳመነበት ነድፎ የሚስለው ነው። ሠዓሊው የነባራዊ አካሉን ጭብጥ ሳይለቅ፣ ከሚታየው አካላዊ ገጽታ አልፎ፣ ወደ ተሣሊው ልቦናና ኅሊና ጠልቆ በመግባት መንፈሱን ጭምር በሥዕሉ ላይ ያንፀባርቃል። አንዱ የነባሩን ሁኔታ በጥሬው እንዳለ ገልብጦ የሚያሳይ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ፣ ነባሩን ጥሬ ሁኔታ ደጀን በማድረግ ከዛ በላይ ደግሞ ደባል ሐሳብን በአላልነት በመቀነስ ወይም በመጨመር፣ የደራሲው ነፀብራቀ ኅሊና የሚታከልበት ነው። የጭብጡ ትክክለኛ ቅጅ ወይም የነባሩ ጥሬ ሁኔታ ነፀብራቅ፣ ፎቶግራፉ ሲሆን፣ እጅ ወለዱ ሥዕል ግን፣ ነባሩን ሁኔታ መነሻ በማድረግ፣ የሠዓሊው ግላዊ አስተያየት ጭምር የሚነደፍበት ነው። ስለዚህም ነው ጋዜጠኛና ደራሲ፣ እንደ ካሜራኛና እንደ ሠዓሊ ተመስለው የቀረቡት።

የካሜራን ድክመት፣ ሌላ ማስረጃ ልጥቀስ። ፎቶ የሰውን ልጅ ምናብ አያሳይም። በአስማት ኃይል መጫኛ እናቆማለን የሚሉ መተተኞች አጋጥመውኝ፣ ድርጊታቸውን በካሜራ ለማንሳት ሞክሬ ነበር። ባይገርማችሁ፣ በቆመው መጫኛ ላይ አስማተኛው ሳይቀር እንደጦጣ ፊጥጥ ብሎ ሲወጣ በዓይኔ አይቼም ነበር። ካሜራዬ ያነሳው ፎቶ ግን ሁለቱንም ሲሆን ሁለቱንም አልመዘገበም ነበር። ምሥጢሩ ምትሐተ-ዓይን ብቻ ነው ማለት ይሆናል።

በቀቀኑ ጋዜጠኛ በጆሮ የሰማውንና እንደእስስትም በአካላዊ ዓይኑ ያየውን ብቻ እንዳለ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት የሙያው ኤቲክ ያግረዋል። በአንፃሩ፣ ደራሲ ግን፣ ከነዚህም አልፎ፣ የራሱን ግላዊ አስተያየትና ፍልስፍና ያክል በታል። የተለያዩ ደራሲዎች እንደመኖራቸውም መጠን፣

የሚያክሉት አስተያየትም ይለያያል። አንዳንዱ የተነሳበትን ጭብጥ መሠረት አድርጎ፣ በሀገሩ ወይም በዓለም ማኅበረ-ሰቦች መካከል የሚንሸራሸሩትን ጊዜያዊ ዝንባሌዎች ያመላክታል፣ ይጠቁማል። አንዳንዱ በሰዎች መካከል ስለሚገኙ የባሕል፣ የፖሊቲካ፣ የእምነት አስተሳሰቦችና ግጭቶች አንስቶ፣ ድክመታቸውን ወይንም ተፅዕኖንታቸውን በተለያዩ መልኮች ያቀርባል። አንዳንዱ ደራሲ፣ በግላዊ አስተያየቱ ተማምኖ፣ ሌላውን ያወግዛል ወይም ያወድሳል። አንዳንዱ፣ ካንዱ ጠንካራ ጐራ ተዳብሎ ድጋፉን በመስጠት ያደንቃል፣ ያራግባል፣ ያጨበጭባል። አንዳንዱ ደግሞ፣ የራሱን " ይሆናኝ " ብሎ ያመነበትን ሐቅ ያራምዳል። ወይም ግላዊ ስሜት-ወለድ ዝንባሌውን ይሰብካል።

በነዚህ ደራስያን ልዩ ልዩ ያስተሳሰብ ልዩነቶች የተነሳ፣ የድርሰትም የአፃፃፍ ፈሊጦች የተለያዩ መልኮች እንዲኖራቸው ግድ ሆኖአል። ስለዚህም ልዩ ልዩ ያፃፃፍ ዘዴዎች ተፈጥረዋል። በምዕራባውያን አባባል " ሪአሊዝም፣ ኢምፕሬሽንዝም፣ ሹሪአሊዝም፣ አብሶልዩትዝም፣ አብስትራክሽንዝም፣ ክላሲዝም፣ ፊዩቸሪዝም፣ ራሺናሊዝም፣ አካዴሚሲዝም፣ ...... በመባል፣ በዘመናችን የሥነ-ጽሑፍና ባጠቃላይም፣ ለሥነ ኪነት ቤተ-ሰብ ፈርጥና ሐመልማል በመሆን፣ የተለያየ ውበት ፈንጣቂዎች ተደርገው ይገኛሉ። እንዲውም፣ እንደ ትምህርተ ቀመር፣ መርሐ-ነቢብ ሆነው፣ " ይህ ዐይነት የድርሰት ሐሳብ፣ በዚህ ዐይነት የድርሰት አፃፃፍ መቅረብ አለበት " እስከመባል ተደርሶ፣ እያንዳንዱ ያፃፃፍ ዘዬአዊ ዐይነቶች፣ ለተለያዩ የድርሰት ሐሳባዊ ይዘቶች ተመድበዋል። ዝርዝሩ ውስጥ ገብቼ





በዚህ ጉዳይ ላይ መንቦጫረቅ አልፈልግም እንጅ፣ የትኛው ዐይነት የድርሰት ሐሳባዊ ይዘት፣ በየትኛው ዐይነት ያፃፃፍ ዘዬ እንደተፃፈ፣ አንዳንድ መጻሕፍትን እየጠቀስኩ እንደምሳሌ በማቅረብ ባሳየሁ ነበር።

በዘመናችን፣ በድርሰት አቀራረባቸውና ባፃፃፍ ዘዴያቸውም እጅግ የተደነቁቱ ደራስያን፣ በተለይ በግለ-ሰቦች ቅንጭብ ታሪክ ላይ ተነስተው፣ የሕይወትንልዩ ልዩ ገጽታ በማስታከክ፣ የየማኅበረ-ሰቡን ደካማ ሆነ በጐ ጐን አጠቃለው ለማሳየት የሞከሩቱ ወገኖች ናቸው። በተለይም፣ ጭብጣቸውን ከመንታ አንፃር እያገናዘቡ፣ ነባሩን እውነታ፣ ሊሆን ከነበረበትና ከሚገባውም አንፃር እያስተያዩ፣ በልዩ ውሕደታዊ ሥምረት የሚያቀርቡ ደራስያን፣ ወደር የማይገኝላቸው የሥነ ጽሑፍ ጠቢባን ተብለዋል።

ለዚህም ዐይነቱ ድርሰታዊ አቀራረብ፣ " ያጭር ታሪክ " መዋቅር፣ ልክ እንደ ሠንጋ ፈረስ ገሥግሦ የሚያደርስ ነው። ተስማሚ ቃላትን፣ ዐረፍተ-ነገሮችን፣ ዘይቤዎችን መርጦ ብቻ በመጫን፣ ቾቾቾ እያሉ መኰልኰል ነው። ከፈለጉትና ከተመኙት ግብ ፈጥኖ ያደርሳል።

ከፍተኛ መጠበብ የሚያስፈልገው " ያጭር ታሪክ " አፃፃፍ፣ በተለይ አነጣጣሪ ቃላትን፣ አመርቂ ሐረጐችን፣ አርኪ ዐረፍተ ነገሮችን፣ መሳጭ ዘይቤዎችን፣ ማራኪ አንቀጾችን..... ማቀነባበር ይጠይቃል። በውሕደት፣ በሥምረት፣ በሥልጠት፣ መቆላለፍ ብቻ ሳይሆን ሠምና ፈትል ጭምር መሆን አለባቸው። ሥነ-ጽሑፋዊ መቅረዝና ፋና፣ ከዚያ ዓይነት የውህደት ሥራት ላይ ፍንትው ብሎ ይሠርፃል። ስለዚህም፣ በአጭር

ታሪክ ህልውና ላይ፣ ነገረ-ድሪቶ ቦታ የለውም። የፀረፍተ ሐሳቦቹ መጠነ ርዝመት መንዛዛት አይኖርበትም። ጉልህና ግልፅ፣ ቀላልና ልቅ መሆን አለባቸው። የሐሳቦችን ረድፋዊና ዘርፋዊ ቅደም ተከተል፣ ውሕደታዊ ፍፁምነትን ይጠይቃል። ቀዳማዊውን ከዳግማዊው ማዛነፍ የለብንም። ለዚህም አሠራር የሚረዳን፣ የታሪኩን ጭብጥ አስቀድሞ በሚገባ ማመንዠክና ማጣጣም ነው። ይህ ከሆነ የታሪኩን መዋቅር በሥርዓት ለመቀየስ ችግር አይፈጥርም። ጭብጡና መዋቅሩ ደርዝ ከያዘ፣ ድርሰቱ አጥንትና ሥጋን ተዋሕዶ፣ በአካል ገዘፈ ይኗል። አካላዊ ግዝፈትን ካገኘ በኋላ፣ ደመ-ነፍሱ፣ ከተዋቡ የቃላት፣ የሐረጎች፣ የዓረፍተ-ነገሮች፣ የዘይቤዎች፣ የአንቀጾች "ሴሎች" ላይ ይነግሣል። ከዚያ በኋላ፣ ግዑዝና ምውት የነበረው፣ የአጭር ታሪክ በደን፣ ሕይወት ዘርቶ፣ መንቀሳቀስ ጀመረ ማለት ነው።

በተለያዩ ሀገሮችና፣ በተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ዘመናት፣ ብቅ ጥልቅ ሲሉ የኖሩ የ "ቍንፅል ድርሣን " ደራስያን ብዙ ናቸው። ደራስያትም አሉበት። ያፃፃፍ ስልታቸውና የባሕርያት አወቃቀራቸው ከሞላ ጎደል ይመሳሰላል እንጅ፣ እንደሚኖሩበት ማንበረ-ሰብ ዐይነትና እንደባሕላቸውም ይዘት የታሪኩን ጭብጥ በሚመለከተው ነቍጥ ላይ ይለያያሉ። የሚያግራቸው አያሌ ገደቦች በመኖራቸው፣ ዋናው ወሣኝ፣ የሚኖሩበት ማኅበረ-ሰብ ዐይነት ነው። የጭብጡ ይዘትም የጽሑፉን ቅርጽ ይወስናል። የመልክዐ-ምድር የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ የኢኮኖሚ እርከን፣ የየታሪካቸው ቅርስ፣ ባሕላቸውና ልምዳቸው፣ ለታሪካቸው ጭብጥ ቅርፅ ያወጣለታል። በአቀራ





ረባቸው ረገድ፣ የአንድን ግለ-ሰብ፣ ወይም የአንድን ድረጊት ገጠመኝ ይዘው ይነሱና፣ ከአንድ ግባዊ ውጤት ላይ ደርሰው፣ ያልባሉ። ድርሰቱን ለመፃፍ ያነቃቃቸውና የገፋፋቸውን ገጠመኝ፣ እንደሁኔታው የመለያየቱን ያህል፣ ተፍፃሜተ ታሪኩም፣ እንደየደራሲው ያስተሳሰብ ዝንባሌ፣ ልዩነቱን ጠብቆ፣ በተለያየ መልእክታዊ ቀልፍ ይከረቸማል። በጀመረበት ፈር የማይጨርስ ታሪክ ግን፣ ያፃፃፉን ሕጋዊ ውል እንዳላከበረ ይቆጠራል። የደራስያኑ ጭብጥ ታሪክ፣ ግላዊ አስተሳሰባቸው፣ ያፃፃፍ ዘዴአቸው፣ መድረሻ ስልታቸው፣ ይለያይ እንጅ፣ ሁሉም ከአንዳች ገጠመኝ ላይ ተነስተው፣ ግብ ካለው አንድ መደምደሚያ የሚደርሱ በመሆናቸው፣ ይህ ነጥብ ያገናኛቸዋል።

ማንኛውም ደራሲ፣ የገዛ ፍጡሩ በሆነው ምናባዊ የድርሰት ሕይወት ውስጥ፣ የፈለገውን ያገናል፣ የጠላውን ይገድላል፣ የወደደውን ያድናል፣ ያፋታል፣ ይድራል። የታሪኩን ዋና ባሕርይ፣ ሲፈልገው ሠይጣን፣ ሳይፈልገው መልአክ አርጎ ያቀርበዋል። እንደዚያ በሐሰብ የመዝናናት ነፃነት ቢኖረውም ቅሉ፣ በተቻለው መጠን ታሪኩ የሚነገርበትን መካን፣ ጨርሶ መልቀቅ የለበትም። ፈረንጆቹ እኒህን ገደቦች " Local colour and Regional life " ይሏቸዋል። በአንድ ቦታና ወቅት ላይ በግብር የተፈፀሙ ድንቅና ታሪካዊ ድርጊቶችን፣ በፈጠራ መልክ ማቅረብ፣ ያጫጭር ታሪኮች ዐይነተኛ ባሕርይና ተግባር ነው ስለሚባል፣ ገጠመኙ የተከናወነበትን ቦታና ወቅት አገናዝቦ፣ አጠቃላይ ሁኔታውን ማንፀባረቅ ግዴታ ነው።

ወግ ለመጠረቅና፣ ተረብ ለመዘብዘብ ካልሆነ በስተቀር፣

ተፈላጊ መልእክትን ሁሉ በሚገባ ለማስተላለፍ፣ " አጭር ታሪክ " ሊያካትት እንደሚችል፣ ብዙዎች አምነውበታል። ለዚህም ይመስላል፣ የዘመናቸው የሩሲያ እውቅ ደራስያን የነበሩ፣ የዐቢይ ልቦለድ (ኖቬል) ፀሐፊዎች፣ እነ ጐጐል፣ ፑሽኪን፣ ቼኮቭ..... በአንድ ወቅት ትልቅ ልቦለድ መጻፋቸውን ትተው፣ በንዑስ ልቦለድ ድርሰት ላይ ተሽቀልቅሎው ተሰቀውበት ነበር። በርግጥም፣ እጥር ምጥን፣ ምጥን ብጥር፣ ቅምም ያለ ማንኛውም ነገር በሙሉ፣ ጣዕምና ለዛ እንዳለው ሁሉ፣ አጭር ልቦለድም ያዘለውን ንጥር ሐሳብ፣ ከተነሳበት ጭብጥ ወለም ዘለም ሳይል አለቅጥ ሳይንዛዛና ሳይበርዝ፣ በአንድ መጥ ሐሳብ እንደጀመረ፣ በአንድ ወጥ ሐሳብ የሚያስ ጨርስ በመሆኑ፣ ለድርሰት አፃፃፍ፣ ተመራጭነቱን አሌ የሚል አይኖርም።

ያጭር ታሪኮች መጠን የማያፈናፍን በመሆኑ፣ በሚጠቀምባቸው ቃላት ጥጥርነት የተነሣ፣ የቋንቋ ችሎታን በመጠኑም ቢሆን ያንዝር ይሆናል። ክርር፣ ጥብቅ፣ ጥርንቅ፣ ውጥርጥር... ያሉ ቃላት እንደ ሽቦ ቀጥነው በየአንጹ ውስጥ ይሠግሠጉ እንጅ፣ በጥቅማቸው አንፃር፣ የአንዲቱ ቃል ጉልበት ብቻ፣ ሐሳብን በመግለጥ ችሎታዋ፣ አሥር ጥርቅም ቃላትን ታስከነዳለች። ማለትም፣ የብዙ ቃላት ጋጋታ የማይገልጠውን ጥርንቅ ሐሳብ፣ አንዲቷ ብቻዋን ታመረቅነዋለች። ደራሲ ቼኮቭ፣ የፃፈባቸውን ያጭር ታሪክ ባሕርያትን ሕይወታዊ ቅፅበቶች፣ በተለዩ እምቦቃቅላ ቃላት ተጠቅሞ፣ ከተደበቁበት ፈልቅቆ አውጥቶአቸዋል። በተለይም ውስጣዊ የመንፈስ ትግል ያላቸውን የግለ-ሰቦች ሕይወት፣ በቃላት አግዝፎ፣





ረቂቅነታቸውን በማጋለጥ፣ ቅርፅና መልክ በመስጠት፣ ባጭር ታሪክ አማካይነት ሐሳባቸውን ለመግለጽ የሞከሩ ብዙ ደራስያን ተጠቅመውበታል።

" አጫጭር ታሪኮች " በቀልጣፋነታቸው አንፃር፣ በአንድ እፍታና ትንፋሽ፣ ተነበው የሚያልቁ መሆን አለባቸው። አቀራረባቸውም፣ ይሆንኝ ተብሎ መነሻና መድረሻ ( cause and effect ) ሐሳቦች የአሏቸው ስለሆኑ፣ ጋማቸውን ይዞ እንደፈረስ ለማጋለብ ያመቻሉ። ሌላው ጥቅማቸው ደግሞ፣ በዚህ አጣዳፊ በሆነው በዘመነ-ጥድፈት ወቅት፣ እጅግ ተጣዳፊ የሆነው የዘመናችን ሰው፣ በሚያዋክበው ኑሮው ውስጥ የጊዜ እጥረት ስላለበት የድርሰቶች ባጫጭር ሆኖ መቅረብ ደቂቃዎቹን ይቆጥቡለታል።

ይህን " ያጫጭር ታሪኮች " ጥቅም፣ በሚገባ የተረዳው፣ ፈረንጁ ጮሌ፣ በብዛት ይጠቀምባቸዋል። ስለዚህም " ያጭር ታሪክ " ሥነ-ጽሑፋዊ ቅርስነት በፈረንጆች ሥነ ጽሑፋዊ ይዘት ውስጥ እጅግ የደራና ራሱንም የቻለ ታሪክ አለው። በሥነ-ጽሑፋዊ ሠነድነቱም፣ የከበረ ቦታ አለው። በረዥምም ታሪኩ አማካይነትም፣ ለዘመናት ካሳየው ባሕርያቱ አንዱ፣ በእድገቱ ለውጥ ማሳየቱ ነው። በሕገ-ተፈጥሮ እንደምናየው ከሆነ፣ በነባርነት ያለና የነበረ ወደፊትም የሚኖር ራሱ " ለውጥ " ብቻ ስለሆነ፣ አጫጭር ታሪኮችም፣ በአቀነባበራቸው አንፃር፣ ይህንን የለውጥ ሕግ አክብረው ኖረዋል። " ለውጥ " ነባር ባሕርያቸው መሆኑን፣ በየዘመናቱ ባሳዩት እድገቶች አስመስክረዋል። በየምዕት ዓመታቱ፣ ባሕርየ ይዘታቸውንና ንድፋዊ ቅርፃቸውን ሲለዋውጡ ኖረዋል።

ይህን ለውጣዊ ኪደቱን ልናይበት የሚያስችሉን፣ በዚህ

ዓይነት አፃፃፍ፣ ሰፋ ያለ ልምድና ቅርስ ካላቸው ብዙ ሀገሮች ውስጥ ቻይና፣ ሩሲያ፤ ፈረንሳይ፣ ብሪታንያና አሜሪካ ይሆኙበታል። ከዋና ዋናዎቹም ደራስያን ውስጥ፣ እነ ሉሹን፣ ቱርጌኖቭ፣ ቼኮቭ፣ ጎጎል፣ ዶስቶቪስኪ፣ ፑሽኪን፣ ቶልቶይስ፣ ፖ፣ ኢርቪንግ፣ ሐርቴ፣ ሔሚንግዌይ፣ ሎወረንስ፣ ኮንራድ፣ ካፍካ፣ ቾሰር፣ ባካሲዮ፣ ሬኔ፣ ሲሲ፣ ማውፖንሳት........ ጥቂቶቹ ዕውቅ ደራስያን ይገኙበታል። ያጭር ታሪክን ሥነ-ጽሑፋዊ ጥቅምና፣ በሱም አማካይነት፣ የፈለጉትን ተልእኮ ባቋራች ለማቅረብ መቻሉን በማስመልከት፣ ሁሉም በየበኩላቸው ያነገቡት አንድ የጋራ መርሆ አላቸው። ይኸውም ....... “ The human spirit could best be cought at close range through short stories! ” የሚለው ነው። ይህን አርማዊ መርሆአቸውን አንግበው፣ ባደባባይ ያስተጋቡበትን ያጭር ታሪክ ሥነ-ጽሑፋዊ ጠቃሜታ፣ ምሳሌ እየሰጠሁ፣ በሰፊው ብዘረዝር እጅግ ደስ ባለኝ ነበር። በተለይም፣ በሐቃዊ እውነታ ጭብጥ ላይ የተመሠረተን ያጭር ታሪክ ድርሰት፣ ባገላለጹ ረገድ፣ ስሜት ወለድና ቀልብ ጠቀስ መግለጫ ( ኢምፕሬሽኒዝም) ይበልጥ ሊያመረቅነው እንደሚችልና፣ ሌሎቹንም ልዩ ልዩ ፅንሰ-ሐሳቦች በምን በምን ዓይነይ አገላለጽ ስልት መቅረብ እንዳለባቸው መጠቆም በተገባኝ ነበር። ግን ሐተታው ስለሚበዛ በዚህች ትንሽ እትም ለመተንተን አልሞከርም።

በሃገራችንም ደራስያን ዘንድ፣ በጣም የሠረገ አይሁን እንጅ፣ “ የአጭር ታሪኮችን ” ህልውና ለማስተዋወቅ ተሞክሯል። በተለይም በጥንታውያኑ መጻሕፍት “ በመዝሙረ ዳዊትና በአራቱ ወንጌሎች ” ውስጥ ሠፍነው የሚገኙት፣ የአን





ድምታ ማብራርያ አጫጭር ታሪኮች፣ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። የየቅኔ ትምህርት ቤቶቹ መቅድመ ዘረፋ ታሪክ ሌላው ነው።በየዘመኑ የተነሱ ኢትዮጵያውያን ደራስያንም የከተቧቸው አጫጭር ታሪኮች አሉ። ይህ ያለንበት ትውልድ የደረሳቸውን ብንጠቅስ፣ የእነ በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት “ የእንስሳት ኮሜዲያ ” እና፣ የነአቶ ህዲስ አለማየሁ “ ተረት ተረት የመሠረት ” ይገኙበታል። በተለይም፣ ከባለ “ ድግግሞሹና ድርብርቦሹ ” መድበለ አካል፣ ሦስት ያቶ ህዲስ ልበለድ መጻሕፍት ይልቅ፣ በበኩሌ ፣ በመልእክታቸው ባቀራረባቸው፣ በመዋቅራቸው፣ ባገላለጻቸው፣ በጭብጣዊ ይዞታቸው አንጻር ኩልልና ጥልል፣ ያለችውን ትንሽቱን “ ተረት ተረት የመሠረት ” መጽሐፋቸውን፣ በአንክሮ ጭምር አደንቃለሁ። መሰሏንም ደጋግመው ጽፈው ቢሆን ኖሮ፣ ምንኛ ደስ ባሰኘኝ ነበር። የሚያሳዝነው፣ እነዚያን መሳይ ድርሰቶች፣ የመጣፈጣቸውን ያህል፣ ብልጭ ብለው ድርግም ማለታቸው ነው። ላንባብያን ምን ያህል ፍሬያማና አርኪ እንደነበሩ፣ ያያቸው ሁሉ ይመሰክራል። በተለይም፣ ተረት መስለው በመቀየዳቸው፣ ተልእኮአቸው ሞራላዊና ትምህርታዊ በመሆኑ፣ በቀረቡበት ዘመንም ሆነ ዛሬ፣ሊሰጡ የቻሉትን ከፍተኛ ሞራላዊና ኤቲካዊ ተመክሮ ማንም ሰው መገመት ይችላል።

በቅርቡም እነአቶ መሥፍን ሀብተማርያም ( የቡና ቤት ወጎች ) እነአብዱ ንጉሤ ( ሙሽራው ) የጫጫሩአቸው ሐቲቶችና አጫጭር ልቦለዶች ሥነ ጽሑፋዊ ዋጋ የሚነፈጋቸው አይደሉም። ያገራችን የዘመኑ ደራስያን እነኛን መሰል መጻሕፍት በሰፊው ማምረት ያልቻሉበት ምክንያት ግን፣ በጭ

ራሽ አይገባኝም። በተለይም የሀራችን ጊዜያዊ ሁኔታ፣ እንደ ነዚያ ያሉትን ታሪኮች ለማምረት ምቹና ያዝመራውም ወቅት ነበር።

ዛሬ፣ ሀገራችን ከደራስያኗ ብዙ ትጠብቃለች። ጥርስ የለሹ ረሀብ ብቻ፣ ሚልዮን ልጆቿን በዓመት እድሜ ውስጥ ቆርጥሞና ሠልቅጦ የበላባት ሀገር በመሆኗ፣ ሌላው ቢቀር፣ ይኸ ትንግርት ብቻ የስንክሳር ቅጾች ያጽፋል። የየቀኑ የወታደሩ አፈሙዝና፣ የካድሬው ደባ፣ ኖቭሎች ያስደርሳል።

ዛሬ ኢትዮጵያ፣ በሶሻልና በኤኮኖሚ፣ በፖለቲካና በባሕሏ ዘርፋዊ አውታሮቿ ሁሉ ተወጥራ፣ እታች እመቅ ዘቅጣ፣ ዳዴ ይል የነበረው እግራዊ መልሕቋ አዘቅት ወርዶ ባሕረ-ወለል የረገጠበት ዘመን ነው። በውስጥም ሆነ በውጭ ያሉ ልጆቿ መዘበቻና መሣለቂያ የሆኑበት ልዩ ቀውጢ ጊዜ ነው። አንዳንድ ለ “ ብቃት ” የደረሱ ደራስያን ይህን ስቃያዊ ምንነቷን በተምሳሊት ለማሳየት ሞክረዋል። አንዳንዶቹ የዘመኑ ደራስያንማ… “ አንባቢ እኔ እንደምሠራው ሠርቶ ወደኔ ደረጃ መወጣጣት ይኖርበታል። እኔ እሱን ፍለጋ ወደ ታች ካዘቀዘቅሁና ከወረድሁ እድገት አይኖርም” እያሉ ከመመጻደቅ አልፈው ያሾፋሉ። “ ድንቄም እድገት እቴ!! ከወለል ላይ ይልቅ ጣራ ላይ መደነስ ያስደስተኛል እንዳለው፣ ዘፋኝ ” መኮኑ እኮ ነው። ፊው!!

በተምሳሊት ለማሳየት የሞከሩት እንደ “ አፅቋ የለመ ለመች ተክል አስመስለው ያቀረቧት ባለቅኔዎችም አሉ። - ችግኝ አፍልተው፣ ተክለው፣ ኰትኩተው፣ ፍግ አልብሰው፣ ወሃ አጠጥተው፣ ተቀፅላዋን ገርዘው፣ ካሳደጉ በኋላ፣ ተክሏ





ማቆጥቆጥ ስትጀምር፣ ቆፅል አውጥቶ፣ ቀንበጥ አብቅሎ፣ ቅጠል አለምልሞ፣ ቅርንጫፎች ዘንጥፎ፣ እንቡጥ አሞልምሎ፣ አብቦ፣ አኮርቶ፣ አጐምርቶ፣ ፍሬ አምርቶ…… የደረጃ በደረጃ እድገቱን ከሳበ በኋላ በስተመጨረሻው ገደማ በማዕበላዊ ዶፍ አዘል ዝናብ፣ ከነጉድጓዱና ከነመብረቁ ጋር ወርዶ፣ አፈር በማስጋጥ፣ ልምላሜ-ተክሉን አራቍቶ መለመላ ግንዱን ብቻ መቅረቱን ጠቁሞ በማሳየት፣ ቅኔውን ያልባል። የገጣሚው ደራሲ ሐሳብ ጽሑፋዊ ተልእኮው እዚህ ላይ ይቁም እንጅ፣ ጠልቆና መጥቆ እንዲነበብለት፣ ካንባብያን ሁሉ ይጠብቃል። አንባብያን ግን የባለቅኔውን ተከላዊ አምሳል ተልእኮ፣ ባራዛሚ መነጥር ሳያዩ ለተራው ተክል ልምላሜና ድርቀት ብቻ ለጥ ፈው ትንሽም ፈቀቅ ሳይሉ ይተውታል። ይህ ጕዳይ በደራ ሲው አንፃር ሲታይ፣ የወታደሩ አፈሙዝ የፈጠረበት ፍራቻ ያስጠበበው ዘዬ ሲሆን፣ ባንባቢው በኩል ግን የራሱንና የሀገሩን ሁኔታ ሳያዛምድበት፣ እንዴው እንዳለ በደፈናው፣ ተክሉን ብቻ አርጐ መቀበሉ፣ የጊዜያችንን ኢትዮጵያ ሁኔታ ረስቶታል ወይም ከምሬቱ ብዛት ሊያስታውሰው አይፈልግም ማለት ነው።

የቻይናም ደራስያን በዚሁ ዘዴ ተጠቅመዋል። በምሥ ራቃዊቷ ቻይና፣ አንዲት ታንኪረኛ ወፍ አለች። “ ቺን ዌይ-ኑዋ ” ብለው የሀገሬው ሰዎች ይጠሯታል። የመልኳ ብሩህነት የወተትን ንጣት ያስንቃል። ፍፁም በረዶ ትመስላለች። ይቺ ወፍ፣ በየዕለቱ፣ ዝምበር ከሰረቀችበት ማለዳ አንስቶ እስከ እምታርብበት ምሽት ድረስ፣ በምትኖርበት አካባቢ ካለ አንድ ሰፊ ባሕር ውስጥ፣ ያገኘችውን ጭራሮና ጠጠር እያጋዘች

ስትጨምር ትውላለች። ያገሬው ከበረኞች እንደሚሉት ከሆነ፣ ዓላማዋ ባሕሩን በምታግዘው ነገር ለመሙላት ነው። ምክንያቱንም ሲዘረዝሩ፣ " ወፊቱ ከዘመናት በፊት፣ ከባሕሩ ዳር የሚኖር ያንድ ቤተሰብ ልጅ አገረድ ነበረች። ወላጆቿ ሳያዩአት ከባህሩ ውስጥ ገብታ ስትዋኝ በመሞቷ፣ ነፍሷ ወደ ወፍነት ተለውጣለች" ብለው ይተርካሉ። " እስከዛሬ ውሃውን ለመሙላት የምታደርገው ጥረት፣ በቀል ለመወጣት፣ ወይም ባሕሩ በየቈሳቀሱ ተሞልቶ ሲጠፋ፣ ጥንት የሞተችዋን ልጅ አገረድ፣ የገዛ ነፍሷን፣ ከንሕይወቷ የምታገኝ እየመሰላት ነው " ይላሉ። ምሣሌያዊ ታሪክ ሊወጣው የሚችል ግሩም "ገድል" ነው። በንጽጽርም መዋቅራዊ አቀራረብ ታሪኩን ከሀገር፣ ከታጋይ፣ ከትግብርት.... ማዛመድና ማቅረብ የሚያስችል ታሪክ ነው።

እንዲህ መሰሉ ታሪክ፣ ለጊዜያችን አንባብያን፣ ለንፅሮ ቢቀርብ፣ ምን ተብሎ እንደሚተረጐም፣ አስቀድሞ መገመት ይቻላል። ትዕምርት ( ሲምቦሊዝም ) በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው። እንደ አንዳንዶቹ ከያንያን "አብስትራክት" አይደለም። ረቂቅንና ጥልቅን ሐሳብ፣ ይበልጥ ግልጽና ጒልህ አድርጐ ለማቅረብ የሚረዳ ደጀን ነው።

ደራስያን እንደየፈሊጣቸው፣ በተለያየ አቀራረብና፣ ለተለያየ አቅጣጫ ይጽፋሉ። ከሞላ ጐደል፣ ያቀራረባቸውን ዐይነት፣ በ " አጭር ታሪክ " አፃፃፍ፣ አስመልክቼ ጠቅሻለሁ። የሚጽፉበት አቅጣጫዊ ዒላማ እንደየችሎታቸው ይለያይ እንጅ ዋናዎቹ ግን ሁለት ናቸው።

አንደኛው ያንባብያን ስሜት ምርኰ አስገብቶ፣ ተልእኮአቸውን በቀላሉ መንገድ እንዲቀበሉ ለማድረግ፣ በቀጥታ





ለልቦና አነጣጥረው የሚተኩሱት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ኀሊናን በምርምር ወጥሮ በማስተዋል እንዲቀበለው፣ በቀጥታ ወደ አእምሮ የሚለጋው ነው። ግልፅ ሆኖ አይታይም እንጅ፣ የሚጽፉ ደራስያን ሁሉ፣ እነዚህን ኢላማዎች ይዘው ነው። እነዚህን የደራስያን ሥውር ኢላማዎች በሚመለከት " ትርጁማን ብትሆኑኝ " በሚል አንድ ግጥሜ ውስጥ የሚከተለው አርኬ ሠፍሯል።

" ለይተህ አስረዳኝ፣ ልብን ከኅሊና፣
ሁለቱን ለመለየት አቅቶኛልና!!
አንዳንዶ እንላለን፣ ጠቅሰን አንድ ደራሲ፣
ልንተቸው አስበን፣ በዓይነ ሒያሲ!
'አገሌኮ ይጽፋል፣ ለሰዎች ልቦና፣
ያ ደራሲ ደግሞ፣ ለዚያ ለኅሊና።'
ሲሉ እሰማለሁ፣ ልቦናን ያን ስሜት፣
ሌሎችም ሲያደርጉት፣ ኀሊናን ምክንያት!!
የሚያፈው ሐቅ ግን፣ አንድ እስከ ሆነ ድረስ
ለምን ይሆን ከቶ፣ የሚሰጡት ልባስ?
አንዱን ሐቅ ለሥጋ፣ ሌላውን ለመንፈስ!
አፍጥጦ ችግሩ፣ እየታየ ሲያምስ!!... "

የዘመናችን ደራስያን፣ በተምሳሊትም ሆነ በገድል ሽፋን ያቅርቡ፣ ወይም እንዳሻቸው ለልቦናም ሆነ ለኀሊና አልመው ይድረሱ፣ ከመቸውም ዘመን ይልቅ፣ ስላለንበት አሠርታት ወቅት፣ መጻሕፍት መጻፍ የግዴታ ኃላፊነት አለባቸው። የዘመናችንን ጒስቁልና ምዝበር ኢትዮጵያ፣ በሆነው መልክ ሥለው ማቅረብ፣ ከየትኞቹም ባለሙያዎች ይልቅ ከደራስያን

ይጠበቃል። ለልቦናም ይጻፉት ወይም ለኅሊና፣ የኢትዮጵያውያን መራራ ብሶት፣ በሐቅነቱ አንድ ዓይነት ስለሆነ፣ ደባን፣ በደልን፣ ግፍን፣ ሥቃይን፣ ቸነፈርን፣ ረሀብን. ............ ማወቅ የማይችል ልቦናም ሆነ ኅሊና ይኖራል ብሎ የሚገምት አይኖርምና! ብቻ ይጻፍ!!

አንድ ጥንታዊ የግዕዝ ብራና መጣፍ ( የመዝሙረ ዳዊት አንድምታ ) ውስጥ፣ ያነበብኩት፣ አንድ ከባድ ብሒል፣ የሀገሬን ሕዝብ ሥቃይ ባስታውስኩ ቍጥር ዛሬም ትዝ ይለኛል። እንዲህ ይላል።

" ኢይመውት ዘእንበለ ዘአሐዩ " የሚል ነው። ቀጥተኛ ትርጉሙ ሕያው ሆኖ ለተፈጠረ ሁሉ የሚጠቀስ ነው። ከባድ ሐሳብ ያዘለ ኃይለ ቃል ነው። አጭር ትርጉሙ ለመኖር የተፈጠረ ፍጡር ሳይኖር እንዴት ይሞታል? ( ሳልኖር አልሞትም እንደማለት )

ዛሬ ኢትዮጵያ፣ የሚሠቃዩ ሕዝቦች የሚታዩባት፣ የትራጀዲያ " መድረክ ናት። መዓዛዋ ሁሉ በሁለንተናው፣ መከራ መከራ ሸትቷል። የውጭና የውስጥ አድኃርያን በፈጠሩት የም ሥጢር ደባ፣ የዋሃኑ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ሲጠበሱ ኖረዋል። በአንዲቷ ምድራችን ላይ፣ በተፈጥሮ ያገኘችው የመልክዐ-ምድር ድርሻ፣ በብዙ አንፃር ማራኪ በመሆኑ፣ ልምላሜዋም ሆነ ከበሐውርት ወደ በሐውርት ድልድይነቷ፣ የኃያላን መንግሥታትን ቀልብ አሳብዶ መራኰቻ አርገዋታል። በተለይም ለአውሮፓውያን የደም ስር የሆነው ቤንዚን የሚመነጭበት አካባቢ በመሆኑና፣ እንዲሁም ውሃ ለውሃ ተንሳፎ ከታላላቅ ውቅያኖሶች መዳረሻ አቋራጭ ኰዳና





በመሆኗ፣ የጥንት ኰሎኒያሊስቶችንና የዘመናይ ኢምፔሪያሊስቶችን የምኞት ልባዊ ትርታ እንዳከነፈው አለ። በዚህ የኃያላን ፍላጐት አጣብቂኝ ውስጥ ላካባቢው ታናናሽ መንግሥታት፣ በሰላም የመኖር ጉዳይ የማይታሰብ መሆኑ ቢታወቅም፣ እንደወረርሽኝ የኢንፍሎዌንዛ በሽታ፣ ውስጥ ውስጡን እንዳማቀቃቸው ናቸው።

በተለይም ኢትዮጵያ፣ ባለፉት ዘመናት በ " አትንኩኝ ባይ " ታሪኳ የታወቀች ገናና ሀገር በመሆኗ፣ በርቱዕ ትግል ያልቻሏትን ያህል፣ በኢርቱዕ ሠርገው ገብተው፣ ለጥንታዊ ሽንፈታቸው በቀል ለመወጣት፣ የማይሸርቡት ሤራ የለም። ዛሬም አንዳንድ የባሕር ማዶ ከበርቴዎችም ይህን የተንኰል ሤራ ለማፋፋም በሚጫረው እሳት ላይ ሁሉ ቤንዚን እንደረጩ ናቸው። ግን ነድዳ እንድትጠፋ የሞከሩት ሁሉ አልተቋጨላቸውም። በአንጻሩም በበጎ የሚያስባትን ሁሉ እያቀፈች እስከዛሬ አለች። ለዘመናት በነጻነት ለመኖር ያስቻላት በዓለም የታወቀው የልጆቿ ጀግንነት ብቻ ሳይሆን፣ ሕዝቦቿ ያላቸው ፍጹም የሰብአዊነት ስሜት አውታራዊ ምግባራቸው ጭምር ነው። የጥንት ኢትዮጵያውያን ትህትና፣ ርኅራኄ፣ ትዕግሥት፣ ባጠቃላይም ሞራላዊ ሥነ-ምግባር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ኢትዮጵያውያን ለቆየ ንጥር የመንፈስ ቅርስ ባለቤት በመሆናቸው ሀገራቸውን እንደ ነጻ የሰዎች መናኸርያ ቆጥረው፣ ሌላው ቀርቶ ለአዝሙድ ንግድ፣ ለሐር ሸቀጣ፣ ለዝሆን ጥርስ ዝሆ፣ ለአራዊትና ለሌጦ ንግድ፣..... ካለም ዳርቻ ጭምር ይገባ ይወጣ የነበረውን ዓለም አቀፍ ነጋዴ በየዘመኑ በክብር ተቀብለው ሲያስተናግዱ መኖራቸው የዚሁ የነጠረ ሞራላቸው

ልዕልና ነጸብራቅ ነው። የዘመነ አክሱምና የዘመነ አዱሊስ ታሪክ ምስክር ነው። በመስተንግዶ ወደ ሀገራቸው የሚገሰግሰው ፍጡር፣ ሰው እስከሆን ድረስ፣ በዝቅተኛ ደረጃ ስለማያዩትም እንደ ነጻ ፍጡርነቱ ተጋብተውታል ተዋልደውታልም። በዚህም ነጻ ሰብአዊ ድርጊቱ " አልሐበሽ " ( ሐበሽ ) ......... " ድብልቅ፣ ብርዝ፣ ዘረ-ብዙኃን " የሚል የተዋረድ ስያሜ ቢሰጡት አያስደንቀውም። እንዲያውም በተዘምዶውም ሆነ በወዳጅነቱ ከሩቅ ምድር ሰዎች ይልቅ ጐረቤቶቹ እንደሚቀርቡት ስለሚያምን ምን ጊዜም የበጎ ፍቃድ በሩን በርግዶ ከፍቶላቸው ኖሯል። ይህ የሰላምና የበጎ ፈቃድ በር የተዘጋባቸው ወቅቶች ቢኖሩ የኢትዮጵያውያንን ነጻ ሕልውና ለመፈታተን " በደረታ ቸው መስቀል፣ በጉያቸው ሾተል፣ ወይም በደረታቸው ጨረቃ፣ በጀርባቸው ጨፌቃ፣ ወይም በደረታቸው ኮከብ በጭናቸው ክላሽኒኮፍ " ይዘው እንደዛር ውላጅ በመንታ አካል ሰርጎ ለመግባት በሞከሩት ላይ ብቻ ነበር። " በቅንነት የመጡትን እንግዶች ሁሉ ኢትዮጵያውያን በክብር ተቀብለው ሙሉ ነጻነት በመስጠት፣ ተልእኮአቸውን እንደፈለጉ ተዘዋው ረው እንዲያሰራጩ መፍቀዳቸውን ለማዘከር፣ የክርስቶስ ሐዋ ርያ የነበረው የሕንደኬው ቶማስ ሌላው ጥሩ ማስረጃ ነው። በአንጻሩ የሮሙ ቫቲካናዊው ሐዋርያ አባ ማስያስ የሠራውን አሻጥር ሁላችንም እናውቃለን። በእንግድነት ገብተው፣ ሴራ የዶለቱትን ሁሉ እዚህ ላይ መዘርዘር አያስፈልግም።

በመሠረቱ እኔ የታሪክ ምሁር አይደለሁም። በሌላ ጥናቴ ስምሪት ወቅት ግን፣ ግላዊ ትምህርቴ እያጣቀሰ ሲነዳኝ፣





ለራሴ ያህል የሚበቃ የታሪክ መጻሕፍት አንብቤአለሁ። ደግሞም በሀገራችን ትምህርታዊ አድኅሮት የተነሳ ከተጻፉት መጻሕፍተ ታሪክ ይልቅ ያልተመዘገቡቱ አፈታሪኮች ይበልጥ ጥራትም ብዛትም ስላላቸው፣ ክብደታቸው የሚናቅ ባለመሆኑ፣ ያጋጠሙኝን አበው ሁሉ አበክሬ ከመጠየቅ የሰነፍኩ ባለመሆኔ፣ ላጣቃሽና ለማገናዘቢያ ያህል የታሪክ ሰነዶች አሉኝ።

ማሳያ ቢያስፈልግ አንዳንድ ድንቃዊ የታሪክ ቅጽበት ድርጊቶችን ልጠቃቅስ። ለምን እንደጠሉት ባላውቅም የኢትዮጵያ ካህናት አጼ ቴዎድሮስን አይወዷቸውም ነበር። እሳቸውም ቢሆኑ፣ " ራሱን ታጣቂ፣ ወገቡን ሰባቂ..... " እያሉ ካህናቱን ያርበደብዱ ነበር። በዘመኑም ከካህናት ጋር መናቆር ቀላል አልነበረም። አምላካቸውን ወንጅለው የሰቀሉ ኃያላን ሴረኞች ካህናት ናቸው። ቴዎድሮስ ግን አልፈራቸውም። የነሱ ጠብ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ሊፈጥር የሚችለው ጠባሳ ምን ሊሆን እንደሚችል ማወቁ ነቢይነት ይጠይቃል። ኃይልና ሥልጣን የሕዝብ መሆኑ በማይታወቅበት በዛ የግለ ሰቦች ገናናነት ዘመን፣ ትግላቸው የሚፈጥረውን ብሔራዊ ጠንቅ መገመት ያስቸግር ነበር። የቴዎድሮስ ቁራጥነትና አይምሬነት እየለየለት መምጣቱን ደረጃ በደረጃ የተገነዘቡ ካህናት፣ የበኩላቸውን እርምጃ ለመውሰድ አልዘገዩም።

" የቤተ ካህናትን ደወል ፣ ቃጭል፣ ጽዋ፣ ጸናጽል፣ መስቀል፣ ርእሰ-መቋሚያ፣ ጽንሐ..... አቅልጣችሁ መድፍ ሥሩልኝ " ብሎ ያወጀ ጊዜ ነበር በሕይወቱ ላይ የፈረዱት። በየዓውደ ዓመቱ ዕለትና በታላላቅ በዓላት ቀን፣ ይቆርብ የነበረውን ቴዎድሮስ፣ በመሥዋእት ውስጥ መርዝ አድርገው

ሲገድሉት ወሰኑ። ወዲያውም መርዘኛ የእባብ ጭንቅላት በሚቆርብበት ዕለት አዘጋጅተው፣ ቅዳሴውን ሲያጣድፉ፣ ይህን ተንኰል የተረዳ አፍቃሬ ቴዎድሮስ የነበረ አንድ ንፍቅ ቄስ፣ የመጀመርያውን ቁርባን እንዳይቀበል በምሥጢር ይነግረዋል። በስተመጨረሻም ዕርገት ወርደው፣ ሲያቆርቡት ሲሉ፣ አጅሬ ቴዎድሮስ “ ጥዒሞ አጥዓም ” ይልብሃልና የመጀመሪያው ላንተ ይልና ዓይኑን አፍጥጦ ገባሬ ሠናዩን ካህን ያዘዋል። ካሁኑም ወደ ቴዎድሮስ አፍ ዘርግቶ የነበረውን መሥዋእት በራሱ አፍ ተቀብሎ ብዙም ሳይሠቃይ ተንፈራፍሮ ይሞታል። ቴዎድሮስም ከዛው መሥዋእት ላይ፣ በንፍቅ ካሁኑ ቄስ አማካ ይነት ተቀብሎ ከቆረበ በሁኋላ ወደ ቤተ-መንግሥቱ ይመለሳል። ከዛ ወዲያ ለካህናት ሁሉ፣ ቴዎድሮስ ነብር እንጅ ሰው አልሆን ላቸውም። በተቆጣ ሽካራ ጥፍሩ እያንጠለጠለ ምድረ ካህናትን በየገደሉ እያምዘገዘገ አሰናብቷል። ግን ያኔ የካህናቱ ሤራ ውጤታማ ቢሆን ኖሮ ቴዎድሮስ ብሲቱ ኢትዮጵያ ምን ይወጣት ነበር? ” ፕሉቶክራሲ ወይስ ቲኦክራሲ? ወይስ ዲሞክራሲ? ..... መተንተን ለሚወደው ለዚህኛው ትውልድ የቀረበ ጥያቄ ይሆናል።

( “ በጥቁር ብሌን ትይታ ” ከተባለ መጣፌ የተጨለፈ )

ሌላ አንድ ኮሚክ የታሪክ ድርጊት ልጨምር። የ “ አበሻ ሀገር ጦርነቶች ” ከሚለው ሰነዴ ውስጥ የምቀነጭበው ነው። በዘመናት ባንደኛው ወቅት፣ በጐረቤት ገናና አምባዎች መካከል ከተደረገ ጦርነት የተገኘ፣ የጦር ታክቲክ ዜና ነው። የአንደኛው አምባ መሪ እጅግ ሲበዛ ዘዴኛና ብልህ ነበር። በቂ መሣርያዎች የሌለው በመሆኑ ይመስላል፣ ብልህነቱን የፈጠ





ረለት። ጣውንቱ የሌላው ባላምባ መሪ ግን፣ እያሌ ሠራዊትና ብዙ ልዩ ልዩ የጦር መሣርያዎች ያለው ነበር። ለመጋጠም ቦታና ቀን ከወሰኑ በኋላ፣ ብልሁ የጦር መሪ አሥር ባለጋሞች ወታደሮቹን ይዞ አስቀድሞ ከተባለው የጦር ሜዳ በመድረስ፣ ረባዳ ቦታ መርጦ ይመሽጋል። ባለብዙው ሠራዊትም እንደ ሚያሸንፍ ተማምኖ፣ ተዝናንቶ እያቅራራና እየፎከረ ይመጣል። እነዚያ ባለአስር ነፍጠኛ የሆኑቱ የብልሁ መሪ ሠራዊት አባላት ከጠመንጃቸው ሌላ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ቀፎ ንብና የንብ መከላከያ የሽቦ ወንፊት አጥልቀው ተዘጋጅተዋል። በተባለው ሰዓት ባለብዙ ሠራዊት ጦር እየተዝናና ሜዳማ ከሆነው የጦር ሜዳ ላይ እንደደረሰ፣ ያ ዘዴኛ የጦር መሪ፣ መልእክተኛ ልኮ “ እንታረቅ ያንተን ጦር ትጥቅና የሠራዊቱንም ብዛት ገና ከሩቁ ሳይ ልቤም ጉልበቴም ተማርኳል። ገናናነትህንም አክብሬ ለመቀበሌና እኔም በገዛ ድፍረቴ ለመቅለሌ ገጸ በረከት ይዠ መጥቻለሁና ተቀበለኝ ” ብሎ ይልካል።

ያም ባለብዙ ሠራዊት የጦር መሪ እውነት መስሎት “ መሸነፉን አምኖ ይገብርልኝ እንጂ ከሰው ደም ማፍሰሱማ እኔ ምን ቆሌ አለኝ ” ብሎ ይቀበለዋል። ጦርነቱም መሰረዙን ለሠ ራዊቱ ይነግርና፣ ምርኮውን እንዲቀበሉ ያለ መሣርያ እንዲ ሰበሰቡ ያዛል። ያ ዘዴኛ ባለ አሥር ነፍጠኛ ጋሜ ጦር መሪ፣ ካንገት በላይ ያለ የሠራዊቱን ፊት እንደ አባ ገሪማ አጽፍ አከናንቦ ከተፍ ይልና “ ገጸ በረከቴ ይኸውልህ! ” ይልና እዛ ባዶ እጁን አውላላ ሜዳ ላይ ለተሰጣ ሠራዊት ያሥሮቹን ቀፎዎች የተቆጣ ንብ ይዘረግፍለትና እነዚያን ባለ አሥር ነፍጠኛ ጋሞቹን “በሉ በነፍጣችሁ እመሩኝ” ይላል። ከዛ ወዲያማ ምን

ምን ይጠየቃል። ያ የንብ ሠራዊት፣ እያባረረ የሚጠዘጥዘውን መከላከያ-ቢስ ሠራዊት በጥይቱ ጭምር አንድነት ጠዝጥዞ ጨረሰው። በስተኋላም ከንቡና ከጥይቱ የተረፈውን ሠራዊት ከነጦር መሪው ማርኮ፣ አምባዎቹን ሁሉ ባንድነት የግሉ አድርጎ ለመምራት በቃ።..............."

ይህንን ከመሰለ ያልተጻፈ ታሪኩ፣ የዘመኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ መማር ይችላል። ሌላው ቢቀር፣ ጠላትን ለመቋቋም ለሚደረገው ግብግብ፣ " የጥራት " እንጂ " የብዛት " ጉዳይ ወሳኝ እንዳይደለ፣ ላለንበት የቀውጢ ዘመን ትውልድ ተመክሮአዊ ትምህርት ሊሆነው ይችላል።

እንደተራ እንስሳ በዝቅተኛ ደረጃ የሚታዩት የየብሔረ ሰቡ ወገኖች፣ ማለትም እንደ ፉጋ፣ አጋሜ፣ ባርያ፣ ወይጦ፣ ሸንሎ....... ያሉ ማኅበረሰቦች አባላት፣ ከተጠናወታቸው የተዋረድና የሳይኮሎጂ ተጽዕኖ ጭምር ነጻ የሚወጡበትን ዘዴና መላ ማዘጋጀትና መታገል ባለብን በዚህ የትግል ዘመን፣ ነጠላ ፔቲ ቡርዣ የትግሉን ጭብጥ በማሳከርና የመደብ ጠላት ሊመታ የሚችልበትን የተጋድሎ ጎራ ለማወናበድ፣ ጥዋት ማታ ሲፍጨረጨር ይታያል። የባህልም ሆነ የኀሊና ነጻነት መከናውን የሚችለው ቅኖቹ የየብሔሩ ምዝብሮችና ጭቁኖች ነጻ ከወጡ በኋላ ነው። ይህ እስካልሆነ ድረስ፣ " የትልቅ ብሔር ዕቡይ ትምክሕተኝነትን፣ በጠባብ የጭቁን ብሔረተኛ ትግል ለመቋቋም፣ ወይም ጭቁን ጠባብ ብሔረኛነትን በትልቅ ዕቡይ ትምክሕተኛነት ለመታገል፣ ወይም ትልቅ የብሔር ትምክሕተኛነትን በጨቋኝ ጠባብ ብሔረኛነት ለመተካት " የሚደረግ የጊዜያችን ትግልና ውጣ ውረድ ሁሉ ትክክለኛ





አማራጭ አይሆንም። ብሔረሰቦች አለቅድሚያ ድርድር እኩልነታቸው መረጋገጥ አለበት። በእኩልነትም መኖር የተፈጥሮ መብታቸው ነው። ፍርድ፣ ነጻነትና ብልጽግና፣ ከነሙሉ መብቱ ኖሮት ይመሠረታል ብለን ለምንመኘው የወደፊቱ ብሩህ ማኅበረሰብ፣ ይህ ዓይነቱ የትግል አስተሳሰብ እንቅፋትና ደንቃራ ከመሆን አልፎ፣ አንዳች ጠቀሜታ ሊሰጥ የሚችለው ለሰፊው ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን፣ ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ሕጻንና ሽማግሌ፣ ሳይመርጥ በመደዳ በመጨፍጨፍ ላይ ያለውን የምርጥ መኰንኖች ሰው-በላ መንግሥት ብቻ ነው። በተጨ ማሪም፣ እንደ ሶሻል ሳይንስ ትንተና ከሆነም፣ የብሔር ችግር፣ ፍትሕና ዲሞክራሲ ከኢኮኖሚ እድገት ጋር በሚሰፍንበት ወቅት፣ ራሱ በራሱ ቀልጦና ሟምቶ የሚጠፋ የማኅበረ-ሰብ ጨው ነው።

በዘመናችን የኢትዮጵያ ጭብጥ ሁኔታ በግልጽ እንደ አሚያሳየው ከሆነ፣ ማኅበረ-ሰባዊውን እርከን ለማስረዳት ብዙ ስንጠቃና ትንተና አያሻውም። የኃይል አሰላለፍ ረድፎች ከመቸውም ይልቅ ቁልጭ ብለው አግጥጠው ይገኛሉ። መጣጩና ተመጣጩ፣ ጨባጩና ተጨባጩ፣ መዝባሪውና ተመዝባሪው፣ ገፊውና ተገፊው፣ እነማን እንደሆኑ ማንነታቸው ባደባባይ ተጋልጦ ይገኛል። የውስጥና የውጭ አድኃርያን ኃይላት ከባንዳዎቻቸውና ከምንደኞቻቸው ጋር፣ ባንድ ጎራ ቦድነው ሲገኙ፣ በሌላው ጎራ ደግሞ ምዝብሩና ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ከተራማጁና ከአጋር ኃይሎቹ ጋር ተሰልፎአል። ፋታ የለሌው እርቅ አልባው ፍልሚያም በየመልኩና በየረድፉ በመጧጧፍ ላይ ይገኛል። እነዚህ ሁለት ተጻራርያን ኃይሎች

በየጎራው ተፋጥጠው በትግል ላይ ናቸው። ማንኛውም ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ሊኖረው የሚችለው ምርጫ፣ ከነዚህ አንደኛው ብቻ ነው። ፈጽሞ የለየለት እብድ ካልሆነ በቀር፣ ከመጀመርያው የመኰንኖች ሰው-በላ መንግሥት ጎራ ለመጐራበት አይሞክርም። አድኃርያን የትም ቦታ ይኑሩ በየትኛውም ወቅት ይኑሩ፣ ዕድሜያቸው ኰንትሽ ነው። ይህን ሐቅ እያወቀ ዓይኑን ጨፍኖ፣ ካድኃርያን ምሽግ የሚገባ አይኖርም። በእንቡዘ-ልብ የሚገባ ቢኖር፣ ወዶ ገባነቱ የፍርድ በራሴ ደረሰኙ እንደሆነ ይወቅ።

የኢትዮጵያ ምዝብርና ግፉዕ ሕዝብ፣ በራሱ ፍላጎትና ውሳኔ መሠረት፣ የገዛ ድሉን በገዛ ትግሉ እስካገኘ ድረስ፣ ከመላው አድኃርያን ሠራዊት ጋር የተያያዘውን የጦፈና የጋለ ግብግብ ያለፋታ ትጥቁን ሳይፈታ ይቀጥላል። ይህን ሕዝባዊ ትግሉን የሚያወናብዱ ድኩማን ሁሉ፣ ጊዜያቸውን የሚጠብቁ ወላልቀው እንደሚጣሉ የከረከሠ መኪና ቡሎኖች ዓይነት ናቸው። ትንሽ በትንሽ ሲዝጉ ቆይተው በስተመጨረሻ የሚጠብቃቸው የውድቀት መራራ ጽዋ ነው።

ይህ ሕዝባዊ የተባበረ ኃይል፣ ውስጥ ውስጡን ተምዋ የሚከሠትበት ዕለት ትንሽ ይዘግይ እንጂ ወቅቱ ሩቅ አይደለም። አንድ ቀን ጎልብቶ፣ የውስጡንም ሆነ የውጭን ምንዝር ጠላቶቹን መንጥሮ ድባቅ ይከታል። በዚህ መራራ ትግል ላይ ግማሽ መንገድ የሚጓዙ፣ ግማሽ ታጋዮች ቢኖሩ አያስደንቅም። የትግል ነገር ባሕርይ ነው። በየጎራው ታይቶአል። " አይነጋ መስሎአት ከቋት አራች " ን ብሂል ያመለክታል እንጂ፣ ጎህ ሲቀድ ተዝናንቶ ሁሉን በነጻ ማድረግ ይቻል ነበር። ያ መከረኛ የኢትዮጵያ ምዝብር ሕዝብ፣ ዝንተ ዓለም ፍዳውን ሲቆጥር





የኖረውን ያህል ወደፊትም ለዘለዓለም የሚቀጥል አይደለም። የኅብረተ-ሰብ እድገታዊ ኪደትም ሕግ፣ በመከራው እንዲቀጥል አይፈቅድለትም። ፍትሕና ነጻነት ከነሙሉ መብቶቹ ጋር ያሰፈነ ሕይወት በእርግጥ አንድ ቀን ይኖረዋል። የብሩህ ተስፋ ባሌበት እንደመሆኑ መጠን የችግርን ተራራዊ አቀበት እየቧጠጠ የወጣውን ያህል በስተኋላ ላይ የሚንደረደርበት ቁልቁለት እንደሚጠብቀው ያውቃል። የማያወላውል ጽኑ እምነትና የማይበገር ቆራጥነት ያለው ሕዝብ፣ ምን ጊዜም ከበስተፊቱ ብሩህ ሕይወት እንደሚኖረው ያምናል። ምዝብርና ጭቁን የማኅበረ ሰብ መደቦች ተስፋቸውም እንዳስተሳሰባቸው ተራማጅ ነው። ፍትሕ የሰፈነባት ሕይወት ከነብሩህ ይዞታዋ ጋር እንደምትገዝፍለት ጠንቅቆ ያውቃል። ስለዚህም ነው የተያያዘውን ትግል የማያዋዛው።

የኢትዮጵያ ማኅበረ ሕዝብ፣ መሠረተ አቋሙ፣ የሰው ማኅበር እንደመሆኑ መጠን ከሌላው ዓለም ማኅበረ-ሕዝብ በባሕርዩ የሚለይበት ብዙ መለዮ የለውም። በተለይም በመሠረታውያን ሰብአዊ ፍላጎቶቹ አንጻር፣ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ነው። በየዕለቱ ለሕላዌው ማቆያ ምግብ፣ ልብስና ቤት ያስፈልጉታል። እነዚህንም ለሟሟላት የበኩሉን ትግል ያደርጋል። ሌላው ሕዝብ የሚኖረውን ሕይወት እሱ እንዴት መኖር አይችልም?

እንደማንኛውም መደባዊ ወጥ ማኅበረ-ሰብነቱንም የሚያደርገው ትግላዊ እንቅስቃሴ ሁሉ፣ ከሌሎች ሀገር ሕዝቦች የተለየ መሆን አይችልም። ቡርዡዋዊ ነፍጠኞች ለተሳሳተ

ዓላማቸው ሲሉ፣ ይህን ሐቅ ለራሳቸው እንዲስማማ አድር ገው፣ ጠምዝዘውና አጣምመው ቢያቀርቡት፣ ከመሠረታዊ ሐቅነቱ የጋት ያህል ወልፈት አይልም። ስለዚህም እንደ ማንኛውም በመደብ የተከፈለ ማኅበረ-ሰብነቱ ሊያካሔድ የሚ ችለው ሐቀኛ ትግል በመደብ ልዩነት ባሕርይ ብቻ የተመሠረተ መሆን አለበት። ይህ እውነታ በሥነ-ማኅበረ-ሰብ ጥናት የነጠረ ሐቅ መሆኑን መካድ አንችልም። የትግልን መሠረታዊ ባሕርይና መንፈስ፣ በማንበግበዥ፣ የሚፈጠርባቸውን ብዥታ ለሌሎች የሚረጩ ሁሉ፣ ይህ ዓይነቱ ብዥታቸው ዘመን ያለፈ በት ተረት መሆኑን መረዳት ይኖርባቸዋል። በተለይም ሰው በላዎቹ መኰንኖች! ወይም ሌሎቹ!!

አሻፈረን ብለው የፈለጉትን ፕሮፓጋንዳ ያራምዱ እንጂ፣ ሙከራቸው ውሃ መቋጠር እንደማይችል ማወቅ አለ ባቸው። እንዲያውም በዚህ ሴራቸው የሚጠቅሙት ድርጅት ቢኖር፣ ሥልጣንና ጥቅም የጠማውን የውጭና የውስጥ ኢዲ ሞክራሲያዊ ቡድን ብቻ ነው። በዚህም ድርጊታቸው በኢት ዮጵያ ሕዝብ ላይ እንደመቅሰፍት ሲወርድ የኖረውን ያሠርታት ግፍና ደባቸውን እንዳራዘሙት መረዳት ይኖርባቸዋል። የተባበረ ኃይል ሕንጻ ሰናኦርን ያህል ጠራራ ግንብ አሠርቶ በጸሐይ ሙቀት ምግብ አብስሎ እስከማብላት ድረስ ማስቻሉን ከታሪክ መማር ይቻላል። ምንም ዓይነት ተአምር ያዘለ ሎጂካዊ ዲያሌ ክትም ቢሆን እንኳ፣ ሰዎችን መበታተን እድገትን ሊፈጥር ይችላል ብሎ በድፍረት መናገር ምንም እርምት የማይገኝለት ድፍን ስሕተት ነው። ካለማችን የተፈጥሮ ሕግ ውጭ መሆኑን በብዙ ማስረጃዎች ማሳመን ይቻላል። ለሌሎች ዘርፋውያን





ትግሎች ሁሉ ከትልቁ አብዮት በኋላ ተከታትለው የሚመጡ በሕዝቦች መካከል ያሉ ቅራኔዎችና እነሱንም በመፈታቀድና በውይይት አማካይነት የሚፈቱ “ የዘመድ ጥል የሥጋ ትል ” እንደሚሉት ያሉ ናቸው።

ማንኛውም የሰው ልጅ በምትሐት ወይም በተአምር ከሰማያት በርቆ የወረደ ፍጡር እንዳለመሆኑ ሁሉ በሥርዓት የሚኖርበት ሀገር አለው። ይህም ሀገሩ እንደፍላጎቱ ሊኖርበት የሚገባው መብተ ልደቱ ነው። በገዛ ሀገሩ ላይ የተፈጥሮ ዋልጌ ሆኖ መኖር የሰብአዊነቱን ክብር ይጻረርበታል። የተፈጥሮ መብቱንም ያጕድፍበታል። ሕግ የሚያስከብረው መብታዊ ጥያቄ በመሆኑ የሁሉም የያንዳንዱም ተፈጥሮአዊ አቋሙ ነው። ስለዚህም ነው የዲሞክራሲያዊ ፍትሕ፣ የነጻነት ፍትሕ፣ የመብት ፍትሕ....... ለሁሉም ለያንዳንዱም በእኩልነት እንዲ ሰጠው የምን ጊዜም የሰዎች ትግል ዓላማ የሆነበት። ይህ ትግል ከያንዳንዳችን ለሁላችን፣ ከየሁላችን ለያንዳንዳችን የሚ ጠበቅ ሐቀኛ ትግል ነው።

ተዘውትሮ እንደሚነገረው ” የኢትዮጵያን ጉዳይ ለኢትዮጵያውያን ብቻ መተው አለበት” የሚሉ ወገኖች አሉ። በርግጥም ባዕዳን፣ የኢትዮጵያውያንን ያህል ለሀገራቸው ደኅንነት ያስባሉ ብሎ ማመን ያስቸግራል። በተጠቀሰው ነጥብ ላይ የበኩሌ አስተያየት የተለየ ነው። እንደ ሰው ልጅነታቸው ስለማንኛውም ሀገር ሕዝብ ችግር የሚጨነቁ፣ ቍጥራቸው ይነስ እንጂ በየትኛውም ሀገር ይገኛሉ። እነዚህ ስለጠቅላላው የሰው ልጅ ቅን አስተያየት ያላቸው ሰዎች፣ በኢትዮጵያ ግላዊ ጉዳይ ላይ ያገባናል ብለው ለእርዳታ ቢመጡ መቃወሙ

አግባብ አይመስለኝም። በትንሹ የባዕድ ሀገር ኑሮ ዘመኔ፣ የሰዎች ችግር እጅግ የሚያንገበግባቸው ብዙ ቅን ሰዎች በየሀገሩ መኖራቸውን ተረድቼአለሁ። አብዛኞቹም ከበርቴዎች ሳይሆኑ የመለስተኛ ኑሮ ባለቤቶች ናቸው። በተለይም የኢትዮጵያ ውያን የእልቂት መጠን እጅግ አብጦ በነበረበት ባለፉት ቀውጢ ዓመታት ወቅት፣ የእነዚህ ባዕዳን ሀገሮች ጭንቀትም እኩል አብጦ እንደነበረ በቅርብ ሆኘ አይቻለሁ። እኛ የሩቅ ምሥራቅ ታላቅ መምህር “ የጭቁኖች የበደል እንጉርጉሮአዊ ዜማ የትም ምንጊዜም ይዘመር እንጂ ቅላጼውና ምቱ ( ሜሎዲውና ሪዝሙ) ተመሳሳይ ነው ” እንዳሉት በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ያልተፈታ ችግር የየትኛውም ሀገር ቅን ዜጋ ቢቆረቆርና በጉዳዩ ያገባኛል ቢል ሎጂክ አለው። ተንኰለኞቹ ባዕዳንማ ጣልቃ ቢገቡ ያለውን ችግር ይበልጥ የሚያቀጣጥሉ ጋዞች መሆናቸውን ደጋግመው አሳይተውናል።

ይህ የባዕዳን ጉዳይ መነሳት አንድ ሌላ ነጥብ አስታ ወሰኝ። እኔ ባለችኝ ትንሽ ዕድሜዬ ውስጥ አራቱን ታላላቅ አህ ጉራት ( በሐወርት ) ላጫጭር ወቅቶች ተዘዋውሬ የማየት ዕድል በማግኘቴ፣ ለግሌ ያህል የሚረዳ መለስተኛ ዓለም አቀፋዊ የትዝብት ጭላንጭል ያካበትኩ ይመስለኛል። የምንኖርበት ዓለም ፍጹም ትክክል ነው ማለት ባይቻልም፣ ሰዎች ከሠፈሩበት ወቅት ጀምሮ የተዛባ ሥርዓት ተንጥፎባት የባሰ ችግር ተፈጥሮባታል። ማን እንደመደባቸው ዝርዝሩ ባይታወቅም፣ በትንሽ ሚጢጢ ሀገር ውስጥ፣ ብዙ ሕዝብ ተጣቦና ተጨናንቆ ይኖራል። ባንጻሩ ደግሞ፣ የሰማይ ስባሪ በሚያህል ሰፊ ሀገር ውስጥ፣ ጥቂት ሕዝብ እየተንቀባረረና





እየተዝናና የሚሆነው መላ ቅጥ ጠፍቶታል። ዓለማችን ( ምድር ) ባለ አንድ ወርድና ስፋት የሆነች አንዲት ነጠላ ሞልሟላ አካል መሆኗ ቢታመንም ሰው ሠራሽ የሆነው የየሀገሩ ድንበር ምድሪቱን በምክንያት ሳይሆን በስሜት ሜትር በየዘመኑ እየለካ ክልሎ ክልሎ እስከዚህ የእገሌ ሀገር፣ እስከዛ የእገሌ ሀገር እያለ በመደንበር የማያስፈልጉ የሰዎች ልዩነቶች ፈጥሮ፣ ለጦርነቶችና እልቂቶች መነሻ ምክንያት ሆኖ ኖሯል። ይበልጥ የሚያሳዝነውና የሚያሳፍረው ደግሞ፣ ለግላዊ ጥቅም በመንሰፍሰፍ፣ ዓለምን የጦር መሣርያዎች ማምረቻ ያደረጓት ሀገሮች የመርዘኞቹ መሳርያዎቻቸው ማምረቻ ኢንዲስትሪዎችና ፋብሪካዎች የሚተፉት አሰርና የተቃጠለ ካርቦን ክምችት ብዛት የተነሳ፣ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ፍጡራን-ምድር፣ እንስሳትና ዕጸዋት መተንፈሻም ሆነ መድረሻ አሳጥተዋቸዋል። ነዋሪዎችዋ ምንም ዓይነት አማራጭ ሊያገኙ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ሌላው ደግሞ የሰዎች ተንኰል ከመቸውም ዘመን ይልቅ ጐልብቶ ጠቅላላውን ሥነ-ምግባሮች እያዳሸቃቸው ነው። ድሆች ሕጻናት ከድሀ ሀገሮች ተሸጠው እየተወሰዱ፣ ጤንነቱ ለከዳው የከበርቴ ሰውነት በጤንነት ማሚያነትና መጠገኛነት የሚያገለግሉ ያካል ተለዋጭ ብልቶች ሆነዋል። የሶስተኛው ዓለም ሀገሮችም የኑክሉር አሰር ኀልኀታ እየሆኑ ነው። ይህ እንግዲህ ዓለማችን ባጠቃላይ መልኳ ስትታይ የምትፈነጥቀው ብልጭታ ነው።

በቅርብና በዝርዝር ደግሞ በማኅረሰባቸው ሥርዓቶች የሚለያዩ ሁለት የኖርኩባቸውን ሀገሮች ልጥቀስ። ጐረቤቶች አይደሉም። አንዱ በጋርዮሽ ሕይወት የሚመራ ሀገር ሲሆን፣

ሌላው ደግሞ በተናጠል ግለኛ ሕይወት የሚያምን ሕዝብ የሚኖርበት ሀገር ነው። አንዱ ብዙ ሕዝብ የሚኖርበት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ጥቂት ሕዝብ የሚገኝበት ነው። ያንደኛው ሕዝብ ለነጻነት ሲንሰፈሰፍ ሌላው ሕዝብ ደግሞ በነጻነት ይጫወታል። አንዱ ለዲሞክራሲ ሲጓጓ፣ ሌላው በዲሞክራሲ ይሞላቀቃል። አንዱ የምድሩን ሲሳይና ጥሪት ለመቆጠብ ሲጨነቅ፣ ሌላው ደግሞ የሀገሩን ሀብት ያላግባብ ሲያባክንና ሲንቀባረርበት ይገኛል። ያንዱ ሀገር ቤተሰብ ባስር ኳድራት ቆጡ ውስጥ ከነልጆቹ ተጨናንቆ ሲማቅቅ፣ ሌላው ደግሞ ከመቶ ኳድራት ሜትር ስፋት በላይ በሆነ ቪላ ውስጥ እየተንደላቀቀ ይዝናናል። አንዱ የላሙንና የዶሮውን ወተትና እንቁላል ምርት በወር እንኳ አንድ ጊዜ ማግኘት ሲሳነው፣ ሌላው በቀን ከሀያ እጥፍ እያገኘ አነሰኝ ብሎ ያጉረመርማል። አንዱ ቡናና ስኳር ለቅምሻ ያህል እንኳ ማግኘት ተስኖት ሲንጠራወዝ፣ ሌላው ተርፎት ያመት ስንቅ ያከማቻል። የቤት እንስሳቱንም ይመግብበታል። ............ ታዲያ እነዚህ የሁለቱ ሀገሮች ሕዝቦች፣ ባንዲቷ ምድር ውስጥ፣ አንዲቷን ዠምበር እየሞቁ የሚኖሩ ናቸው። " ኖሩ " የሚለው ቃል ለሁለቱም ሕዝቦች እኩል ማገልገሉ በጣም ይደንቀኛል። ታዲያ ይህን አድላዊ ዓለም ምን ይሉታል? ዳግማይ የመዋቅር ተሐድሶ ሊደረግበት የሚገባ ዓለም ነው። የየሀገሩን ቅን ሰዎች ሐቀኛ ትግል ይጠይቃል። የየሀገሩን ስፋትና የየሕዝቡንም መጠን እንደገና ማስተካከልና ማካፈል ያስፈልጋል። በበኩሌ በመንታ ተቃርያን ሥርዓት አደር ሀገሮች በመኖሬ፣ ከቀለሙ ትምህርታቸው ይልቅ፣ ያኗኗራቸውን ሁኔታ ማየቴ ብቻ ሰፊ እውቀትና ከፍተኛ





ተመክሮ ለግሰውኛል። ትዝብቴን ሳጠቃልለው፣ ያለማችን ጊዜያዊ ችግር፣ የግለ-ሰብ ስግብግብነት ( ኢጎይዝም ) ስሜት በየሀገሩ ጥቂት ሰዎች መንፈስ ላይ ሰፍኖ፣ አለመጠን መጎልበቱና መደርጀቱ ነው። እነዚህም ጥቂት የየማሕብረ-ሰቡ ከበርቴ ክፍሎችና ገገር መደቦች በባሕርያቸው የሕዝብ ወገኖች ባለመሆናቸው፣ የብዙኃኑ ጭንቀት አይሰማቸውም። ከሚኖርበት ቪላ ሌላ ትርፍ ቪላዎች የሚጨምርበትን ዘዴ ይፈልጋል እንጅ፣ ሌላው መሰሉ ፍጡር ማደርያ ጐጆ አጥቶ በየበረንዳውና በየዱሩ ሲንገላታ መኖሩ ጭራሽ አይታሰበውም። ደሀ በልቶ ቢያድር ባያድር፣ ደንታው አይደለም። ሲፈጥረው "በቃኝን " የማያውቅ በመሆኑ ካለው ላይ ይበልጥ ለመጨመር ምን ጊዜም እንደተንሰፈሰፈ ነው። የሚገርመው ደግሞ እነዚህ ዓይነቶች ሰዎች፣ ራሳቸው ሳያመርቱ የሌሎችን ምርት በመዝረፍ የቶጀሩ ፓራሳይቶች ናቸው። እጅግ የሚገርመኝ ባለማችን ያሉ ሥርዓቶችና ዓለሙ ራሱ ለእንደነዚህ ያሉ እበላ ባዮች ፍላጎትና ምኞት ሆን ብሎ የተቀናጀ መሆኑ ነው። ያደባባይ ዘራፊዎች ሆነው፣ ድርጊታቸው እንደ ትልቅ ሙያ ተቆጥሮ፣ ሎሌ ( ስማርት ) እስከመባል ድረስ ይደነቁበታል። ይሁን እንጅ ዓለማችን በዚህ ሁኔታ መኖርም ሆነ መቀጠል እንደማይችል እሙን ነው። እያደገ የመጣው የሙስና ቅራኔ እልባቱ ላይ ሲደርስ ራሱ እንደሚገታው ግልጽ ነው። ያለሙን ኪደት ወይም ይህን ጥቂቱን ሰፍሳፋ ክፍል፣ በእንቡጡ ቀጭቶ ባጭር ወቅት ውስጥ ለማግታት፣ የየሀገሩ ቅንና ተራማጅ ሕዝባዊ ወገኖች አሁንም በትብብር መሥራት ይኖርባቸዋል። የጊዜና ያስተባባሪ እጦት ሆኖ እንጅ፣ ይህ ውሳኔ ከጸደቀ ከርሟል።

በዓለማችን ላይ ጥቂቶች አልጠግብ ባይ ስፍሳፎች እስ
ካሁ ድረስ፣ በምድር ላይ ሰላም ሊሰፍን አይችልም። በሰዎችም
መካከል፣ የጋርዮሽ የሆነ ነጻነት፣ ፍትህ፣ ፍቅር፣ ...... ሊኖር
አይችልም።

" ሽምብራ በልቶ የማይፈስ፣ ኮካ ኮላ ጠጥቶ የማያገሳ
የለም " እንዲሉ፣ ምድራችን ዕቡዮችንና ተንኰለኞችን፣ ትዕቢ
ተኞችንና ትምክህተኞችን ይዛ እስካለች ድረስ፣ ሰላማዊ ሕይወ
ትና የነጠረ ሥነ ምግባር ይሠፍንበታል ብሎ መጠበቅ፣ መቃ
ዠት ነው። ከእንደዚህ ዓይነቱ ባዶ ምኞትና ተስፋ ይልቅ፣ ለዓ
ለማችን ጠንቅ የሆኑትን ጥቂት ፀረ ሕዝቦችን መመንጠሩ፣ ጥሩ
አማራጭ ነው። በተለይም አንዳንድ በመሪነት ደረጃ ጫፍ ላይ
ቂጥጥ ብለው ለግል ትልማቸውና ጥቅማቸው ሲሉ ሕዝብን
እርስ በርስ በማናከስ የሚያምሱ በመሆናቸው አስቀድሞ መመ
ንጠሩ፣ ተቀዳሚ የማይገኝለት ግዴታ ነው።

ምንም እንኳ፣ የጥልጣሉን፣ የጉጂውን፣ የኩናማውን
ኑሮና፣ የጎቢን የካልሃሪን፣ የሰሐራን ምድረበዳዎች፣ እንዲሁም
የራስ ዳሽንን፣ የቲቤትን፣ የአልፕስን ተራራዎች ............
ምንነት በቅርቡ ሆኖ ዝርዝር ሁኔታቸውን ሠቅሥቆ ያጠና
ባይኖርም፣ ዛሬ ዓለም ከመቸውም ይልቅ፣ ወርድና ስፋቷ
በሳታላይት ረዳትነት ጭምር ተለክቶና ተቀምሮ፣ በትንሽ ወረ
ቀት ላይ ሠፍሮ ይገኛል። ጤናማ የሆነ የማንኛውም ሰው
ኅሊና እንደሚረዳው ከሆነ፣ ምድራችን ቀርታ ኅዋኀወ-ሰማያት
( ጋላክሲ) ጭምር እጅግ ጠባብና ትንሽ ድምብላል እየሆኑ
መጥተዋል። እውቀትና ሥልጣኔ የሰዎችን ጠባብ ያስተሳሰብ
አድማስ እያሰፉ በመጡ መጠን፣ የዚያኑ ያህል ለዓለም ያለን





ዕውቀታዊ ምልዓት በመጥለቁ፣ ዛሬ እድሜ ለብሩሃን ወገኖች
እንጂ፣ በፈጣን ሰማያዊ ሠረገላ ተምዘግዝጎ ካንዱ በሐውርት
ወደ ሌላው በሐውርት በሰዓቶች እድሜ ውስጥ መድረስ
ተችሏል። በዘመናችን አዲስ አበባ ላይ ቍርሱን የበላ ቸኳይ
መንገደኛ በአክናፋት ተንደርድሮ፣ ለኒው ዮርክ ምሳው ተዝና
ንቶ ይደርሳል። ዕድሜ ለኮምፒዩተርስና ሪሞት ሴንሰሮች
እንጂ፣ ጥንት ሲያስቸግር የኖረው የርቀት ኃይላዊ ጉልበት
ተሰብሮ፣ በኬክሮስና በኬንትሮስ ስንባጭ መለካት ግድ
ሆነበታል። ዛሬ ካንደኛው ግማደ-መሬት ዋልታ ላይ የሚደ
ረገውን ድርጊት፣ በዛው ቅጽበት ለሌላው ግማደ-መሬት ዋልታ
ኣስተላልፎ ማሳየትና ማናገር ተችሏል። እነዚህ ሁሉ ሳይንሳዊ
እሴቶች የሚያስረዱን፣ የምንኖርበት ምድር ትንሽና ያንድ
ተፈጥሮ ወጥ ሕዝቦች መኖርያ ዋሕድ ቤት እንደሆነች ነው።
ሌላው ታንቲራ ሁሉ ግን በእውቀት ማነስ ምክንያት በየዘመኑ
የነበሩ ደካማ ሰዎች የፈጠሩት፣ ኋላ ቀር ልማድ ነው። በዚህም
ልማዳዊ አሠራር የተነሳ፣ የዓለሙ ሕዝቦች ሁሉ፣ ያለምድሪቱ
ባሕርይ፣ በድንበር ተከፋፍለውና የባሕል አጥር ሠርተው
ይኖራሉ። ያስ ዓለማችን ጠባይ ሕዝቦች ተለያይተው እርስ በር
ሳቸው እንደተናቆሩ አሉ። በየዘመኑ እንደ አሸን የፈሉትም
ጦርነቶች፣ ላጠቃላይ እድገት ሊውል የሚችለውን የኢኮኖሚ
ምንጭ ጨልጠው እየጠጡ፣ አብዛኛውን የዓለም ሕዝብ
በችግር ሲያማቅቁት ኖረዋል።

በየሀገሩ ድንበሮች መጣስ በተጫሩ ጦርነቶች ምክንያት
ብቻ፣በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ንጹሐን የሰው ልጆች አልቀዋል።
የአንዱ ክልል ሀገር ሕዝብ በሀብቱ ጠግቦ ቁንጣን ሲያማቅቀው፣

በአንጻሩ ደግሞ የሌላው ሀገር ሕዝብ፣ በረሀብ ጠኔ ተጠብሶ ያልቃል። የአንዱ ሀገር ሕዝብ የሌላውን ሀገር ሕዝብ ተንኩሶ ይቀጠቅጠዋል። ሌላው የሦስተኛው ሀገር ሕዝብ በመገላገል ፋንታ፣ ከዳር ቆሞ ያስካካል። ሌላው ደግሞ የሚቀጣቀጡበትን መሣርያ እየቸበቸበ፣ በገንዘቡ ሻምፓኙን ይልፋል። ሌላው ደግሞ በግርግሩ መሐል ገብቶ እያወናበደ ይዘርፋል። .......... ይህ ሁሉ የሚሆነው በተፈጥሮአቸው ተመሳሳይ በሆኑ የሰው ልጆች መካከልና ነጠላና ዋሕድ በሆነችው አንዲት ምድራችን ላይ ነው። ፊው!!! በእግርጥ አለመታደል ነው።

ይህ ዓይነቱ አሳዛኝና አሠቃቂ ክሥተት፣ ከየትኛውም ሀገር ይልቅ በተለይ ከሺ ዓመታት ላላነሰ ጊዜ፣ በኢትዮጵያውያን ላይ እጅግ ከፍቶ ታይቷል። የጥንቱ እንኳ፣ በዕውቀት ማነስ የተፈጸመ የድንቍርና ድርጊት ነበር የሚያሰኝ የይቅርታ አስተያየት በመስጠት ሊታለፍ ይችል ይሆናል። ዛሬ በኻያኛው የሥልጣኔ ክፍለ ዘመን ካባውን ቀይሮ በዓለም አቀፍ ወዳጅነት ስም ሲፈፀም መታየቱ ላጠቃላዩ የሰው ልጆች ሞራላዊና ኅሊናዊ አስተሳሰብ የሚቀርብ፣ የዘመናችን ታላቅና ተቀዳሚ ጥያቄ ነው። በሕግጋተ-ዓለም አሻፈረኝ የሚል ደባን ሕገ-ሞራል ይቋቋመው ነበር። ሕገ-ሞራልንም ጭምር ረግጦ የሚያልፍ ጋጠ-ወጥና ጀርጃራ ኃይል ሲነሳ የምን ጉልበትና ሥልጣን ያርቀው ይሆን? የዘመኑን የኃያላን ውንብድና፣ ለታሪክ ፍርድ ብቻ መተው ይሻላል።

በዓለማችን ነባራዊ ባሕርይ ሁኔታ በጣም ከሚያገዙ ሰዎች አንዱ ነኝ። የኢኮኖሚያዊ ፍትሕ ማጣት፣ ነዋሪዎቿን ከረበሸው ዋናውና አንደኛው ችግር ነው። ተከታዩ ደግሞ





በየሀገሩ፣ የቅን ዜጎች ማነስና መመንመን ነው። ባለማችን የእንደዚህ ያሉ በቍዔቶች አለመሟላት ጠብና አለመግባባት እንዲነግሡ ረድቷቸዋል። ስለሆነም፣ በዓለሙ ውስጥ በተፈጥሮ ሕመም ከሚሞቱ ሰዎች ቍጥር ይልቅ፣ በኢተፈጥሮ ሕመም የሚያልፉቱ ይበዛሉ። ይህም አሠቃቂ ሁኔታ መጠኑ እየጨመረ እንጅ እየቀነሰ አልመጣም። ኸረ ለመሆኑ በሕዝቦች ዘንድ ፍቅርን ለማስፈን ምን ዓይነት መፍትሔ ይበጅ ይሆን? መልስ የሚጠብቅ ጥያቄ ነው።

በርግጥ እኮ የሰው ልጆች የርስ በርስ መራራት ባለማችን ቢሰፍን ኖሮ፣ መች ጠላኝና ተጠላኝ፣ መጥማጭና ተመጥማጭ፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ........ የሚባሉቱ መንታ መደበ-ሰዎች ይኖሩ ነበር? የርስ በርስ መራራት ባለመኖሩማ፣ ይኸው በደረስንበት የማኅበረ-ሰብ እርከናዊ ደረጃ ላይ፣ የከበርቴው ሥርዓት ምንጩ- ምርቶችን በሥርዓተ-ግለኝነት መመሪያው፣ እንደ መኻገር ለብቻው ተጣብቆ እየመጠመጠ ባስገኘለት ጉልበቱ፣ ተቀናቃኞቹን የሥርዓተ ጋርዮሽ ሶሻሊስቶች ሲከላከል ይታያል። ግን ባይገባው ይሆናል እንጅ፣ የዓለማችን ሕዝባዊ ጉዞ ሁሉ ነገር የጋርዮሽ ወደ እሚሆንበት ካምፕ ነው። የመዳረሻ ጉዞውንም ወቅት ለማሳጠር፣ ትግል በየመልኩ በየሀገሩ ይካሔዳል።

በየሃገሩ ያሉ አድኃርያን ኃይሎች ግን፣ ይህን ትግል ለማሰናከል እንደጣሩ ናቸው። ከንቱ ጥረት!! ሰው እንዴት ከታሪክ ለመማር እንደማይችል ኣይገባኝም። ያለፉት ዘመናት ታሪክ በሙሉ፣ ሲያሳዩ የኖሩት የለውጥን ያዲስ ልደታዊ ኪደት ነው። ከነበረው ምን ጊዜም ለመሻሻል......

በጊዜያችን በሀገራችን ሥልጣን ኮርቻ የተፈናጠጡ ገዢዎች፣ ይህን ሐቅ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የረሱት ይመስላል። በመሆኑም ከጥንተ-ሥርዓታቸው ጋር ተጣብቀው፣ በመከረኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ፣ በሙስናና በወሲብ ሲባልጉበት ይታያሉ። ምንም እንኳ የቆብ አጥላቂነት ዝርያነታቸው ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መሆኑ ቢታወቅም፣ እንደዘመኑ ሰውነታቸው ራሳቸውን አርመው ማስተካከል በተገባቸው ነበር። ይህ ዓይነቱን ባሕርይ ምርጥ መኰንኖች የወረሱት ነው ሲባል ያለ ምክንያትና ያለማስረጃ አይደለም። ጥንትም ዛሬም መከረኛውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲለበልቡት የኖሩ የዛሬዎቹ ገዢዎች የሙያ አባቶች ለመሆናቸው ካንዲት መጽሐፍ ብቻ ልጥቀስ ( ይህ ማለት ሞራል ያላቸው ጥቂት ወታደሮች እንዳሉ በመዘንጋት አይደለም። )

...... " እስከ ትላንት ድረስ በነአጼ ቴዎድሮስና በነአጼ ዮሐንስ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ደሀ ለወታደር መጫወቻ ባርያ ነበር። ባርያ በገዛ ራሱ ማዘዝ እንደማይሆንለት የኢትዮጵያ ደሀም በገዛ ቤቱ ማዘዝ አይሆንለትም ነበር። የሚያዝበት ቆር ፋፋ ጋሻ ያነገበና፣ አንድ ባለጌ ጦር የያዘ፣ አንድ የመሸበት ደበናንሳ የጀራረገውና ተሰገባው በስፍራ ተጣልቶ ፀሐይ የሚሞቀው ጎራዴ መሳይ በወገቡ ያገነበጠ ቅማላም ወታደር ነበር። ይኸ ወታደር ግን እሱን ደስ ላይለው የሌላውን ደስታ ሲከላከል ለገዛ ራሱ ላያልፍለት የድሀውን ንብረት ሲያፈርስ ይኖር ነበር። ይኸ ወታደር እንኳንስ ተሰሪነት ገብቶ፣ ለቅሉጥ ሒዶም ባደረበት አገር ሳይቀር፣ ድሀውን የፊጥኝ አስሮ፣ ንጭ ኑግ፣ ጥቁር ወተት ውሰድ ሲልና ባለቤቶቹ ሚስቲቱ እንደ





ገረድ፣ ባልየው እንደሎሌ እግር አጥበው፣ አልጋ አንጥፈው፣ ትራፊውን በልተው፣ እነሱ ተምድር፣ እሱ ታልጋ ተኝተው ያድሩ ነበር። ከቶም አንዳንድ ጊዜስ መልከ ቅን ምሽት የነበረችው በላገር በመከራ ላይ መከራ፣ በግፍ ላይ ግፍ፣ በውርደት ላይ ውርደት ታክሎባት ያድር ነበር። " ( ገጽ 2) ..... በነአጤ ቴዎድሮስና በነአጤ ዮሐንስ ጊዜ ከጅብ አምልጦ የቀረ ቆርበት የመሰለ ጨርማዳ ጋሻ በብብቱ ያጣበቀና፣ ባለቋድ ወይም ሲሶ እንጨት ብረት መሳይ በጫንቃው አጋድሞ ብቅ ያለ እንደሆነ አንድ እከካም ነፍጠኛ ብቻውን ሆኖ አንድ መንደር ሲያስር ሲፈታ፣ ሲያስጨንቅ ያድር ነበር......... ( ገጽ 4) ..... ወታደሩ ዘመቻ ሲሉት ጐራዴውን መሳል፣ ፈረሱን ማጠጣር፣ ጠበንጃውን መወልወል፣ ተነስም ሲሉት ለውሻ የሥጋ ክምር፣ የርጎ ባሕር አለ ቢሉት ወዴት ነው ሳይል እንደሮጠ ለመዝረፍ፣ ከብት ለመንዳት፣ ተልባ እስካሮጌው ለመፍጀት፣ ተቆንጆ እስከ ባልቴቱ አጋፎ ለባርነት ለማምጣት ይቸኩል ነበር እንጂ......" ( ገጽ 45 )

( ዳግማዊ ምኒልክ፣ አፈወርቅ ገ.ኢየሱስ 1901 ዓ.ም. )

የወረስነው የማኅበረ-ሰባችን ዋርድያ፣ ጥንተ-ልምዱ፣ ጥንተ-ግብሩ፣ ጥንተ-ባሕሉ፣ እንዲህ መሆኑ ከታወቀ፣ በዘመናችን የሚገኝ ዝርያው ሞዴልነቱን ቢያንፀባርቅ ከቶ ምን ያስደንቃል? አሁንም የሰው ልጅ ለምን ካለፈ ታሪክ መማርና ተመክሮውንም ለመረዳት እንደማይችል አይገባኝም። የዚህ ትውልድ ትልቁ ተግባር እንዲህ ያለውን ድክመት ተረድቶ ይህንን የጃጀ የወታደር ሥርዓት ማናጋትና ማፍረስ በምትኩም አዲስ ዲሞክራታዊ ሥርዓት መገንባት ነው። ጉልበት የሚገ

ዛውን ምንዝር ሕዝብ፤ ጉልበት ያለው የተባበረ ሕዝብ ነጻ
ያወጣዋል። ኅብረት የዘመናችን ክበሮ የዕለቱ ታንቡር ነው።
ተባበሩ በሚል የጥሪ ድምጽ ይንራል፤ ይነዝራል። በአሁኑ ጊዜ
አገዘን ኅሊና አለኝ የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ፤ በመስማት ሊጠ
ቀምበት የሚገባው ድምጽ ቢኖር ይህንን ጥሪ ብቻ ነው።
የሀገራችን ሕዝባዊ ችግሮች ከመቸውም ጊዜ ጎልተውና አፍ
ጠው በአደባባይ በሚታዩበት በአሁኑ ዘመን ችግሩ የሚመለከተን
ወገኖች ሁሉ የምናቀርበው መፍትሔ ለዘለዓለሙ የሚደነቅ
ነው። እንዳንዶቹ መፍትሔዎች በቀረቡበት ዘይቤና በሚገ
ለጹበት ይትብሀል ቢገመገሙ " ከፍየልና ከበግ ሥጋ የትኛው
ይጥማል? " ተብሎ የተጠየቀ አንድ መገለጢጥ ሰው፤ ያልበ
ላውን እንደሚያኩለት ጭቷም ሰው፤ ' የዓሳ ሥጋ ያሟል
ጫል' " ብሎ እንደመለሰው ዓይነት ናቸው። የማኅበረ-ሰብ
ችግር መንስኤዎችና መፍቻም ቊልፎቻቸው በሶሻል ሳይንስ
ቊልጭ ተደርገው ነጥረው ቀርበዋል። የችግሩም አጠቃላይ
መምሪያው " መጣጭን ከተመጣጭ የግድ ገንጥሎ የመጣል
ዚቅ ብቻ ነው። " በዘመናችን ዓቅም ያነሳቸው ፈሪ ተገፊዎች
እንኳ፤ ዕድሜ ለዘመኑ ሳይንስ በሩቅ የሪሞት ኮንትሮል ፈንጂ
ገፊ ኃይሎችን ያጠዛሉ። ...... የኛ ሊቃውንት ግን ልዩ የትግል
መፍትሔ ቆፍረው ለማውጣት ግላዊ ሪሞት ኮንትሮላቸውን
በአየር ላይ ደግነው የሚያፈንዱት ግዙፍ አካል ሳያገኙ ቆይተ
ዋል። ይህም በመሆኑ የሀገራችን ሕዝብ ችግር ከጌዜ ወደ ጌዜ
እየባሰበትና እያስመረረ መጥቷል።

እንደሚታወቀው በማዕበለ የካቲት የለውጥ ጭላንጭል
በመጠነ ጨረር ፈንጥቆ ነበር። ገና እንደተወጠነ መቀጨቱን





ብዙዎቻችን እናውቃለን። ያ ጅምር ከፍጻሜ መድረስ ያለበት
ሕዝባዊ ውጥን ነው። በመደበኛ ደረጃ ያሉ መደበኛ ቅራኔ
ዎችን እንዳሉ ወዝፏቸው ጨንግፏል። የትግል ስልት ተሳክሮ
ጠላኸ ጠላትን ከሥልጣን ላይ አስቀምጦ አልፏል። ቢቸግ
ራቸው የጊዜአችን አንዳንድ ታጋይ ክፍሎች በሁለተኛ ደረጃ
የሚገኝ ቅራኔን አስቀድመው፤ አለደረጃው ለመፍታት በመራ
ወጥ ላይ ናቸው። የትግል ሥርዓት ግን እንደ መሰላል ያለ
በመሆኑ፤ በስተታች ያሉትን ቀዳማይ መወጣጫዎችን ሳያልፉ፤
ከላይኛው መድረስ እንደማይቻል ግልጽ ነው። የደረጃን
ቅደም ተከተል ይጠይቃል።

ሉሹን የሚባለው የቻይና እውቅ ደራሲ የመጀመርያ
የሙያ መስኩ ሥነ-ጽሑፍ አልነበረም። በዘመኑ፤ ከዚያ ሁሉ
መዓት የቻይና ምሁራን ውስጥ የተለየ ዕድል ገጥሞት፤ ጃፓን
ቶክዮ፤ ነጻ የትምህርት ዕድል አግኝቶ ሊማር የሔደው ሕክ
ምና ነበር። በትምህርቱ ላይ እንዳለ የሰፊው ቻይና ሕዝብ
በሽታና ደዌያት መነሻው ራሱ በሽታው ሳይሆን፤ የማኅበረ-
ሰቡ በትምህርት ወደ ኋላ መቅረትና ለድንቊርና ተገዢ መሆ
ኑን ይገነዘባል። እነዚህን ህዝባዊ ችግሮች መቋቋም የሚቻለው
በኪኒንና በመርፌ ( መድኃኒት) ሳይሆን በመሰረተ-ትምህርት
ነው ብሎ በመወሰን፤ ወዲያው የጀመረውን የሕክምና ትምህ
ርት አቋርጦ ወደ ሀገሩ ኰብልሎ በመመለስ፤ በደረሰ በማግ
ስቱ ባስተማሪነት ተቀጥሮ የመምህርነት ሥራ ጀምሯል። በማና
ቸውም የተግባር ስምሪትና መርሐ ግብር ላይ የቅደም ተከተ
ልን ሥርዓትና የደረጃ እርከናዊ አሠራርን ዘዴ ማወቅ፤ ለጥሩ
ወጤት ወሳኝ ነው። በኢትዮጵያ ትግላዊ ኪደት ላይም፤ ይህ

ያፈጻጸም ደረጃን ያለመጠበቅ ድክመት ተዘውትሮ ተንጸባርቋል። ለተፈጠረውም ቀውስ አንዱም ምክንያት ይኸው ድክመት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተዘፈዘፈበት የክስረት ዝቅጠት ውስጥ መውጣት አልቻለም። የዘመኑን ቀውስ ያባባሰው "ያለኔ የሚያውቅልህ የለም" በሚል ድፍረት ከሥልጣን ኮርቻ ላይ ተሳፍሮ፤ ከጥንት ጀምሮ በየጊዜው በግፍና በበደል አድራጊነቱ እያደገ የመጣው የወታደሮች መኰንናዊ አምባገነንነት ነው። ይኸው አድኃሪ ኃይል ላለፉት አሰራ አምስት ዓመታት በየዋሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈጸመውን መከራና ሽብር ሥቃይና እልቂት ተናግሮ መጨረስ አይቻልም። በሀገር ውስጥ የሚገኙ ደራስያን፤ ይህን ግፍና በደል ባጠገቡ ሆነው ማየት ቢችሉም፤ ባለባቸው ተጽዕኖ የተነሳ መዝግበው ሊያሳትሙት አይደፍሩም። የደፈሩ ቢኖሩም ከሕይወት መዝገብ ላይ ወዲያው ተፍቀዋል። የጨለማው ዘመን መንግሥት ባለሥልጣኖች፤ ደራስያንን በማጥፋት የሚፈጽሙት ግፍና ሙስና ተደብቆ የሚቀር ይመስላቸዋል። በሕዝቦች ላይ የሚፈጸም አስቀያሚ ግፍና በደል ግን እንደተናኘ ጭስ ሽንቁርና ቀዳዳ ፈልጎ ሰርስሮ መውጣቱ አይቀርም። በዚህ እትም ላይ የሰፈሩ ታሪኮች፤ የዚህ ሐቅ ክስተት ናቸው።

እነዚህ ቆናጽል ድርሳናት ( አጫጭር ልቦለዶች) በይዘት አቀራረባቸውና በመዋቅር ቅርጻቸው ፈጠራ ልቦለድ ይሁኑ እንጂ ጭብጥ ይዘታቸው ያለፈውን አሰራ አምስት የጨለመ ጠቋራ ዘመን ከነሰንኮፉ የሚያንፀባርቁ መስተዋቶች ናቸው። አጫጭር መሆናቸው ካላቸው ወርድና ስፋት መለጠጥ ሳይ





ችሉ ቀርቶ ሳይሆን፤ በየዘርፉ የተፈጸሙት በደሎች እጅግ ብዙ ስለሆኑ፤ ከየዓይነታቸው ለናሙና ያህል እየቈነጠሩ ለማቅረብ ታስቦ ነው።

እነዚህ ሚጢጢ ልቦለድ ታሪኮች፤ በከረረ አቀራረባቸውና ጥርንቅ ይዞታቸው፤ ባስራአምስቱ ዓመታት ውስጥ የተፈጸሙትን መራራ ቅጽበቶች ጥቂቶቹን ብቻ የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ በውሱን ቦታና ወቅት ላይ የተፈጸሙ አስቀያሚ ድርጊቶችን በማሳየት ረገድ ወደር የሚገኝላቸው አይደሉም። በተለይም የማኅበረ-ሰቡን የመከራ ገጠመኞች ማንፀባረቅ ብቻ ሳይሆን ባቀራረባቸው ረገድ እንዲያብለጨልጩና እንዲያጥበረብሩ ተደርገው የተዋቀሩ መሆናቸው ሆን ተብሎ ነው። የማጥበርበርና የማብለጭለጭ ባሕርይ ያለው ወስተዋት የተመልካችን ዓይን ይጣላል። ዓይኑ እንዳይቦዝበት የሚፈልግ ተመልካች ደግሞ ከብልጭልጩ አካል ዓይኑን ለመከላከልና ለማዳን ተገቢውን ዝግጅት ያደርጋል። ተራው መስተዋት ሁለንተናን እንዳለ ከነጕድፉ ጭምር የሚያሳይ ሲሆን፤ እነዚህኞቹ የማኅበረ-ሰባዊ ሕይወት መስተዋቶች ግን ከዚያም አልፈው ጕድፉን ብቻ በማሳየት ሳይወሰኑ፤ የጕድፉን ማስወገጃ ዘዴ ጭምር ይጠቍማሉ። ከሌሎች መሰል ያጫጭር ልቦለድ ታሪክ ድግሶች የሚለዩበት ቅመም ቢኖር፤ ይህ ባሕርያቸው ነው።

ታሪኮቹ በሙሉ የሚተርኩት ስለ ድኅረ የካቲት ኢትዮጵያ መቅሰፍት ሲሆን፤ እንዳጋጣሚ እኔ በዚህ ረገርም ዘመን ወቅት በአካል ኢትዮጵያ ውስጥ አለመኖሬ ግልጽ ነው። በአካል ካልነበረ " ምን አይቶ ከምን አግኝቶ እንዴትስ ሰምቶ ሊጽፈው ቻለ? " የሚሉ ተራቢዎች ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል። ለደቂቃም

በመንፈስ እንዳልተለየሁ ብናገር የሚያምኑኝ ባይሆኑም፣ ዛሬ ባለንበት ዘመን በአንድ የምድር ጥጋት ላይ ስላለች ሀገር ሁኔታ ለማወቅና ለመጻፍ ለሚፈልግ ሰው፣ ፍላጎቱ እስካለ ድረስ በአካል አገሪቱ ድረስ ሲጎተት መሔድ አይኖርበትም። ሁሉን ዜና ካለበት ሆኖ ማግኘት ይችላልና። ርቀት ተሸንፏል።

በእትሙ ውስጥ የሰፈሩ ታሪኮች ከፊሎቹ የልዩ ልዩ ሰንካላ ሐሳቦች ቀላጤዎች ሲሆኑ፣ ከፊሎቹ ደግሞ የሌላ ባሕርያት ወኪሎች ናቸው። ለማሳያ ያህል አልፎ አልፎ አንዳንዶቹን ላቅርብ።

" የሽሽግግር ደባ "—( ገጽ 65 ) የሚለው ታሪክ ትእምርታዊ ( ሲምቦሊክ ) የሆነ የወንዛ ወንዝ ታሪክ ይሟል፣ ይኳል፣ እንጂ እንደው በእንተ ወንዝ ሙላት ብቻ የተጻፈ ከቸሮና ደረቅ ሐቲት አይደለም። ሐቀኛ ትይታው ሦስትና አራት ነቍጦችን ያካትታል። ወንዝ፣ ማዕበል፣ ተሻጋሪ፣ አሻጋሪ። የአንድ ማኅበረ-ሰብ ሕዝብ የሚኻዝበት ሥርዓት ከርክሶ ሲቆም፣ በሆነው ዐይነት ዘዴ ወደ ታዳጊ አዲስ ማኅበረ- ሥር ዓት ለመለወጥ ሲሞክር፣ የሚያጋጥመውን የወርሐ ማዕዶት ሁኔታ የሚጠቁም ታሪክ ነው። እንደሚታወቀው ወንዝ ሲሞላ መቸገር ያለ ነው። ወንዙ ከሞላና ተሻጋሪውም ዋና የማይችል ከሆነ፣ አሻጋሪ ማስፈለጉ ያለና ግድም ነው። የዚህኛው ወንዝ ሙላት ግን ማዕበሉና ጎርፉ የተለመደ ቢሆንም፣ ያሻጋሪው ሰው ዓይነት ከወትሮ የተለየ ነው። የውሀ ማዕበል ገጥሞአቸው ተጨንቀው ለነበሩ የዋሃን መንገደኞች ምንም ዓይነት የሞራልና የዲስፕሊን ዝንባሌ አለማሳየቱ ብል ግና ነው። የዚህን ታሪክ ይዘት በዚህ ዓይነት ትንተና ጀምሮ፣





ከታሪኩም ተልእኮአዊ አድማስ ባሻግር የሚኖረውን ምናብ ማዘከሩ፣የአንባቢያን ጉዳይ ነው።

" .... አዋልደ ወንዴ "—( ገጽ 79 ) የእውነተኛ ታሪክ ሰምና ወርቅ ነው። በወይዘሮ ትምክሕተ የተመሰለች ኢትዮጵያ ከዕብደት ባላነሰ ደዌና ጭንቀት ተሠቃይታለች። ማናቸውም ነገር መነሻ ምክንያትና መድረሻ ውጤት እንዳለው ሁሉ፣ እናት ትምክሕተን ለዚያ ዓይነቱ የጭንቀት በሽታ የጣላቸው፣ ከማሕጸናቸው የወጡ የመንታ ልጆቻቸው እርስ በርስ መናቆር ነው። በባሕላቸው " ይቅርታን፣ ዕርቅን፣ ስሕተት መቀበልን.... " እንደሸንፈት የሚቆጥሩ መንታ ልጆቻቸው እርስ በርሳቸው ተጠፋፍተው እስኪያልቁ ድረስ በየጀመሩት አቋማቸው የጸኑ ይመስላል። እናት ትምክሕተን እየነጀሰ የሚያወፍፋቸውና የሚቀውሳቸው ይኸው የመንታ ልጆቻቸው እርቅ የለሽ አቋም ነው። ታሪኩ ባጭሩ ይህን እውነታ ያንጸባርቃል።

" ሞኝ ባገኝ "—( ገጽ 137 ) ይህ በአንድ ድኅረ የካቲት ወቅት የተከሰተ የበሽታ ዓይነት ስያሜ ነው። ወረርሽኝ። ያላንዳች ተቀዳሚ ጥናትና ያካባቢ ዝግጅት፣ ተራማጁን ለጋ ወጣት ካጠገ ባቸው ለማራቅ ብቻ ሲሉ ያቀዱት የገጠር ዘመቻና ያስከተ ለውን አሠቃቂ ውጤት ለማሳየት የተነደፈ ታሪክ ነው። በሽታው የተላላፊነት ባሕርይ ስለነበረው፣ ታመው በተመለሱ ዘማቾች አማካይነት አዲስ አበባ ሳይቀር ገብቶ ሕዝቡን አምሶት እንደነበር ይታወሳል። በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በህልሙ ያየውን ቅዠት ሁሉ፣ በአዋጅ እያስተላለፈ፣ የሕዝቡን ታዳጊ ልጆች አለምሕረት ይጨፈጭፍ እንደነበር አይዘነጋም። የዚህ ታሪክ ጭብጥ የሚያሳየው ደግሞ፣ የአዋጁ ተንኮል

ከተነቃበት በኋላ ግድያውን በስውር ለመቀጠል የተጠቀመበት ሌላው ዘዴ እንድነበር ነው።

" ዘሊባኖስ "–( ገጽ 203) ገና በወጣትነት ዕድሜው የማኅበረሰቡ አድኃሪ ሥርዓት በፈጠረበት ወንጀል ታስሮ፣ አበባ ዘመኑን ጀሀነም በሆነ እስር ቤት ውስጥ፣ የሚያማቅቅ አሳዛኝ ወጣት ሁኔታን የሚያጋልጥ ታሪክ ነው። ቦታው አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኝ ዓለም በቃኝ፣ ዘመኑ ድኅረ የካቲት ነው። ቀደም ሲል ራሴ ባይኔ ያየሁት አጋጣሚ ሲሆን፣ የዚያም እስር ቤት ጀሐነማዊ ሁኔታ እስከዚህችኛዋ ቀን ድረስ ያለምንም ለውጥና መሻሻል እንዳለ ነው። ዛሬማ እስረኛው ጢም ብሎ ሞልቶበታል ይሉ ኛል። እኔ ካገር ቤት ከወጣሁ ጀምሮ፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የዓለም አቀፍ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ተቋሞች ሁሉ (የተባበሩት መንግሥታት ፣ አምነስቲ ኢንተርናሺናል..... ) ስለ ዓለም በቃኝ እስር ቤት ሁኔታ ገልጬ፣ ከሥሩ ተመንግሎ እንዲደመሰስ ብዙ ሙከራዎች አድርጌ ነበር። ሙከራዩ ዋጋ እንዳላገኘ በተረዳሁ ጊዜ ነው፣ ባለጉዳዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ እስርቤቱ ውስጣዊ ይዘት እንዲያውቅ በማሰብ ይህን አጭር ታሪክ የጻፍኩት።፣..... ወዘተ.....

እንግዲህ እነዚህን ታሪኮች ለምን ራሳችሁ አታገላብጧቸውም። በወሲብ፣በሙስና፣ በጦርነት፣ በረሀብ....... የማቀቀች ሀገራችሁ፣ የሁላችሁንም ቆራጥ መስዋእትነት ትጠይቃለች። በርግጥ ካንጀታችሁ ካሰባችሁላት፣ ልትረዷት የምትችሉበት ብዙ መንገዶች አሉ። ቢቻል ተባብራችሁ፣ አለያም በየግላችሁ ልታደርጉ የምትችሉትን ከማድረግ ወደ ኋላ አትበሉ። ብዙዎቻችን የግለ-ሰቦችን መልካም ጥረት ስናካኪስና ስናቃልል






" አንድ ሰንበሌጥ ቢመዘዝ ቤት አያፈስም " እንላለን። ቁምነገሩ በእርግጥ " ከመምዘዙ" ላይ ከሆነ " አንዲት ራስ ክብሪት ተመዛ በመጫሯ አይደል፣ ሀገሩን ምድሩን ለኮሳ የምታቀጣጥል? " ሀገራችንን ራሳችን ልንረዳት ካልቻልን፣ በዓለም ዓቀፍ ወጃጅነት ስም ባዕዳን እየገቡ፣ ወገኖቻችንን እንዴት እንዳመሳቀሏቸው አይተናል፣ ተረድተናልም። የ " ሠመነ " " የተጣሰ አጥር " ........ የተባሉት ታሪኮች በዚህ እትም ውስጥ መሥፈራቸው ይህንን ጥሪ ለማጠንከር ነው።

በስደት ላይ ያለነው ወገኖች ብዙ ፈተናዎች እየገጠሙን ነው። ማንነታችንን ለማዘናጋትም አያሌ ውጥረቶች እየተፈታተኑን ነው። በእርግጥ የምፈራው የገጠሙን ውጥረቶች በየጊዜው እያደጉና እየከረሩ መጥተው " አባቱን ገድሎ ለአማቹ ይነጭ፣ አማቱን ጋርዶ እናቱን ያስፈጭ " የሚባለውን ብሂል እንዳያስተርቱብን ነው።

በተረፈ እነዚህ ታሪኮች እንደተኮማተሩ ላስቲኮች ዓይነት ናቸው። በወጠሯቸው መጠን መሳብ ይችላሉ። ለድርጊቱ ያንባብያንን ጡንቻ ይጋብዛሉ። ባጠቃላይም ማንኛውም አንባቢ እነዚህን ታሪኮች ካነበበ በኋላ፣ ወገኖቹ ኢትዮጵያውያን በተፈጸመባቸው በደሎች እጅግ ተሰምቶት እንድሚበግን አውቃለሁ። የታሪኮቹ በእንደዚህ ዓይነት መቅረብ ዓላማና ግብ ግን፣ አንባብያንን ለማብገን ሳይሆን፣ በያሉበት ሆነው፣ ለዚያ ምዝብርና ግፉዕ ሕዝብ፣ አንዳች መፍትሔ እንዲፈልጉለት በምሬት ለማሳሰብ ብቻ ነው። እንግዲህ ከሌሎች አዳዲስ እትሞቼ ጋር በቅርብ እስክንገናኝ ድረስ እስከዚያው በያላችሁበት ደኅና መሆንን አድርጉልኝ!!

ወንድማችሁ ( ገ.ነ. ብልጣሶር )

# የሽግግር ደባ!



ጐርፍን ተገን አርጎ፣ ዕቡይ ዋነተኛ፣
ጨዋ መስሎ ገብቶ ፣ ውስጠ-ተንኮለኛ፣

እችላለሁ ብሎ፣ ያሻጋሪ አታላይ!
አርክሶ አጣላ፣ ከኑሮ ሊያለያይ!

ይህ ዐይነቱስ ታንኪር፣ ደባ አይደለም ወይ?
በወርሀ-ማዕዶት፣ የበቀለ እንጉዳይ!

(የጠፍ. ቁ.2)

# መንደርደርያ

የሰው ልጅ የህይወት ጣቢያዎች ቁጥራቸው ብዙ ቢሆ ንም፣ ዓበይቶቹ ግን ሦስት ናቸው። ልደት፣ ሰርግ እና ሞት። እነዚህን አብዛኛው ሕዝባችን አምኖ የተቀበላቸው ሲሆኑ፣ በነ ባር ባህልነትም ሰንጠረዥ ላይ አስፍሯቸዋል። የዚህች ታሪክ ንድፈ ሐሳብ በሠርገኞች ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው። ሠርገ ኞች ለአዲስ ህይወት የተሰለፉ የረዥም ጉዳና ተጓዦች ናቸው። ዘመቻቸው ውጣ ውረድ ይኖርበታል። ገና ትኩስ የሥርዓተ-ጋብቻ ምልምሎች ቢሆኑ፣ ማሕበረ-ሰቡ ባላቸው ከፍተኛ ዓላማቸው መዝኖ ያከብራቸዋል። ያንድ ማህበረ-ሰብ አቢይ አቋማዊ ድርጅት የሚመሠረተው፣ ከትንሽቱ የቤሰ-ሰብ ሕዋስ ላይ በመጀመር ስለሆነ፣ አክብሮታቸው ምክንያታዊ ነው። ጤናማ ቤተ-ሰብ ከሌለ፣ ጤናማ ማሕበረ-ሰብ ሊኖር አይችልምና።

በዚህች አጭር ልቦለድ ታሪክ ውስጥ የቀረቡት ሙሽ ሮች ግን፣ ገና በጋብቻቸው ሰሞን ውስጥ፣ ባንድ ወቅት ላይ ፈተና ይገጥማቸዋል። የብሩህ ተስፋቸው ጉዳና ሦክና አሜካላ እንደሞላበት በዚሁ አጋጣሚ አሻግረው ለመመልከት ይረዳ ቸዋል። ቤሰ-ሰብ በመመሥረታቸው የተደሰቱ ዘመድ ወላጆቻ ቸው፣ ያገር ልምድ ነውና ቤት ማያ ድግስ ይጠሯቸዋል። አንዱ ጋር ደርሰው ወደ ሌላው ሲያመሩ ውሃ ይሉ የወንዝ ጐርፍ ያግዳቸዋል። ወሃው እስኪያንስ ወይም ጐርፉ እስኪ ሰክን መጠበቅ ቀጠሮ ማበላሸት ይሆንባቸዋል። እንዳይሻገሩ የወንዙ ሙላት ይጐለብትባቸዋል። በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ እን ዳሉ፣ ከዚህ መጣ የማይሉት " አሻጋሪ ነኝ ባይ " ዋነተኛ ከፊታ ቸው ከቸች ይላል። የታሪኩ መሠረተ ጭብጥ በዚሁ ሁኔታ ላይ ይጀምራል።

አራት ነቍጦችን ማስታወስ ያንባቢዎች ግዴታ ይሆናል። ተሻጋሪዎች፣ አሻጋሪ፣ ማዕበል ( ጐርፍ ) እና ባሻገር ( ማዶን ) ናቸው። እነዚህም የሐሳብ መሽከርከርያ ነጥቦች በነዚያ ሙሽ ሮች ሁኔታ ላይ የሚታዩ እውነታዊ ግኝቶች ይሁኑ እንጂ፣ በሥነ-ጽሑፍ ጥበባዊ አወቃቀር ላይ “ ተምሳሊት ” ይባላሉ። “ ስለዚህኛው ” የሚተርኩ መስለው ስለዚያኛው የሚያወሩ ናቸው። “ ስለዚህኛው ” ጸሐፊው ቢዘረዝም “ ስለዚያኛው ” ገንግኖ ማየት ያንባቢያኑ ፋንታ ነው። በትምህርተ-ሳይንስ የምና ውቀውን ያህል፣ በጸሐይ ጨረራዊ ኃይል፣ በገጸ-ምድር ላይ ተንጣልለው ያሉ “ውሀዎች” ሞቀውና ግለው በአየርነት ተነው ወደ ሕዋ ያርጋሉ። በሕዋ ላይ ተንሳፎ የሚገኝ ቁር በበኩሉ፣ ቢጋለ አየርነት በመትነን ሸሽቶ በሙጥኝታ የመጣውን አየር አቀዝቅዞ እንደገና ወደ ጥንተ ወሃነት በመቀየር በዝናምነት ወደመጣበት ምድራዊ ቤቱ ይሸኘዋል። ወሃ ሆኖ ሲሞቀው ይተናል፣ ሲቀዘቅዘውም ይዘንባል። አንዳንዴም የቁሩ ኃይልና ጉልበት ሲበዛበትና ሲጫነው በረዶ የሚሆንበት ወቅት አለው። ይህ እንግዲህ የውሃ የዝንተ ዓለም “ ዑደት ” መሆኑ ነው። ወዶ የሚያደርገው ሳይሆን ተገድዶ የሚፈጽመው ነው።

በዝናም መልክ የወረደ ወሃ ረባዳ ቦታዎችን ፈልጎ ወላጅ እናቶቹን ባሕራትና ውቃያኖሶች ለመቀላቀል በየሸለቆ እየ ተሽሎከለከ ይነጕዳል። የውሃውን ጉልበትና ብዛት የሚወስ ንለት፣ የዝናቡ መጠን ነው። ሙሽሮቹን ያጋጠማቸው የውሃ ጐዳና ( ወንዝ ) የዶፍ ዝናብ የወረደበት ወቅት በመሆኑ እጅግ ጐልብቶ ነው።

እንደሚታወቀው በሃገራችን በተለይም በገጠሩ ክፍል የወ ንዞችን ጉልበት የሚያግሩ ድልድዮች በብዛት የሉም። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ተጓዦችን በሥርዓት ለማሻገር ድልድይም





ለመሥራት ሆነ ጥበበኛ ዋነተኛን ለማሠልጠን በሚገባ አለ መታሰቡ ነው። እናውቃለን የሚሉ የሕዝብ ጥቅም አስከባሪ የሕዝብ ወገኖች በዚህ ተግባር ላይ በሚገባ አስበውበት አያው ቁም። ለማዘጋጀትም ያሰቡ ቢኖሩ፣ በሚሠራው የድልድይ ዓይነትና ያሻጋሪ ዋነተኛ ምንነት ላይ በሐሳብ ተስማምተው አያ ውቁም። ካንጀታቸው ያላሰቡበት በመሆኑ፣ የሚሠሩት ድል ድይ ተሽላልና ተልካሻ እየሆነ ዋነተኞቻቸውን አምቡጋርነት ስለ ሚያጠቃው ለመሻገር የመጡትን ብዙ ወገኖች ህይወት በከንቱ አስበልተዋል። አጅሬ ጐርፍ ግን ወቅቱን እየጠበቀ መምጣቱን አላቋረጠም። ድልድዮችን በማነጽ ረገድ አንዱ ባለዋህድ ዓምድ ይሁን ሲል ሌላው ደግሞ ባለመንታ ዋልቶች ያዋጣል ይላል። ያም ተባለ ይኸ እስካለንበት ዘመን ድረስ፣ በተለይም በገጠሩ አገራችን ውስጥ ወንዞች ሁሉ፣ እንበለ ድልድይ በመሆናቸው እየፏለሉ ተሻጋሪውን ሁሉ እንደዋጡ ይገኛሉ። ለተሻጋሪ ወገ ኖችም ምንም የበጀ ነገር አልተገኘም።

አንዳንዴም፣ መንደርና አምባ ያፈራው፣ ራሱን በራሱ፣ አሻጋሪ ዋነተኛ አድርጐ የሠየመ ኀረምሣ፣ እንዳሻው ሲምቦ ራጨቅ ይታያል።

እነዚህም ሙሽሮች ያጋጠማቸው አሻጋሪ ዋነተኛ ይኸው ዓይነት ነው። አካላዊ ሞያው እንኳ ከሞላ ጐደል ባላነሰው ነበር። የማሻገር ሙያ ግን አላካዊ ቅልጥፍና ብቻ አይደለም። ኀሊናንም ይጠይቃል፣ ሞራልም ይመለከታል። ምንም እንኳ ዋነተኛው በተገኘበት ያስተዳደግ አከባቢ ያን ያህል የማይጠበቅ ቢሆንም፣ ሰውን ያህል ክቡር ፍጡር ከበላተኛ ማዕበል አሻግሮ በማዳን፣ ከሚፈልገው ግቡ ለማድረስ፣ ካሻጋሪው ብዙ ነገር ይጠበቃል። ድርጊት ብቻውን አየር የወጠረው ስልቻ መሆን ነው። ትምህርት፣ ችሎታ፣ ከዛ በላይ ደግሞ ሞራል እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። በተለይም ተሻጋሪዎቹ ወገኖች በሰላም

እንዲያሻግራቸው ሙሉ እምነት የሚጥሉበት ስለሆነ፣ የተለየ ጥንቃቄና ጥበብ እንዲኖረው ግዴታ ነው። በተለይም በዛ ሕይወት አድን ተግባር ላይ የሚሰማራ ዋነተኛ፣ ከቅብጠትና ከእብሪት ከብልግናና ከግብዝነት ባጠቃላይም ከማን አለብኝ ባይነት አደገኛ ዝንባሌዎች ነፃ የሆነ ሰው መሆን አለበት። ያን ሁኔታ በመጠቀም፣ የራስን ግላዊ ስሜት ብቻ ከማርካት መቆጠብም ተገቢ ነው። ከሆነማ ከነጠላ አሻጋሪ ዋነተኛ ይልቅ፣ ማኅበረ-ሰቡ ተሰባብሶ የሚሠራው ድልድይ ወሳኝነት አለው። ለዘለቄታም አገልጋይ ሆኖ በየወቅቱ ተሚጎርፈውን ማዕበል ሁሉ በቍጥጥሩ ስር ሲያውል የሚችለው በብዙኃን አስተዋፅኦ ተዋቅሮ የሚሠራው ድልድይ ነው። ያም ድልድይ እስካለ ድረስ አንዳን ነጠላ ሞራለቢስ ዋነተኞች " እናሻግራችሁ " ብለው ከማጭበርበር ይታቀቡም ነበር። የተባለው ድልድይም ታንጾ ግልጋሎት መስጠት እስካልቻለ ድረስ እነዛ ሙሽሮች ያበሳጫቸው ዓይነት ኩታራ ዋነተኛ፣ ወንዞች በሞሉ ቍጥር ብቅ እያለ ፣ ማበሳጨቱን ምንጊዜም አይተውም.......

በዚህች አጭር ልቦለድ ታሪክ ውስጥ አንባቢያን ሊያተኩሩበት የሚገባቸው የመደምደምያ ነጥብ አለ። ይኸውም ከባለጌው አሻጋሪ ዋነተኛ ቅጽበታዊ ርካታ በኋላ፣ በፍራቻና በመርበርበድ፣ ሙሺሪትን ከማጾ ላይ ጥሏት ሲሄድ፣ ጅምሩ ታሪክ እንዲያበቃ የተደረገበት ጭብጣዊ መዋቅር ጉዳይ ነው። እንዲያውም ማለቢያው ቃል " ውሻማ " ቃል እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት ሁሉ አለ። እኔ ብጥልጥሉን እያወጣሁ ከምተነትነው ይልቅ፣ ለምን አንባቢዬ ራስዎ በግል አመለካከትዎ እንዲያጣጥሙት አላደርግም? ምናባቱስ ቆርጦኝ ነው፣ እንደ ፈለጉ የማየት ነጻነትዎንስ የምደፍረው!! ስለዚህ ከማሰብ ነፃነትዎ ጋር ታሪኪቱ ይቻትልዎ።

# የሽግግር ደባ!

ወቅቱ ወርሃ ክረምት ነው። ሁለት ሙሽሮች ከወንዝ ዳር ተቃቅፈው ቆመዋል። ሠርጋቸው የተፈፀመው ከጥቂት ወራት በፊት፣ በፋሲካው ሰሞን ነበር። የሙሽርነታቸው እንቡጥ አበባ ገና አልጠወለገም። በአፍላ ነዲድ ፍቅራቸው ላይ ነበሩ።

" አይራራ " የሚባለው ወንዝ ከአንኮበር ገመገም ሥር የሚፍለቀለቅ ታላቅ ዠማ ነው። ይህን መሳይ አስፈሪ ስሙን ያገኘው፣ ከዘመናት በፊት በፈጸመው ግፍ ምክንያት ነው። እናት አንድ ልጇን አዝላ ስትሻገር፣ ልጁን ብቻ አስቀርቶ እናትን ነጥሎ በመውሰዱ ነው። " አይራራ " የስንክሳርን አጠቃላይ ገጾች ሊያስለቅቅ የሚችል ሰፊ የበደል ታሪክ አለው። ልሻገርህ የሚለውን ደካማ ሁሉ ያለምሕረት ሲበላ ኖሯል።

የጫጉላ ወቅታቸውን ያላገባደዱት እሊያ አዲስ ሙሽሮች፣ ከሙሽሪት አጐቶች ባንደኛው ቤት፣ የመልስ ድግስ ላይ ውለው አድረው ወደ ሠፈራቸው በመመለስ ላይ ነበሩ። ሠፈራቸው ለመድረስ " አይራራን" መሻገር ነበረባቸው። ከድግሱ ያጐት ቤት የስድስት ሰዓት ያህል ጐዳና ተጉዘዋል። " አይራራን " ተሻግረው፣ ከሠፈራቸው ለመድረስ ያን ያህል ጊዜ ይቀራቸዋል። አጅሬ " አይራራ " ጉሽ ጠላ የመሰለ ዝናቡን ጠጥቶ፣ ጥምብዝ ብሎ ሰክሮ ባየር ላይ ይጨፍራል። አለወትሮው እስከአፍጢሙ ሞልቶ ድንበሩን ለቆ በመውጣት፣

የራሱን ጎዳጎች ያስሳል። ከደጋው ላይ ጀምሮ እያጋበሰ ሲወጥ ያመጣውንም ደለል በየዳርቻው ይተፋል። አዲሶቹ ሙሽሮች፣ ያቅማቸውን ያህል ዋና ቢችሉም፣ ያን "የአይ ራራ" ጎርፉማ ሙላት የሚሞክሩት አልነበረም። ያላቸው ምርጫ፣ ተግባራቸው ማሻገር የሆነ፣ በዋና የተካኑ ባለሙ ያዎችን ማግኘት ነበር። እንደዚህ ያሉ ባለሙያዎችም፣ ሥራዬ ብለው ከዠማው ዳርቻ አይታጡም ነበር። በዛ ወቅት ግን አንድም አልነበረም።

ሠርገኞቹ "ምን እናድርግ?" እያሉ በየርከኑ ዳር ዳር ሲያመነቱ፣ አንድ ከባቱ ዶልዶም፣ ከደረቱ ገምደል፣ ያለ ጠብደል ጎረምሳ፣ ከዚህ መጣ ሳይባል ከወደኋላቸው ድንገት ከቸች ይላል። ጠይምነቱ ቆለኛነቱን ያሳጣበታል። ንዳድ ያጋ የው ጸጉሩና መልኩ ከጸሓይቱ መጐራበቱን ይመሰክራሉ። የሚናገረው ቃል ካንደበቱ ሲወጣ ይተናነቀዋል። ሲቅለሰለስ ደግሞ ትሕትና ያለው ገር ይመስላል። አካሔዱ ከምበል ደፋ ያለ ምታዊ ቅኝት አለው። አለባበሱ እንደነገሩ ነው።

"እንዴት ዋላችሁ! ድልድይ የምትቃኙ ይመስላል" አላቸው።

"ቢገኝማ ማን አርጎት! በዚህ ድብልቅልቅ ውስጥ" አለ ሙሽራው፣ የጐረምሳው ጠብደልነት እየቀፈፈው። ሙሽራይቱ ግን የጐረምሳውን የሚገረምም አስተያየቱንና የፈ ረጠመ ሰውነቱን አልወደደችውምና፣ አረመመች። ጐረም ሳው ለተግባር የመጣ ነበርና "ስንት ትከፍላላችሁ?" ሲል ጠየቀ፣ የጀጠባቡን እጀታ እየጠቀለለና ተነፋነፍ ሱሪውን ወደ ላይ እየሰቀሰቀ። ሙሽሪት ቀደም ብላ "የደንቡን ነዋ!" አለች። ጐረምሳውም ቀበል አድርጎ "ዛሬ ጅረቱ ተጋፊ ነውና እጥፍ መክፈል አለባችሁ!" አለ።

እንደ መከንከን የጀማመረው ሙሽራ "እጥፉ ስንት ይሆናል?" ሲል ጠየቀ፣ ወንዝወንዙን አሻግሮ እያየ። "ሁለት ሁለት አላድ በየራስ" አለው ጐረምሳው የሙሽሪትን እግሮች አሻግሮ እየመተረ። "ደግሞም ….. " አለ ጐረ ምሳው። "ሁለት ጊዜ ሳይሆን አራት ጊዜ መመላለስ እንዳለብኝ አትዘንጉ"

ይህን እንደተናገረ ሙሽራው ብርክ ያዘውና አቈዘመ። እጅግ ተጨንቆም ያሰላስ ጀመር አቀርቅሮ። በሓሳቡም ውስጥ ያብሰከሰከው "እሷን አስቀድሞ ቢያሻግር፣ ማዶ ላይ ብቻዋን ያገኛታል። እኔን አስቀድሞ ቢያሻግር አድርሶኝ ሲመለስ፣ ብቻዋን ሊያገኛት ነው።….. " የሚለው ሓሳብ ነው። ጐረምሳውም አቅበጠበጠውና፣ "ቶሎ ወስኑ! አሲያ ዛሬ 'አይራራ' እያበጠና የባሰ እየገነፈለ ነው የሚመጣው! ከወዲያ ባሻገር የሚጥለውን ዝናም አታዩም?" አለና አሻግሮ ማዶውን በጣቱ እየጠቆመ አሳያቸው፣ የዝና ቡምን መምጣት። ጉዳዩ ያሰጋው ሙሽራ ግን፣ የመሽጋገሩን የተናጠል ሁኔታ እያወጣና እያወረደ "ወንድሜ አትቸኩል! የቸኰለ አፍስሶ ለቀመ ሲሉ አልሰማህም!" አለውና በኀሊና ተመስጦ "የሚበጀው ሁለታችንንም ባንዴ ማሻገሩ ይሆናል!" አለና ዋነተኛውን! ጠየቀው።

ጐረምሳውም ወዲያው "ይህ የማይሞከር ነው። እንኳን ዛሬ 'አይራራ' ከመጠን በላይ ሞልቶ ሲጨፍር ይቅ ርና በሌላውም ጊዜ ቢሆን የሚቻል አይደለም" ሲል መለሰ።

" እንግዲያውስ " አለና ሙሽራው የሚያዋጣውን
የሽግግር መላ ያሰላ ገባ። " የሚበጀው እሷን አስቀድሞ ቢያ
ሻግር ይሆናል። ምክንያቱም የሱ ቤትና የሚከፈለውም ገን
ዘብ፣ ከወዲህኛው ማዶ ስለሚቀር፣ ለሁለቱ ጥቅሞቹ ሲል
እሷን አሻግሮ ካደረሳት በኋላ ፈጥኖ መመለሱ አይቀርም "
በሚለው ሐሳብ ወሰነ። ይህን አስቸጋሪ ውሳኔ ለማድረግ
በሓሳብ ተውጦ በሚያውጠነጥንበት ወቅት፣ ፈንጠር ብሎ
ቆሞ የነበረው ዋነተኛ ጐረምሳ፣ ሙሽሪትን ደህና አድርጎ
በጠብደል ዓይኖቹ እያገላበጠ መተራት። የሱ አለመሆኗ
ቆጭው።

ውበቷ " መች ተሻግራልኝ!" እያሰኘ አስቋመጠው።
በሩቁ የሚፈነጠቀው ደም ግባቷ አቍነጠነጠው። በርግጥም
ሙሽሪት ውብ ነበረች። ሙሽሪት ሐማራዊ ገርዳሳ በተጐነ
ጐነው ሐርማ ፀጉሯ ዳርዳር ላይ፣ ሽብ አርጋለች። በጥልፍ
ተሸለምልሞ የቀበጠው ቀሚሷ፣ ያቡነ ሰማላን መስቀል ከደ
ረቷ በስተርግርጌ ላይ  አስፍኗል። በአልቦ ምትክ በእግሮቿ
ላይ የተነቀሰችው ጠልሰም፣ የተመልካቹን ኅሊና ይማታል።
የበስተጀርባዋ መለያልይ ቅርፂ፣ ስሜት አልባውን ሳይቀር ይነ
ዝራል። ከአንገቷ በስተግርጌ ያንቀላፋው የብር መስቀሏ፣ ክር
ስቶስን ሳይሆን ፍቅረኛን የቸነከረ ይመስላል። ከድግስ ቤት
መመለሷ ቢሆንም፣ መቀነቷን ያገለደመችበት ሆዷ፣ እህል የገ
ባበትም አይመስልም። የወገቧ ቅጥነት ችቦ አይሞላም። ከመ
ከዳው ደረቷ ላይ እንደፈርጥ ጉብጉብ ያሉት ዕቶን መሳይ
ጡቶቿ፣ ልጇን ባረገኝ ያሰኛሉ። እንደ ቀዘባ ዘንባባ ዘንጠፍ
ያለው ዳሌዋ፣ ዐይነማዝ ደዌ ያለበት  ሁሉ፣ ገና በሩቁ ሲያ





የው ይፈወሳል!! ስለ ገፅታ ብሰው፣ ዋ ላይሀ፣ ስለ ዐይኖቿ፣
ስለአፍንጫዋ....... መናገር፣ ቋንቋ ማበላሸት ይሆናል። .....
ዝም ነው። የቃላት አፅናፍም እንኳ አይሸፍነውምና ነው!!

ያ አዲስ ሙሽራ ባሏ፣ አቆዝሞ ሲያሰላስል ከቆየ
በኋላ " አጐትሽ ቤት እንደገና ተመልሰን፣ 'አይራራ' ሲጐ
ድል ነገ ብንመለስ ይሻላል.." ሲል ሚስቱን አማከረ። " ረሳ
ኸው እንዴ! ለምን ቸኩለን መጣንና ነው! ያቺ አክስቴ
ደግሳ ብንቀርባት ትቃጠላለች! ሰዎች አታደርገንም! ማታ
መገኘት  እንዳለብን  አስጠንቅቃናለች  አይደል? " አለች
አበከራ!!

" እሱስ እውነትሽን ነው! ለቤት ማያው ድግስ የሚ
መጡ እንግዶችና ቤተ-ዘመድ ሁሉ፣ ባንደርሳላቸው ሊያስቡና
ሊደነግጡ ይችላሉ። ደግሞም በጉን የምታርደው አንተ ነህ
ብላለችና አክስትሽ፣ መቅረትስ  የለብንም....." አለ እያቅማማ።

ጐረምሣው ዋነተኛ፣ ንግግራቸውን ሲሰማ ቆይቶ እየ
ተቆናጠረ፣ " የምታመነቱ ከሆነ፣ እኔ ሌላጋ እሔዳለሁ። በየ
እርከኑ ሁሉ አሻጋሪ ዋነተኛ የሚፈልግ ሰው ሞልቷል!!
ዕድሜ ' ላይራራ' ! እንጅ፣ ጠሜን እንደሁ አላድርም! "
በማለት ተናገረ።

" በቃ ወስነናል። አራቱን አላድ መጨረሻ ላይ
እንከፍልሃለን! በል፣ ባለቤቴን መጀመሪያ አሻግራት " አለ
ስለዋነተኛው ባሕሪ እየተጠራጠረና...... ሲፈራ ሲቸር። ከላይ
የሚለበሰውን ዋናውን ልብስ በማንጠልጠያ በትሩ ላይ
አደረገችና፣ ያቺን ጠምበለል መሳይ ልጅ፣ ከባሏ ነጥሎ
ይዟት ወደ " አይራራ " ኸረት ገባ።  ገና ከዳርቻው ላይ


" አይዞሽ አትፍሪ! " ብሎ እየዳሰሰ ሲይዛት ሁኔታውን ማየቱ ባሏ አስጠልቶት ዐይኖቹን ጨፈነ። ዋነተኛው ጉረምሣ ሆዬ ግን፣ በግላጭ ያገኘውን የትኩስ ሙሽሪት ሚሜይ ይዞና በቀጥጥሩ ስርም ያዋለውን ውብ ገላዋን እየዳሰሰ፣ ' ያይራራን ' ጉርፍ ሠነጠቀው። በተቀዳሚም ያሻሽ የገባው እንዚያን የተመኛቸውን የደደሩ አጐጠጐጤ ጡቶቿን ነበር። ከቾረቱ ዳርቻ እስኪደርስም ድረስ፣ ጠቅላላ አካሏን ሲዳስስ ምኗም ምኗም አልቀረው። ከዳርቻው እርከን እስኪደርስም ድረስ እጅግ ተንሰፈሰፈ። በሞቀው ውሃ ውስጥ፣ የጋለው ሰውነቷ ሙቀቱ ስለገላመጠው፣ በፍትወት ጣመነ። ከወዲያኛው ማዶ በልዩ ፍጥነቱ አንጠልጥሏት እንደደረሰ፣ በውሃ ከራሰው ቀሚሷ ውስጥ ደብቃ ካጉቷ ድግስ ይዛ ያመጣችውን ድፎ ዳቦ፣ ይቦጠቡጠው ገባ።.......

ጊዜው የቀትር በስቲያ በመሆኑ፣ ማዶ ለማዶ ያለ፣ ሁሉ ነገር ወለል ብሎ ይታያል። ባል ሆዬ፣ ከወዲያኛው ማዶ ብቻውን ሆኖ፣ ጉሮሮው ሊያወጣው የሚችለውን ድምፅ ያህል፣ በማውገዝ ጮኸ! ኰነነ! ረገመ! ሊሻገርም ከጅሎት፣ ' አይራራ ' ጉልብቶበት፣ ባቱን እያጠፈ የሚያስተናግደው ሆነ። ከነበረበት ማዶ አንዲት ዲብ ላይ ተቀምጦ፣ እንደ ሕፃን ልጅ እዬዬውን ያቀልጥ ጀመር። ሰውነቱን፣ የማዶው ድርጊት ትይታ ወረረው። ያሚያየው ሁሉ ቅዥት መሰለው። ዋነተኛው ጉረምሣ፣ የዳቦውን እንቡጥ እንቡጥ ከኰመኰመ በኋላ፣ እንደመጥገብና እንደመርካት ሲሞክረው፣ ያን ባሏን እየጮኸ ጠራውና " ስማ! ገንዘብህን አልፈልግም! ድግሱ ቤት ከበላኸው ዳቦ ትራፊ አግኝቼ፣ እስክጠግብ ከስክሻለሁ።






ባለቤትህን ያሻገርኩበት ዋጋም ሆኖልኛል፣ ደህና ክረም !...." አለና፣ የመሠናበቻ ምልክት አሳይቶት፣ ሙሽራዋን ከነልቅሶዋ ጥሎለት፣ ወደ እሚሔድበት እየዘፈነ ነጐደ። ሁለቱም ሙሽሮች በያሉበት ማዶ ላይ ሆነው፣ ሲያለቅሱ ከቆዩ በኋላ፣ ቀኑ እየመሸ በሔደ መጠን፣ " አይራራም " ይጐድል ጀመር። ብዙም አልቆየ፣ " አይራራ ሙላትህ ይበቃሃል " ያሉት ይመስል፣ ማምሻው ላይ ባፋጣኝ ጐደለ። ወዲያው ማዶ ላይ የነበረው ባሏ፣ ከነእልሁ ዘሎ ወንዙ ውስጥ ገባና፣ በንዴት ፈረሱ ውሃውን እየጋለበ፣ ተጨብጣ ከምታለቅስ ሚስቱ ዘንድ ደረሰ። " ያሁኑ ይባስ! " እንዲሉ፣ እንደደረሰ፣ ቢያዘው ቆመጡ፣ እያገላበጠ ይጠልዛት ጀመር። ሚስቱም " ምን ላድርግ? አቅም የለኝም! እሱ መረመንድ ግንድ ያህላል! እንዴት ችየ ራሴን ልከላከል ብለህ ነው? " ብላ በልቅሶዋና በዱላው ጣልቃ ነገረችው። ባልዬውም " እሱስ ውነትሽን ነው። እኔንስ ይበልጥ ያናደደኝና ያበሸቀኝ " ስታሸረግጂ ለት " ማየቴ ነው!" አላት።



አንዳንድ ጮሌ ለጋም፣ላሻግርም ቢል፣ራሱን ብቻ አሻገረ እንጅ፣ ሌሎችን አላሻገረም!


# አዋልደ ወንዴ



ያመጣሽው ጠርሙስ፣ አረቄ ነው ብለሽ፣

ኦዶኮሎኝ ሆነ፣ትምክሕተ ምን ነካሽ?

(የጠፍ.ቁ.3)



"ከሁሉም ከሁሉም፣ ካየሁት በደሌ፣
እንደ ሬት መራራው፣ለኔና ለባሌ፣
ከውርሱም በኋላ፣ብድሩን መክፈሌ!"

(ትምክሕተ)

# መንደርደርያ

አንድ ኅብረተ ሰብ ባላሰበውና ባልጠበቀው ዓይነት፣ ከአንድ መራራ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና፣ የሶሻል ቀውስና ክስረት ውስጥ ድንገት በተዘፈቀ ጊዜ፣ በግለሰቦችም ሆነ በማኅበረ ሰቡ ላይ ብዙ አሳዛኝና አስቀያሚ ድርጊቶች ይፈጸማሉ። በመንታ ትውልዶች ያስተሰሰብ ግጭት አንጻር፣ ወላጅን ከተወላጅ፣ ወንድምን ከወንድም፣ ወንድን ከሴት፣ ከተሜን ከገጠሬ፣ በአእምሮ አዳሪውን ከጉልበት አዳሪው፣ ........ ያጋጫል፣ ያናቁራል፣ ያናችፋል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ፣ አንድ ዓይነት ማኅበረ ሰብ ፣ በነባር የለውጥ ሕግ ተገድዶ፣ ወደ አዲስ ማኅበረ-ሰብነት ሲለወጥ የሚያጋጥም፣ የሰው ልጆች በሚኖሩበት አካባቢ ሁሉ፣ ሲመጣ ሲሔድ፣ ሲወጣ ሲገባ፣ ሲያረጅ ሲተካ፣ ሲዘቅጥ ሲለወጥ፣ በየዘመኑና በየወቅቱ የሚከናወን ቀዋሚ ክስተት ነው።

የለውጡን ሁኔታና ኪደት፣ ይዘትና ቅርፅ፣ የሚወስኑት ምክንያቶች፣ አካባቢና ዘመን፣ የማኅበረሰቡ የንቃት ደረጃና ያደረጃጀት መዋቅር፣ የትዝምደ-ምርትና አምጻኤ-ምርት፣... ዓይነተኞቹ ሲሆኑ፣ ያለፈው ትውልድ ያስተሳሰብ ቅርስና ይጠቀምበት የነበረው የታዳጊ ሕፃናት ያስተዳደግ ሥርዓት በየበኩላቸው ለሚፈጠረው ለውጥ አስተዋፅኦ አላቸው። ያን ዘመነ-ማዕዶት ( የሽግግር ዘመን) በሚገባ ለማስተናገድ ያልተዘጋጀ ሕዝብ፣ አቤት የሚደርስበት ፍዳ!

በዚች ቊንጽል ታሪክ ውስጥ ይህ እውነታ ከድሕረ የካቲት ወዲህ በሰፊው ማኅበረ-ሰብ ውስጥ ቀርቶ፣ በትንሽዋ አንድ ቤተ-ሰብ ውስጥ እንኳ፣ እንዴት እንደተንጸባረቀ ያሳ

ያል ። የወንድማማቾቹና የወላጆቻቸው ታሪክ የነበረና ያለ እውነታም እንኳ ቢሆንም፣ ጭብጣዊ የታሪኩ ይዘት በሕይወት ያሉ ሕያዋንን ጭምር በተምሳሌት ከመጠቀሙ በስተቀር፣ ማንንም አይመለከትም ። በሥነ-ጽሑፍ ታሪካዊ ኪደት ውስጥ፣ ብዙ ጊዜ ተዘውትሮ እንደታየው፣ አንዱ ደራሲ ካምቻትካ ተቀምጦ የጻፈው ድርሰት፣ ከነሙሉ ባሕርያቱ ጋር ሌላ ደራሲ አላስካ ተቀምጦ ከጻፈው ታሪካዊ ይዘት ጋር ያለ ነገር አባትና ያለ ጥሎሽ፣ ያለ አማጭና ረማጭ ተጋብቶ ይገኛል ። ፈረንጆቹ ይህን መሰል አጋጣሚ " ኮኢንስደንስ " ይሉታል ። " ተአምራዊ ጥምረት ወይም ሳይገናኙና ሳይተያዩ ተመሳስሎ በመስተጻምርነት መዋሐድ " እንደማለት ነው ። እንደዚህም ሁሉ በዚህ ቊንጽል ድርሳን ውስጥ ሰፍረው የሚገኙ ባሕርያት በሙሉ የኮኢንሲደንስ አጋጣሚ ካልሆነ በስ ተቀር፣ " እኔን ይሆናል " የሚለውን ባይ ሁሉ በጭራሽ አይመለከትም ። የኢትዮጵያ ድሕረ-የካቲት ኰድኵዶ ካስወለደው የቀውስ ዱብ ዕዳዎች ውስጥ አንዱ ክሥተት እንደሆነ ግን ሁላችንም እንደምንገነዘበው አምናለሁ ። ያንድ ቤተሰብ ልጆች የርስ በርስ መከሳከስ፣ የወላጆቻቸውን ጤንነት እንዳቃወሰው፣ በዚህች አጭር ታሪክ አማካይነት ለማሳየት መሞከሬ፣ የደረሰብን ቀውስና ክስረት ምን ያህል የሚጐመዝዝ መራራ ሠፍንግ መሆኑን እንደሚያስረዳልኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። ከዚህ አስተሳሰብ ክልል ውጭ ግን የሚሠነዘር ሌላ ትርጉም ቢኖር፣ ትርጁማኑን እንጅ እኔን አይመለከትም ።



# " አዋልደ—ወንዴ "

" .... መከረኛ፣ እናት፣ መንታ ልጆች ወልዳ፣
አንዱ፣ ሳት፣ ሌላው ማይ፣ ፅሩራን ዱብ ዕዳ፣
ወግ ደርሷት፣ ሳትጦር፣ ባልሠራችው ፍዳ፣
ሳትኖር፣ ልትሞት፣ ነው፣ ሕይወት ሆኗት፣ ባዳ......"

.......ያለችበት ማኅበረ ሰብ ያወጣለት ሥያሜ " እናት " ነው ። እንስፍስፏ እናት-እምዬ ። ስምነቱ የወል ስም ይሁን እንጅ፣ የትኛዋም እናት እንደ ግል የተፀውኦ ስሟ ታየዋለች ። ስምነቱ፣ የመጀመሪያዋ ሴት በወላጅነት እስከታወቀችበት ወቅት ነበረ፣ አለ፣ ይኖራልም ። በዘመናት መካከል ሲንፏፏ የሚኖረውን የትውልድ ዡማ ያስገኘችና የምታስገኝ ምንጭ በመሆኗ፣ በየትኛውም ሕዝብ፣ በማናቸውም ሀገር እንደ ተከበረች ትኖራለች ። ለፈፀመችው የተፈጥሮ ሙያዋ፣ ይህ የክብር ስጦታ ቢያንሳት እንጅ አይበዛባትም ። ስለዚህም ውለታዋ በሕይወቷ እስ ካለች ድረስ በሰላም፣ በደስታ፣ በምቾት፣ ለመኖር፣ ከሌላው እንኳ ቢቀር፣ የማህፀኗ ፍሬዎች ከሆኑት ልጆቿ የምትጠብቀው ተራ ወሮታ ነው ።

በምንኖርበት ሥርዓት ባሕርይ ድክመት የተነሳ ብዙዎች ነገሮች እንደሚጠበቁት ሆነው አይገኙም ። በዚህ ላይ ደግሞ የጥቂቶች ሰዎች የግብዝነት ጠባይ ሲበረዝበት፣ የባሰውን መራራ ሁኔታዎችን ያሳያሉ ። በዘመናችን እንዲህ ያሉ ጐምዛዛ ድርጊቶች፣ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ጐልተው ይገኛሉ ።

እንደሚታመንበት ሁሉ፣ ሕገ-ተፈጥሮ የራሱ መመሪ

ያዎች አሉት ። በዚህም መሠረት ፀሐያችን ሙቀቷንና ፀዳሏን
ከመስጠት አልተቈጠበችም ። በዚህም ዕለታት ይነጋሉ፣ ይመ
ሻሉ ። ዕፀዋት ያብባሉ፣ ያፈራሉ ። ክረምትና በጋ ይፈራ
ረቃሉ ። ነፋሳት በዘፈቀደ አይነፍሱም ። የመንገደ ምዕራብ
ስምሪቱ፣ የራሱ ሕገ-አመንክዮ አለው ። የስግረቱ መፍጠንና
መዘግየት፣ የራሱ የሆነ መርሖ አለው ። ማያት ይፈሳሉ ። ካል
ተገደዱ በስተቀር፣ ፍሰታቸው የተዋረድ ቍልቁሊት ነው ።
ከሾረት በላይ የሚጠጣን ኸብ፣ ከበታቹ የምትጠጣውን አህያ
አደፈረሸብኝ ማለት አያስችልም ።.... ዓለም ከነተፈጥሮዎቿ
በጤነኛ ኪደት ላይ ትገኛለች ። የሚያንገዳግዷት እንከኖቿ ግን
ጥቂት አይደሉም ። አመንጭዎችም ኢሰዎች ናቸው!!

ከሚኖሩባት ደመ ነፍስ ፍጡራን ሁሉ፣ ሰው የተባ
ለው፣ ዓለምን እንደነጀሳት አለ ። የሚበላውን ከሚኰሳባትና
የሚጠጣውን ከሚሸናባት አልፎ፣ በሠራው መርዙ እየመረዛት
ነው ። የተነሰነሰባት፣ መርዝም፣ ሲጠዘጥዛትና ሲመዘምዛት
ቆይቷል ። የሰዎች ዓለምን መድፈርና ማስቸገር፣ ከራሳቸው
የእርስ በርስ ግጭት የተፈጠረ ነው ። ፍልስፍናቸው እርስ
በርስ ይፋጫል ። አንዱ ክፍል፣ የሰዎች መሠረት፣ " ግለ
-ሰብ! " ነው ብሎ ሲያስተምር ሌላው ደግሞ "ቤተ-ሰብ "
ነው እያለ ያስተምራል ። የቀረው ክፍል ደግሞ፣ ጠቅላላው
" ኅብረተ-ሰብ " ነው ብሎ ይሠብካል ። በዚህ በተሣከረ አስተ
ሳሰብ ውስጥ ጮሌዎች ይጠቀማሉ፣ የዋሀን ይጐዳሉ ።
የመንታ ፅንፍ አባሎች በተቆራቆሱ መጠን፣ ዳፋቸውና ጦሳ
ቸው ሌላውን ገር ክፍል እንደረበሸ ነው ። ፅንፋውያን ግን፣
ምንጊዜም " ፕሪንስፕል ያድናል፣ ፕሪንስፕል ይገላል "
ይላሉ ። የነሱ ዓላማ ግብ እስኪመታ ድረስ፣ ዓለም የሆነች





ውን ብትሆን፣ ደንታ የላቸውም ። የነሱ ምኞት ይፈፀም
እንጅ፣ አረጋውያን ወላጆቻቸው፣ የዋሁ ሕዝባቸው፣ ጤዛ
ቢልስ፣ አፈር ቢምስ፣ ደንታቸው አይደለም ። የነሱ የራሳ
ቸው ሐሳብ ብቻ የነጠረ፣ የጠራ፣ ይመስላቸዋል ። የሌላ
ውን፣ በፈለገው ዐይነት በቂ አሳማኝ ማሳረጃ ቢቀርብም፣
ይሞታሉ እንጂ አይቀበሉም ። ይህ ግትርነታቸው፣ የገመዱት
ይመስል፣ እየከረረ ይወጠራል ። ጦዞ በሚወጠርበት፣ ደረጃ
ሲደርስ፣ ዐይነ ኅሊናቸው ጨርሶ ይታወራል ። በዚያን ወቅት
የሚሠሩት ሁሉ አይታወቃቸውም ። የሚፈስ የሰው ደም፣
ተራ ውሃ ይመስላቸዋል ።

ለእንደዚህ ያሉ ልጆች እናት የሆኑ፣ አንድ እመቤት
አዲስ አበባ ይኖራሉ ። ስማቸው ወይዘሮ ትምክሕተ ይባላል ።
ተጀምሮ እስኪጨረስ ያዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው ። ወይዘሮ
ትምክሕተ በኖሩበት ማኅበረ-ሰብ ሥርዓት መሠረት እኩያ
ቸውን በቁርባን ተድረው ረዥም ጊዜ ኖረዋል ። በሕገ-ተፈ
ጥሮ፣ ሥርዓትም፣ ልጆች፣ ወልደው፣ አሳድገዋል ። ባለቤታ
ቸው ባላምባራስ ወንዴ ይባላሉ ። በዕድሜ ከወይዘሮ ትምክ
ሕተ ጋር ብዙ አይበላለጡም ። ንብረታቸው የደራ፣ ትዳራ
ቸው የሞቀ ነበር ። በዚያ የረጅም ዘመን የትዳር ዘመናቸው፣
አንድ ጊዜ ብቻ መንታ ወንዶች ወልደው ነበር ። ይህም የሆ
ነው የጣልያን ወረራ ካከተመ በኋላ ነው ። በስለት፣ በስተኋላ
የተገኙ ልጆች ነበሩ ። " ወንዴ ወንድ ወለደ " የሚል ዘፈን
አስፈልስፈው፣ ወራት አዘፍነዋል ።

እሊህ መንታ ልጆቻቸው፣ ለወይዘሮ ትምክሕተና ባላ
ምባራስ ወንዴ የሕይወታቸውን ያህል የሚያስቡላቸው፣
ምትክ የማይገኝላቸው፣ ቅርሳቸው ነበሩ ። ያከባቢያቸው ሥል

ጣኔና ባሕል የፈቀደላቸውን ያህል፣ በሚገባ አሳድገዋቸዋል ። 
እጅግ ስለሚሳሱላቸው፣ አንዳንዴ በጣም ያሞላቅቋቸው ነበ
ር ። በተለይም፣ የማቆላመጫ ስም ሰጥተው ከዋና ስማቸው
ይልቅ በዚሁ ስማቸው እንዲጠሩ አርገዋል ። እንደ ውልደ
ታቸው ቅደም ተከተል “ መሩ ” እና “ መራ ” ይባሉ
ነበር ። ትምህርት ቤት ውለው እስኪመጡ ድረስ ወላጆ
ቻቸው ልባቸው ተሰቅሎ ይውላል ። ተጨንቀው ተጠበው
ነው ያሳደጓቸው ። ጉንፋን እንኳ ሲይዛቸው፣ ከልጆቻቸው
ይልቅ ራሳቸው ይታመሙ ነበር ። ይሳሱላቸው የነበሩ መንታ
ልጆቻቸውም ቢሆኑ በትምህርት አልሠነፉም ነበር ። እንዴ
ውም፣ አይተኙበት ጀንዲ ሆነ እንጂ ዲግሪ እስከማግኘት ደር
ሰዋል ። በዚህም ሙያቸው ተሾመውበታል፣ ተሸልመ ውበ
ታል ።

“ ልጆቼ ” እያሉ ወላጅ ወይዘሮ ትምክሕተና ባላም
ባራስ ወንዴ ጥሩ ኑሮ በጀመሩበት የተደላደለ ሕይወት ውስ
ጥ፣ ያልጠበቁት ነገር ድንገት ፈነዳ ። የየካቲት ሕዝባዊ ግፊት
ያመጣው ዱብ ዕዳ ነበር ። አዳዲሶች ሁኔታዎች መጡ ። አዳ
ዲሶች ሁኔታዎች ሔዱ ። ነገሮች ተመሰቃቀሉ፣ ተሠበጣጠ
ሩም ። መከሩን ከእንክርዳድ የሚለየው ሰፌድና ወንፊት ሳይ
ቀር፣ በቀጥቃጭ መራጃ ተተክቶ የማይደረገው ተደረገ ። ንፁ
ሐን ያለፍዳቸው ወደቁ ። ግለሰቡ በየምርጫው ወገነ ። በዚ
ህም ድርጊት ላይ መንታዎቹም፣ መሩ እና መራ ነበሩበት ።
የሚደንቀው፣ አሠላለፋቸው ጐራ ለይቶ፣ መሆኑ ነበር ። ካር
ባ ዓመታት በላይ በፍቅር ተሣስረው የነበሩ መንቶች፣ የለየ
ላቸው ጠላቶች ሆኑ ። አንዱ የማዕከላዊ መንግሥት ተጠሪ
ሹም ሲሆን፣ ሌላው፣ፀረ ማዕከላዊ መንሥት ሆኖ ተሠለፈ ።





በየካምፓቸው መሽገው፣ “ ቆይ ባላርድህ! ” በመባባል ይፎ
ካከሩ ገቡ ። ይህን ሁኔታ በስተኋላ ላይ የተረዱ ወላጆቻ
ቸው፣ መግቢያ ቀዳዳ፣ መሸሸጊያ ጓዳ፣ መሮጫ ሜዳ፣
ጠፋባቸው ። የሚሆኑትን አጡ ። የሚመገቡት እስኪያስመ
ልሳቸው ድረስ፣ የመንፈስ ሕመም ተጠናወታቸው ። ደረቅ
ጭንቀት! የልጆቻቸው እንዲያ መሆን፣ “ በእንቅርት ላይ
ጆሮደግፍ ” እንዲሉ እንጅ፣ የስም ዐብዮተኞች አላግባብ የዘ
ረፋቸው ንብረትና ያወረሳቸው ድህነት፣ ብቻውን፣ ለማናደድ
ይበቃ ነበር ። ዘመድ አዝማድ እያጀበ ያሞቅ ያደምቀው
የነበረ፣ ያ ሙሉ ቤታቸው ተበትኖ ጭርታ ዋጠው ። የቅጥር
ሠራተኞቻቸው ሣይቀሩ፣ ነፃ ጐጆ ፍለጋ ተሠማርተው አልተ
መለሱም ። ያልተለዩአቸው ወዳጆች ቢኖሩ፣ ታማኞች መንታ
ድመቶቻቸው ነበሩ ። በዚህ ሁኔታ ሲኖሩ ዐመታት አልፈ
ዋል ። “ በማንም የደረሰ ነው ” እያሉ፣ ያሉበትን ሁኔታ አያ
ማርሩም ።

በሩቅ ያሉ ልጆቻቸው፣ ከየተሠማሩበት ጐራ አልፈው
አልፈው ደብዳቤ ይጽፉላቸዋል ። ባንዳንዱ ደብዳቤ ውስጥ
የሰፈረውን ሐሳብ ሲያነቡ፣ ልጆቻቸው እስከመጨረሻው ባይ
ጽፉላቸው ይመርጣሉ ። እጅግ መራራ ነው ።

ባላምበራስ አንድ ቀን በረንዳቸው ላይ ቁጭ ብለው
የማታ ፀሐይ ሲሞቁ፣ የድሮ የመንታ ልጆች ጓደኛ፣ ሁለት
ደብዳቤዎች አምጥቶ ይሰጣቸዋል ። “ ቤት ግባ! ” የማለቱ
ልምድ ቀርቷልና “ ደብዳቤዎች ከመጡ ሰንብተዋል ። በአ
ደራ በሰው እጅ ነው የተላኩት ። ሥራ በዝቶብኝ ትንሽ ዘግ
ይተውብኛል!” ብሎ ነበር መልእክተኛው ለወንዴ ሰጥቷቸው
ከደጅ የተመለሰው ። ባላምበራስም ደብዳቤዎቹን ይዘው፣ ባለ

ቤት ትምክሕተን እየጠሩ፤ " የልጆችሽ ደብዳቤ መጥቷል! ቶሎ ነይ!" ብለው ማርጀት ወደጀማመረው አሮጌ ሳሎናቸው ያመራሉ። እዚያም እንደደረሱ፣ መንተብ ከሞካከረው ሶፋ ቸው ላይ ጋቢያቸውን አጣፍተው ቁጭ አሉና፤ አዘውትረው የሚያዜሟትን ባለ ልዩ ቅኝትና ቅላፄ እንጉርጉሮ፣ ይዘይሩ ገቡ። ዜማዋ፣ የማንም ልብ አኝካ የምትውጥ ነበረች።

" የመንትዮች እናት፣ ልቧም ሆኖ መንታ፤
ልብረር ልብረር ይላል፣ ወዳሉበት ቦታ፤
አንዱ ወደ ስሜን፣ ሌላው ሰሜን ዋልታ፤
እንደፈረደበት፣ ሔዶ ሲንገላታ፤
ባልፈፀመው ወንጀል፣ በልጆች ትዝታ!

--- " ይቺ የዋይታ ዜማህ፣ አትሰለችህ መቼም! ዛሬ ደግሞ ምን ጽፈውልን ይሆን ? " እያሉ ከባላምባራስ በስተፊት ያለውን የሚዘምር የሳሎን በር ከፍተው፣ ትምክሕተ ይገ ባሉ። ወንዴ፣ ባለቤታቸውን እንዳዩ፣ ዋይታ የተበረዘበት ሣቃቸውን ይለቁታል።

--- " ዛሬ ደግሞ ኩታውን ቀሚስ አርገሽዋል! " አሉዋቸው።

በርግጥም፣ ወይዘሮ ትምክሕተ ኩታቸውን አሸር ጠው፣ ቀሚሳቸውን እንደኩታቸው አጣፍተው ለብሰው ታል። የልጆቻቸው ነገር ልባቸውን ሰልቦት፣ ብዙውን ድር ጊት ልዩ ማድረግ፣ የማይገባቸውን አዘውትረው ያደርጋሉ። ይህ ዐይነቱ ድርጊት በዚያ ቤት የተዘወተረ ድርጊት ሆኗል። የማይገባቸውን ሁል ጊዜ ያደርጋሉ። እንዲህ ያለው ነገር በነዚያ የነሁለቶች ቤት መደረጉ አያስደንቅም። በወዲያኛው ወር፣ አንድ የልጆቻቸው የድሮ ጓደኛ ደብዳቤ ይዞላቸው





መጥቶ፣ አለወትሮአቸው ምሳ ሊጋብዙት አስበው፣ ወይዘሮ ትምክሕተ " ዛሬ ደግሞ ይህ ደብዳቤአቸው ምን ያሰማኝ ይሆን ?" እያለ በሚጨነቅ ልቦናቸውና ቀልባቸው እንዳሉ፣ ማእድ ቤት ገብተው ወጥ ሲሠሩ፣ ዘይት መስሎአቸው ጋዝ ጨምረው በማዘጋጀታቸው፣ እስከ ዛሬ ባላምበራስ፣ በባሌቤ ታቸው ትምክሕተ ላይ ጥሩ መቀለጃና መተረቻ አርገውት ቈይቷል። እንዲያውም እንደቅኔ እየሞከሩቸው "እመ-ጋዝ" (የጋዝ እናት) የሚል መጠሪያ አውጥተውላቸዋል።

--- " አንተዬ! እኔ አያስችለኝ! አንተ ትቀልዳለህ! ያንተን ልብ ምናለበት ነበር የኔ ልብ ቢያረገው ኖሮ! በርግጥ የምት ሆነውን እና የምትሠራውን አይ ነበር! " አሉ ወይዘሮ ትም ክሕተ፣ ያገለደሙትን ኩታ ቀይረው ቀሚሳቸውን እያጠለቁ።

---" አሁን እሱ ያለው ላይቀር፣ ያላለውም ላይሆን፣ ምን በወጣኝ ነው የምጨነቀው! ቀድሞውንም መንቶች አርጎ ሰጠ! በመንታ አቅጣጫ በታትኖ አሠማራቸው! እርስ በርስ ተፃራርያን! አንዱ ሌላውን ሊያጠፋው እንደሮጠ አለ! ታዲ ያንን የኔ የወንዴ ዓቅም ይህን ውትብትብ ሁኔታ እንዴት ሊፈታውና ሊለውጠው ይችላል ብለሽ ታምኝያለሽ ? ከሆነስ ለምንድነው እንዳንቺ እንድጨነቅ የምትጋብዥኝ! መፍትሔ ቢስ የሆነ ራስ አድርቅ ባዶ ጭንቀት! " አሉ የተለመደ የዋ ይታ ለበስ ሳቃቸውን ገርገብ ባለ አፋቸው እየለቀቁት።

--- " የፈሪዎችና የአምቡጋሮች ቋንቋ ብዙና አወዛ ጋቢም ነው! " አሉ ትምክህተ ብው ብለው እንደ መተቸት።

---" ይኸማ ለመላው ወንዶች ተብሎላቸው የለ! በተለይ ያዲስ አበባውማ ወንድ " ነገ ጃን ሜዳ እንዲገኝ፣ አርባ ጅራፍ ትገረፋለህ! ተብሎ ቢታወጅበት፣ ገና ማለዳ ወፍ

ሳይንጫጫ ተነስቶ፣ ለግርፊያው ልብሱን ማውለቅ የሚጀ ምረው፣ እዚያ ታች ራስ መኰንን ድልድይ ላይ ነው " ተብሎ ተተርቶበት የለ! እንደ አባ ገብረሃና ያለ - " የእንዝ ልዝል " - ቀልድ ዓይነት ።


---" አንተዬ! እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ ቀልዱን ተውና! አሁን ያ መሩ አላግባብ ስለ ተፈረደብን የቤት መወ ረስ ጉዳይ ቢሰማ ኖሮ፣ እዚያው አለበት የዱር አምባው ውስጥ ጧ ብሎ ተቃጥሎ አይሞትም ትላለህ! " በንዴት ስሜት በጃቸው ያጨበጭባሉ ።

--- " ያርር እንጂ ትምክሕትዬ! እስቲ ፍትህ መጣ፣ ነፃነት ተገኘ በሚባልበት ዘመን፣ እንዴት ሁለቱንም ክሶች ባንዴ እናጣለን?" አሉ ባላምበራስ፣ ባለፈው ሰሞን የተረቱ በትን ክስ እያስታወሱ ።

--- " አንተዬ! እኔንስ በጣም የገረመኝ የባንኩንም ብድር እንድንከፍል ሲወስኑብን ነው ። እንዴት ያንዳል! ቤቱ ተወርሷል ። እንዲያውም የሚኖርበት ካዲ ደበሉ ካድሪ ነው ። (ስሙ አይያዝ ልኝም) በነፃ ነው የተሰጠው አሉ ። ቤቱ ከተወረሰ የሚጠቀምበት ወራሹ የባንኩን ዕዳ ከነወለዱ መክ ፈል ሲገባው፣ እኛ እንዴት ለማንጠቀምበት ቤት እንከፍ ላለን ? ይህንን ጉድ ያ መሩ ቢሰማ፣ አራስ ነብር ነበር የሚሆ ነው! በእርግጥ አያስችለውም! " አሉ ትምክሕት፣ ኰልል እያለ የሚወርደውን እንባቸውን ከፊታቸው ላይ በመዳ ፋቸው እየጠረጉ ።

--- " አንችንስ ያንገበገበሽ የባንኩን ብድር መክፈል ጉዳይ ነው ። እኔን ግን እየቈጠቈጠ የሚያቃጥለኝና ጤናም የነሳኝ፣ በምኑም በምኑም ከኛ የማይሻል፣ አንድ ጋጠወጥ "





## ካናት ተቀምጦ

ሳይሠራ ሳይገዛ፣ በጉልበት ቀምቶ፣
ሳያስብ ሳያልም፣ በነፃ አግኝቶ፣
ደም ተፍተን ባነፅነው፣ ፎቅ ላይ እንፈራጦ፣
እንዳሻው ይዝናናል፣ ካናት ተቀምጦ።
በሚበርደው ብሩ፣ እያረደ ውስጡ፣
ፈርሱን ያራግፋል፣ በኛ ላይ ከአናት።
ምን እንደሚጠጣ፣ ባናውቅም ሀይነቱን
እንደሸናብን ነው፣ ያን አሊዳም ሽንቱን!
አለቅጥ ጠምበር፣ የሠከረ ለታ፣
እንደናደብን ነው፣ የጠርሙስ እሩምታ
ካቀመ በላይ ውጦ፣ የምግብ አይነቶች፣
ያቀረሸብናል፣ ሸምጋጁን ወደታች።
ሁሉ እያጋዘ፣ ያገር ጋሰሞታ
ካናት እያስካካ፣ ነስቶናል ፀጥታ።
በገዛ ቤታችን፣ ባይተዋሮች ሆነን፣
ኑሮ ተባለና፣ ይኸው እንኖራለን፣
ይህን ሁሉ መዓት፣ ካናት ተሸክመን!

ካዲ ” (ካድሪ ትምክሕተ ካድሬውን እንደምትጠራው) ካናታችን ላይ ተቀምምጦ፣ ተፈናጦ ማለት ይሻል ይሆን፣ ያገሩን ጋለሞታ ሁሉ በየምሽቱ እያፈራረቀ ዳንኪራ ሲረግጥብን፣ በየሰንበቱ የሚያርደውን ሙክት ፈርስ ሲጥልብን፣ በነጋ በጠባ ሲገባና ሲወጣ እየገላመጠ ሲያፌዝብን ዘወትር ማየቱ ነው ።

---“ ድሮም ቢሆን ሲያቀብጠን እንጂ፣ ይህን መሳይ ፎቅ ቤት መቸ ያስፈልገን ነበር ? ” አሉ ትምክሕተ፣ ውርደቱን ያመጣባቸው ፎቁ መሆኑን እያማረሩ ። ሚዶ መስሏቸው ጸጕራቸው ላይ የሰኩትን ሹካ እየሳቁ በማንሳት ። “ ወይ ጉዴ! ዛሬ ደግሞ ሹካውን ሚዶ አርጌዋለሁ ለካ! ” አሉ ሳቃቸውን እያራዘሙ ።

--- “ ፎቅ ቤትነቱስ ምንም አልነበረም ። የብሩን ላለማጥበብና ለሌላውም ወገን እንዲደርሰው ስንል ነበር ወደ ሕዋ የተስፋፋን! እኔን የገረመኝ የአንድ ቁምን መኖርያ ቤት፣ እንደ ትርፍ ቤት ተቈጥሮ፣ ፎቁን ነጥለው መውረሳቸውና ለካዲ መስጠታቸው ነው ። ” አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ ።

---“ምን አለፋህ ወንድዬ! ያ መሩ ይህን በደላችንን ቢሰማ ኖሮ አያስችለውም! መራማ ሁል ጊዜ የሚለው፣ “ ከሰው ጋር የመጣውን ሁሉ እንዳመጣጡ መቀበል ነው ። ” የኛን ጣጣ እሱ አላወቀ ። እዚያ ሃች ተቀምጦስ እንዴት ሊያውቅልን ይችላል! ”

--- “ መራንስ ባንድ ቁምነገሩ አከብሬዋለሁ ። ሀገር ተቈርሶ እንዳይሔድ ኬላውን በመጠበቁ! ” አሉ ባላምባራስ ሻካራ ግንባራ ቸውን እየሰነበሩ ።

---“ አይ ወንድዬ ቢቸግርህ ነው! ምኑን ይጠብቀ





ዋል! ውስጣችን ተራቍቶ እርቃነሥጋችንን ብቻ ቀርተን....” እንባቸው እንደተለመደው ካይኖቻቸው ውስጥ ይፍለቀለቃል ።

---“ አዬ ትምክሕተ! ያስችልሽ እንጂ! እኔ የሚገርመኝ እነዚህን ጥቁር ዓመታት ሁሉ ስታነቢ እምባሽ አለመድረቁ፣ ዓይንሽ አለማለቁ ብቻ ነው ። እድሜአችንም ቢሆን ትንሽ አይደለም ። ብዙ አይተናል ። አላየሽም እንዴ ስንቱ ቀዘባ ወጣት በየፈፋው ወድቆ እንደቀረ ? ተመስገን ማለት ነው! ” አሉ ባላምባራስ ትምክሕተን እያባበሉ ።

---“ ባያድለን ነው እንጂ የምንጦርበት የዕረፍታችን ዘመን ነበር ። እንደሌላውም ቤተ-ሰብ፣ የልጅ ልጅ ከቦን፣ ዘመድ አዝማድ አጅቦን የምንዝናናበት ወቅታችን ነበር ። በመንታ ልጆቻችን ፈንታ፣ መንታ ድመቶቻችን ብቻ ናቸው የቀሩን ። በሩቅ የሚገኙት ልጆቻችንም ቢሆኑ፣ አይጥና ድመት ሆነው አንዱ ሌላውን ለማጥፋት እንዳቋቱ ናቸው ። የዘር እርግማን እንኳ ያለብን አይመስለኝም ። ሁላችንም ወላጆቻችንን በሚገባ ጦረን ተዝናንተው ነው ያለፉት ። ቤታቸው ሁል ጊዜ እንደሞቀ ነው ያለፉት ። የኛ ኑሮ ከነሱ ጋር በምንም አይመሳሰልም ። ሌላው ቀርቶ የቅርብ ዘመዶቻችን ሳይቀሩ፣ በልጆቻችን ሁኔታ ምክንያት ከቤታችን ዝር አይሉም ። ከዚህስ የበለጠ መከራ ምን አለ ? ” .......የማያልቀው እንባቸው ይፈሳል ።

--- “ እንዲያ ቢቸግርሽ እንጂ የሚፈሰው እንባሽ ፏፏቴ ሆኖ ልጆችሽን ከያሉበት ጠራርጎ አያመጣልሽ! ” አሉ ወንዴ ባለቤታቸውን ማባበል ሰልችቷቸው ።

--- “ እሱንስ የኔዋ በዓታ ማርያም ታውቅልኛለች ”

አሉ በተማጥኖ ድምፅ ።

--- " አይ! እንዴው ቢጨንቅሽ ነው! በዓታማ ራሷን አስወርሳ ዝም ብላ የለ! " እንደመሳቅ እየከጀላቸው ወንዴ ባለቤታቸውን ይተቻሉ ።

--- " አንተዬ እሷንስ አትፈታተን! ዝም ያለች አይምሰልህ! ቀኑን እየቀመረች ነው! " አሉ ትምክሕተ የበዓታን ነገር ሲያነሱባቸው አለመውደዳቸውን በመግለጽ ።

---" የሷ ነገር ሲነሳብሽ እንደማትወጂ አውቃለሁ! እሷን ለጊዜው እንተውና እስቲ ዛሬ የመጡልን ደብዳቤዎች ደግሞ ምን ይዘው እንደመጡ እንመልከት! " አሉ ወንዴ ደብዳቤዎቹን እያመቻቹ ።

--- " እስካሁን እንዴት አስችሎህ አስቀመጥከው?" አሉ ትምክሕተ ለማየት ቸኩለው ።

--- " የደንቡን ስጠብቅ ነዋ! የመክፈቻ ጠበል! " አሉ ወንዴ መጠጣት ፈልገው በደብዳቤው ሰበብ ። " የገላጭ ይባል የለ በባሕላችን! ትምክሕትዬ! "

--- " እስቲ ለሁሉም የላኩልንን ደብዳቤዎች እንያቸውና ይሻላል! መርዶም ሊሆን ይችላል እኮ! " አሉ ትምክሕተ በከፍተኛ የጉጉት ስሜት ።

--- " እንዴት ደረቁን እንክፈተው ትምክሕቴ ? ሠቀቀን የሆነብን ደብዳቤ እኮ ነው! የሚጠጣ ጠበል አቅርቢና ይሻላል፣ ለክፉም ለደጉም! " አሉ ወንዴ እንደጠማቸው ለመጠቆም ።

---" እኔን ሞት ይርሳኝ! ቀልቤ ከድቶኝ የለ! ከነጋኮ ምንም አልቀመስክም! የጐረንጎም ቢሆን እኮ ያ የትላንቱ ዳግም አረቄኮ አለ! " ብለው ሊያመጡ ወደ ሌላ ክፍል ይሔዳሉ ።





ባላምባራስ ወንዴ፣ ትምክሕተ አረቄውን እስኪያመጡ ድረስ ዘወትር ብቻቸውን ሲሆኑ የተለመደች እንጕ ርጕሮአቸውን ያላዝናሉ ።

" የመንትዮች እናት፣ ልቧም ሆኖ መንታ፣
ልብረር ልብረር ይላል፣ ወዳሉበት ቦታ፣
አንዱ ወደ ሰሜን፣ ሌላው ሰሜን ዋልታ፣
እንደፈረደበት፣ ሒዶ ሲንገላታ፣
ባልፈፀመው ወንጀል፣ በልጆች ትዝታ!..... "

ወይዘሮ ትምክሕተ ከጓዳ ይዘውት የመጡትን ጠርሙስ ከሳሎን ጠረጴዛ ላይ ያስቀምጣሉ ። ጠርሙሱ ጥቁር ስለነበረ ያረቄውን መጠን አያሳይም ። ዕለቱን ለማዋል ያህል እንደሚበቃ ለመገመት፣ ትምክሕተ ያመጡትን ጠርሙስ አን ስተው ያንቃንቃሉ ።

--- " ለዛሬ ይበቃሃል ወንድዬ - እኔ መቸም ብዙ እንደማልጠጣ ታውቃለህ..... " አሉ፣ የቀረበው መጠጥ ብዙ እንዳልሆነ እየገለጹ ትምክሕተ ።

--- " እሱስ ይበቃ ነበር! ግን ያመጣሽውን ጠርሙስ አይተሻል! " አሉ ወንዴ ውስጥ ውስጡን ሳቅ አፍኖአቸው ።

--- " ምኑን ይሆን ያመጣሁት ? መቸም የኔ ቀልብ ጠፍቷል " አሉ ትምክሕተ ወደ ጠርሙሱ እየተመለከቱ ።

--- " የዘይት ጠርሙስ እንኳ ቢሆን ይሻል ነበር! እኔ የገረመኝ የአዶኮሎኙ ጠርሙስ ከምግብ ቤት ክፍል መግባቱ ነው! " አሉ እየሳቁ ወንዴ ።

--- " ውይ እኔ በጠፋሁ! ለካ ያመጣሁት አዶኮሎኙን ኖሯል! አሉ ትምክሕተ፣ ራሳቸውን በራሳቸው እየታዘቡ ።

---" እኔ የምፈራው እንዴው ጨርሰሽ እንዳትቀው

ሽብኝ ነው! ” አሉ የአዶኮሎኝ ጠርሙስ፣ ሳሎን መምጣት ጉዳይ አሳስቧቸው ።

--- “ እዚያስ አልደርስም! በዓትዬ አለች! ግን እንዴው ለመሆኑ የተሰቀለ ልብ የሚያወርዱበት መድኃኒት፣ ሐኪሞች አይኖራቸው ይሆን ? ብዙውን እየደበቅሁህ ነው እንጂ በየቀኑ የማረገውን ስሕተት ሳስታውሰው፣ ነገሩ አላማ ረኝም !” አሉ እንደመተከዝ አንገታቸውን አቀርቅረው ።

--- “ ውነትሽን ነው! ነገሩ አላማረኝም ። አሁንስ የግድ መፍትሔ መፈለግ ከሚያስፈልገን ደረጃ ላይ ደርሰ ናል ። መቸም ዋናውማ መድኃኒትሽ፣ የልጆችሽ በአንድ ማዕከ ላዊ አቋም ላይ ተደራድረው ቢተባበሩና እንደወትሮአቸው ቢፋቀሩ ነበር !--- ” አሉ ወንዴ እሳቸውም ተክዘው ።

--- “ በዓታ ካለች አንድ ቀን ያደርጉታል! በመሐሉ እኛ ተጐዳን እንጅ......” አሉ ትምክሕተ፣ በምኞት ሰመመን ተውጠው ።

--- “ የኛን መጐዳት ተናገሪ እንጅ፣ እነሱስ የሕይ ወት ድብብቆሽ ጨዋታቸውን መቀጠላቸው የማይቀር ነው ። ‘ በምናምንበት እንሞታለን፣ ’ የሚሉ እምቦሶችስ፣ አንዱ ሌላውን ካላጠፋ ሰላም የሚያገኝ አይመስለኝም ። የማዝነው የነሱ ጦስ እኛን እንዲህ ቀልበ-ቢስ በማድረጉ ነው ። ”

--- “ ወንድዬ፣ ያን ያህል ሔደናል እንዴ ? ” አሉ ትምክሕተ ተደናግጠው ።

--- “ እንዴታ ከዚህ የባሰ ምን ይመጣል ? ” አሉ ወንዴ ፈርጥመው ።

--- “ ያዶኮሎኙ ጠርሙስ ጉዳይ ነው እንዴ እንዲህ ያስመረረህ! ”



አዋልደ-ወንዴ

--- “ ያዶ ኮሎኙ ጉዳይ ቀላል ነው ። በዚያ ሰሞን የሆንሽው ግን ምንጊዜም ቢሆን ከኅሊናዬ አይወጣም! ” እያሉ ማሰላሰል ጀመሩ ።

--- “ የቱን ይሆን ወንድዬ ? ” በከረረ ጉጉት ጠየ ቋቸው ።

--- “ ትምክሕቴ ረስተሽው ይሆናል ። በዚያ ሰሞን መንፈቀ ሌሊት ላይ የሆንሽውን ዘወትር ሳስታውሰው ይዘገ ንነኛል ። ድመቶቻችን፣ ረስተን ባልዘጋነው የበስተግርጌ መስ ኮታችን በኩል ካመሹበት ዘለው ሲገቡ፣ በቀሰቀሱን ጊዜ፣ እን መሩ መጡ ብለሽ በእንቅልፍ ልብሽ መንፈቀ ሌሊት ላይ መስኮቶቹን ሁሉ ከፍተሽ፣ ምግብ ለማምጣት ወደ ማዕድ ቤት ልትሔጂ ስትዪ፣ አከላክዬ ያስቀረሁሽ ትዝ ይልሻል ? በሌሊት ድንገት የሚነቁና ካልጋቸው ላይ ሳያውቁት ተነስ ተው፣ በያጋጣሚው የሞቱ ሰዎች ቍጥራቸው ጥቂት እንዳ ይመስልሽ ትምክሕቴ....... ” አሉ ፈርጥመው ።

--- “ እንደዚህ ካለውስ አደጋ ትጠብቀኛለች - በዓታ የት ሔዳ! ይልቅስ አሁን ካረቄው ፋት ፋት እንበልና፣ ደብዳ ቤዎቹን እናንብባቸው! ” ብለው፣ ካመጡት አረቄ በመለኪያ ይቀዱ ጀመር ።

--- “ እስቲ ቸር ያሰማኝ ” ብለው የደብዳቤዎቹን ኤንቬሎፕ መክፈት ጀመሩ፣ የድርሻቸውን የመለኪያ አረቄ ባንድ ትንፋሽ ከጨለጡ በኋላ ።

--- “ እንግዲህ ረጋ ብለሽ አድምጭ -- መጀመሪያ ከስሜን የመጣውን የመሩን ደብዳቤ አነብልሻለሁ ። በዘመን ማመኑን ትቶታል መሰል፣ ቀኑን አልፃፈበትም ። ”.....

ምንጊዜም ለምትታሰቡኝ ወላጆቼ
አባቴ ወንዴ
እናቴ ትምክሕተ፣

ይህ ደብዳቤዬ እንደሌላው ጊዜ ሁሉ በሰላም እንደ ሚያገኛችሁ ተስፋዬም እምነቴም ነው። ባለንበት ትውልድ ግዳጅ መሠረት፣ የነበረኝን ንብረትና ሥልጣን፣ በተለይም እናንተን ወላጆቼን ዐቅም ባነሳችሁና መጦርም በሚገባችሁ ወቅት፣ ትቼ እዚህ ትግል ላይ በመሠማረቴ፣ የፕሪንስፕሌን ከፍተኛነት ያሳስበኛል። ከዚህ ቀደም እንደገለፅሁላችሁ ሁሉ፣ ያን ከሐዲ ወንድሜን ከነግብረ-አበሮቹ ይዘን ለፍርድ ለማቅረብ፣ የመጨረሻ ዝግጅት እያደረግን ነው። ይህ ያለሁበት ድርጅት ትግላዊ ውሳኔ ይሁን እንጅ፣ በበኩሌ መራን ባገኝ፣ ርኩስነቱን ይጠየፈዋል እንጅ፣ በጥርሴ ነበር የምዘለዝለው። ይህ ባይሆን ደግሞ፣ በጥይቴ ሳይሆን በጠበንጃዬ ሣንጃ ነው የማርደው። የፈጠሩትን ችግር፣ ከኔ ይልቅ በቅርቡ ሆናችሁ በየዕለቱ የምታዩት እናንተና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል። መራ ሞተ ብላችሁ በጭራሽ እንዳታዝኑ። የሕዝብ ጠላቶች መጨረሻቸው አጉል ሞት ነውና። ጊዜው ይርዘም እንጅ፣ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ እንገባለን። ይህ ምኞት ሳይሆን ውሣኔ ነው። ፍላጐትም ሳይሆን ግዴታ ነው። ፍትሕ በሚያምንበት እንበቀላለን። ነገሮች ሁሉ እንዲህ እንደተጨማለቁ አይኖሩም። ልጅ አይ በለውና፣ ያንን መራን እንደረገማችሁት በሐሳቤ እገምታለሁ። ርግማን ሲያንሰው ነው። ዛሬ ብዙ አልጽፍላችሁም። የኔን ስም እያጠፉም ይጽፍላችሁ ይሆናል። ያን ከሐዲ ለመዘረር ዝግጅት ላይ ነኝ።





እንደተለመደው ደብዳቤ ይፅፍላችሁ ከሆነ፣ የሚቀጥለው ደብዳቤ ይዘት የራሱን መርዶ እንደሆነ አትጠራጠሩ። ይህ ዕውን ባይሆን፣ ቃል ለምድር ለሰማይ!

ሁልጊዜ ከሐሳቤ የማልለያችሁ
ልጃችሁ፣ መሩ ( ኤርማ)

ትምክሕተ፣ ከረጅም እንቅልፍ የተቀሰቀሱ ይመስል፣ ሲያዳ ምጡ ቆይተው፤

--- " እኛ እንደሆን ደንዝዘናል! መርዶም ሆነ ልደት አይሰማንም። የሚያሳዝነን፣ እርስበርሳቸው የተጋደሉ መንቶች እየተባሉ መተረቻ መሆናቸው ነው "

--- " አንቺ ስለኛ መደንዘዝ ነው የምታስቢው። ልጆቻችን ግን በየግላቸው አመለካከት የሚያስቡት ስለወደፊቱ ትውልድ፣ ደኅንነትና ብልፅግና ነው። ሁሉም እንደሚሉት፣ ትግላቸው ለጠቅላላው የሃገራችን ሕዝብ መድኅን ለመሆን ነው። ሞታቸውንም ቢሆን የሚቆጥሩት በመሥዋዕትነት ነው። የትኛው ወገን እንደሚያሸንፍና የትኛውስ ወገን ትክክለኛ መስመር እንደያዘ ጊዜ ያሳያል። ላረጋውያኑ እኛ ግን የጠቀመን ፋይዳ የለም። ካዲው እናታችን ላይ ተቀምጦ፣ ይበልጥ እያሰረጀን ነው.... እባክሽን አረቄውን ቅጅልኝ! " ይላሉ ወንዴ።

--- " ደብዳቤውን አንበህ ጨርስ ብዬኮ ነው " አሉና ትምክሕተ አረቄውን ቀዱ።

--- " እውነትሽን ነው! ለብ ካለኝ ወይ እቀንሳለሁ ወይ እጨምራለሁ! እዚያ ደረጃ ሳልደርስ፣ የመራን ደብዳቤ ደግሞ ላንብልሽ " አሉ እየቀለዱ።

*ሚያዝያ* 30- 79 *ዓ.ም.*

ሁልጊዜ በልቤ ላላችሁ ወላጆቼ፣
አባቴ ባላምባራስ ወንዴ
እናቴ ወይዘሮ ትምክሕተ

የተለመደ ሰላምታዬን አስቀድማለሁ።

የዐብዮት ግዴታ ሆኖብኝ በተሰጠኝ ኃላፊነት ስባክን፣ ደብዳቤ ሳልጽፍላችሁ ዘገየሁ። ሆኖም ደኅንነታችሁን ካካባቢያችሁ ካሉ ካድሬዎች እሰማለሁ። መቸም ያ ወንበዴ እንደሚጽፍላችሁ አውቃለሁ። ባለፈው ወር ላይ ለጥቂት አመለጠ እንጅ፣ ከዚህ የተላኩ የነበልባል እሆች ሊማርኩት ነበር። እንዲህ በሀገሩና በዐብዮት ላይ ወንብዶ አይቀራትም። አንድ ቀን ዋጋውን ያገኛል። አንድ ቀን ምርኮ ገብቶ፣ እንደ ተለመደው፣ የፍየል ወጠጤ ይዘየርበታል። አብዶ ይሆናል እንጅ፣ በርግጥ በጤናው፣ ሕዝቡንና ሀገሩን አይከዳም ነበር። ሀገራችን በዓለም የለየላት ምስኪን ሆናለች። በለማኝነትም የመጀመሪያውን ደረጃ ይዛለች። ለዚህ ሁሉ ያደረሷት፣ እንደ መሩ ያሉ ፀረ ዐብየተኞች የቦደኗቸው የወንበዴ ድርጅቶች ናቸው። በስንት አርበኞች መስዋዕትነት የተገነባች ሀገራችን፣ በደምና አጥንት የታነፀች ድንበራችን እንደነመሩ ባሉ ወንበዴዎች መመዝበር የለባትም። የምናካሔደው ትግል የሞትና የሕይወት ትግል ነው። የመጨረሻዋ ደም ጠብታ ድረስ ለሃገራችን ክብር ልንዋደቅላት ቆርጠናል። ይህን የምጽፍላችሁ፣ ያ ወንበዴ መሩ፣ የኔን ስምና ዓላማ በማርክስ፣ አዘውትሮ እንደሚጽፍላችሁ፣ በመገመት ነው። ጽፎላችሁ ከሆነ ሐሰት ነው። እንዲያውም እሱን መሳይ ከሐዲ





ከኛ ቤት መወለዱ ዘወትር ያስደንቀኛል። ዘር የሚያሰድብ ወስላታ ነው። ጭራሽ እንዳትሰሙት። ሌላው ደግሞ፣ ማናቸውንም ዓይነት ችግር ለመታገስ ሞክሩ። ሰው እንደ ሆነው ሁሉ ለመሆን ሞክሩ። የድል ቀን ሩቅ አይደለም። ጠቅላላው ሀገር ሁሉ ነፃ ሲሆንና ነባር ሰላም ሲሠፍን፣ እኔም እዚያው አዲስ አበባ መጥቼ አብረን እንኖራለን። የዚያን ወራዳ ወንበዴ ልጅነትና ሕይወት ግን፣ ብዙ ጊዜ እንደ መከርኳችሁ ሁሉ፣ መሠረዝና እስከ መጨረሻም መርሳት ይኖርባችኋል።

ምንጊዜም በመንፈስ የማልለያችሁ
አንዱ ልጃችሁ
*መራ (ሎርማ)*
ኢትዮጵያ ትቅደም።

--- " ሰማሽው አይደለም ትምክሕትዬ! መንታ ልጆች ቢኖሩን ከመንታ ድመቶቻችን የተሻሉ አልሆኑም። አንዱ ሌላውን ሠርዞ ይላል። *1-1 = 0* ለማለት ነው። ድሮውንስ ቢሆን ' የስለት ልጅ ' ይባል የለ። አለመታደል ነው! " አሉ ባላምባራስ ወንዴ አለወትሮአቸው እንደመመረር ብለው።

--- " ወንድዬ! ዛሬስ እኔ ነኝ በደንብ መጠጣት ያለብኝ! " አሉና ትምክሕተ መለኪያቸውን እስካፍጢሙ ሞልተው ጭልጥ አረጉት። በዚያው ቢበቃቸው እንኳ ደግ ነበር፣ ደገሙት።

--- " ትምክሕተ በነገር መቃጠሉ አንሶሽ፣ የመጠጡን ቃጠሎ ባትጨምሪበት ደግ ይመስለኛል! " አሉ ወንዴ

በባለቤታቸው ያልተለመደ ድርጊት ተደናግጠው ።

--- “ ትጠጣ እንደሆን ልቅዳልህ! ድህነታችንን ሳይሆን ልጆቻችንን የሚያስረሳን ሌላ መፍትሔ ያለ አይመስለኝም! ” አሉ ትምክሕተ፣ እንደበታቸው በመጠጡ እንደ መለፋደድ እየቃጣው ።

--- “ ለጤናችን! እንኳ ከእንግዲህ ማለቱ አያዋጣም..... ትምክህተ፣ ለሞታችን-ፅዋችንን እናንሳ! ” ብለው፣ ያቺ ያረቄ ጠርሙስ ጠብታዋ እስክታልቅ ጠጥተው ጨረሱ ። በስተምሽቱ ላይም፣ እንደምንም እየተንገዳገዱ፣ ተያይዘው አልጋቸው ላይ ወደቁ ። መንቃታቸውን ያየ አንድም ሰው ባይኖርም፣ እንቅልፍ ሊወስዳቸው ገደማ፣ ባላምባራስ ወንዴ፣ እንደ ‘ ደጎና አሳድረኝ ፀሎት ’ ያቺ የተለመደች እንጉርጉሮአቸውን ሲያላዝኑ ይሰማ ነበር፤

“ የመንትዮች እናት ልቧም ሆኖ መንታ፤ ..
ልብረር ልብረር ይላል፣ ወዳሉበት ቦታ፤
አንዱ ወደ ሰሜን፣ ሌላው ሰሜን ዋልታ፣
እንደፈረደበት፣ ሔዶ ሊንገላታ፣
ባልፈፀመው ወንጀል፣ በልጆች ትዝታ!.....
መከረኛ፣ እናት፣ መንታ ልጆች ወልዳ፣
አንዱ፣ ሳት፣ ሌላው ማይ፣ ፅሩራን ዱብ ዕዳ፣
ወግ ደርሷት፣ ሳትጦር፣ ባልሠራችው ፍዳ፣
ሳትኖር፣ ልትሞት፣ ነው፣ ሕይወት ሆኗት፣ ባዳ....”

ለጊዜው አበቃ



# የ ተ ጣ ሰ  አ ጥ ር



“ ወጋ ወጋ አድርጐ እዚያም እዚህ ምድር!
የኔም ሆነ ያንቺ ግዴታኮ ነበር!
ማንም የጣሰውን እንደገና ማጠር! “

( የጠፍ. ቁ.4)